## ጨርሶ የማዳከሚያው
## አዋጅና ጦሱ።።

ከላይ የተጠቀሰው፡ ከሰሞን መሬት የሚሰበሰበው ገቢ፡ በዚያ መልክ እየተሠራበት ሣለ፡ ያንን የሚሽርና አዲስ የመሬት ግብር አከፋፈልን የሚተካ፥ ቤተ ክህነትም፡ ያንኑ የቆየውን አነስተኛ ገቢዋን ሳይቀር እንድታጣ የሚያደርግ፡ "የእርሻ ገቢ ግብር" የተባለ አዋጅ፡ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. ወጣ!

በዚያ አዋጅ ውስጥ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ ያላትን ብሔራዊ መብት፡ በዘመናዊ መልክ የሚያስከብር፡ አንዳች አንቀጽ ሊሰጠው ቀርቶ፡ እንዲያውም፡ እንደተለመደው፡ ያ፡ ጥንታዊና ቋሚ መብቷ፡ ኾነ ተብሎ፡ መሠረዙን የሚያረጋግጡ፡ የትርጉም ሐተታዎች የሚገኙበት ኾኖ እንዲወጣ ተፈቀደ! ቤተ ክህነት፡ እኒያን ኹሉ፡ እልፍ አእላፍ የአገልግሎት ሠራዊቷንና የአገልግሎት ተቋማቷን የምታስተዳድርበት የገቢ ምንጭ፡ በዚያ አዋጅ፡ እንዲያ፡ በአንድ ጊዜ፡ እንዲደፈን ሲወሰን፡ በዚያው አዋጅ ላይ፡ ስለዚሁ ውሳኔ፡ በግልጽ የሚናገር፡ ምንም ዓይነት ሕጋዊ አንቀጽ ተጽፎ እንዲታከልበት አልተደረገም።። ምክንያቱም፡ ያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ የእግዚአብሔር ስም ስለሚጠራባት ቤትና ስለእርሱ አገልጋዮች፡ ከነበረው ንቀት ጋር፡ ምንም ደንታ ያልነበረው በመኾኑ እንደነበረ፡ እነሆ፡ በዚያ አዋጅ፡ በይፋ አሳየ።።

ታዲያ፥ እንዴት ይኹን! በዚያን ጊዜ፡ በወር ቀርቶ፡ በዓመት፡ ፲ (አሥር) ብር የማይከፈላቸው፡ እኒያ፡ በየዳር አገሩ ሳይቀር ወድቀው፡ በመዓልትና በሌሊት፥ በማያቋርጥ ትጋት፥ በጾም በጸሎት ተጠምደው የሚያገለግሉት ምስኪኖች ካህናት፡ ያም "በዛባቸው!" ተብሎ፡ ሊቀርባቸው ይኾን? እነርሱስ ችለውት ኖረዋል! ይህን ግፍ በሚፈጽምባቸው ግፈኛ ላይ የሚፈርደው አምላክ፡ ይህን ግፍ ዝም ብሎ የሚመለከተው እስከመቼ ነው? አዬ! የፍጡር ደካማነትና አለማወቅ! ለካ፡ ለግፈኛውም፡ በሰፊው የተሰናዳለት፡ ድግሥ ኖርዋል!

በአዲስ አበባ፡ ከዋናው መሥሪያ ቤት ጀምሮ፡ ራቅ ባሉት ክፍላተ ሀገር እስከተመደቡት ካህናትና ሠራተኞች ድረስ፡ ለኹለት፥ ለሦስት ወራት ያህል ደመወዝ ሳይከፈላቸው እየቀረ፥ በተለይም፡ እጅግ የሚያሳዝነው፡ ትንሣኤን የመሰለ፡ ታላቅ በዓል በሚከበርበት ጊዜ፡ የሚፈስኩበት እንዳያጡ፡ ሌላ አማራጭ እየጠፋ፡ ቤተ ክህነት፡ ያላትን ንብረት እያስያዘች፡ ከቤተ ንዋይ (bank ባንክ) ገንዘብ በመበደር፡ የክፍያ ግዴታዋን ትፈጽም እንደነበረ፡ የቅርብ ትዝታዬ ነው።።

ቤተ ክህነት፡ ያንኑ፡ ታገኘው የነበረውን፡ የራሷን፡ ታናሽ ድርሻ እንኳ እንዳትሰበስብ፡ በዚህ፡ በአዲሱ አዋጅ ስለታገደች፥ ከዚህ ችግር እንድትወጣ፡ ይህን ለማድረግ ሥልጣን ወደተሰጠው፡ ወደገንዘብ ምልክና (ministere ሚኒስቴር) ኼዳ፡ እንደደጀጠኒ አቤቱታዋን በምታቀርብበት ጊዜ፡ ከምሉኩ፡ ይገኝ የነበረው መልስ፡ "የኃላፊነት ሥራዬን የማካኺደው፡ በአዋጁ መሠረት እንጂ፡ ከዚያ ውጪ የማደርገው ምንም ነገር የለም!" የሚል በመኾኑ፡ ያለው ዕድል፡ ጉዳዩን፡ ለአጼው ማቅረብ ብቻ እየኾነ፡ በዚሁ መስመር አቤቱታዋና ደጅ ጥናቷ ይቀጥል ነበረ።።

ይባስ ተብሎ፡ መብቷ፡ በአዋጅና በሕግ ሊረጋገጥላት ይገባ የነበረችው ቤተ ክህነት፡ አሁን፡ በጽሕፈት ምልክና (ministere ሚኒስቴር)፡ የቀላጤ (የቃለ አጼ) ደብዳቤ ብቻ ተወስኖ፡ የቤተ ክህነትን ድርሻ፡ እየሰበሰበ እንዲሰጣት፡ የገንዘብ ምልክና ታዘዘ! ቤተ ክህነትም፡ በአጼው ትእዛዝ መሠረት፡ ድርሻዋን እንዲከፍላት፡ የገንዘብ ምልክናን ስትጠይቀው፡ "የታዘዝኩት፡ ሲሰበሰብ እንድሰጥ ስለኾነ፡ አሁን የተሰበሰበ ገንዘብ ስለሌለ፡ የምሰጣችሁ የለም!" በሚል ምክንያት ማጉላላቱን ጨማመረበት:: "'የትምህርትና የጤና ግብሮች አልተሰበሰቡምና፡ የምሰጣችሁ የለም!' ብለህ፡ የትምህርት ምልክናንና የጤና ምልክናን ትመልሳቸዋለህን? አትመልሳቸውም! ግዴታህ ስለኾነ፡ ባይሰበሰብም፡ ከሌላ ፈላልገህ ትከፍላቸዋለህ! ግብሩን መሰብሰቡም፡ ያንተ ተግባር ነው:: ለቤተ ክህነትም፡ ማድረግ የሚገባህ ይኸው ነው" ተብሎ፡ ከቤተ ክህነት፡ መልስ ቢሰጠውም፡ ምክንያቱን በቂ አድርጎ ሊቀበለው ፈቃደኛ አልነበረም::

ስለዚህ፡ "ይግረማችሁ!" ተብሎ፡ በደብዳቤ የተላለፈው ቀላጤ፡ አሁንም፡ እንዲህ፡ ተፈጻሚነት የሌለው ኾኖ ስለተገኘ፡ ለቤተ ክህነት፡ የነበራትና የቀራት ግዳጅ፡ አንድ ብቻ ነበረ:: እርሱም፡ ችግሩ በደረሰ ቁጥር፡ ጉዳዩን፡ በየጊዜው፡ ለአጼው በማብራራት፡ አቤቱታ ማቅረብና እርሳቸው ሹመው፡ በቦታው ላይ የመደቧቸው፡ የገንዘቡ ምሉክ (ministre ሚኒስትር)፡ ካቶሊካዊው አቶ ማሞ ታደሰ የተባሉት፡ ተጠርተው፡ በግንባር ሲገኙ፡ እየተለመኑ፡ ትእዛዙን እንዲፈጽሙ ማድረግ ነበር:: ምናልባት፡ አጼው፡ በቅርብ ሊገኙ የማይቻልበት ኹኔታ ሲፈጠር፡ ችግሩዋን ለመወጣት፡ ለቤተ ክህነት የነበራት ዕድል፡ ያው፡ እንደተለመደው፡ ወደቤተ ንዋይ ሄዶ፡ ከላይ የተገለጸውን፡ ንብረቷን እያስያዘች፡ ገንዘብ በመበደር፡ ግዳጇቿን መወጣት ብቻ ነበር:: ይህን የመሰለው ውጣ ውረድ፡ እስከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም ድረስ ቀጥሎ፡ ያን የመሰለው ግፍ፡ ባመጣው የቅጣት ዓመፅ ሊያበቃ ቻለ!

እንዲህ ነበር፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት! የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ መለኮታዊና ሕጋዊ መብቷን አላገባብ ተነጥቃ፡ ከዚያ የቀራትም ቢኖር፡ ያንኑ ለማስከበር፡ ለካቶሊካዊው ባለሥልጣን እያጎበደደች፡ ደጅ እንድትጠና ተገድዳበት የነበረው ፍዳዋ!

## የባለ"ሲሶዋ መንግሥት"
## የቤት ኪራይ ገቢ::

የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ በዚህ ብቻ አላበቃም! የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት፡ እንደሌሎቹ ባዕዳን ሃይማኖቶች ኹሉ፡ የቤት ኪራይን ከመሰለው ገቢዋም ላይ፡ "ለመንግሥት ግብር መክፈል አለባት!" የሚል መመሪያ፡ ከዚሁ በካቶሊካዊው ባለሥልጣን ከሚካኼደው መሥሪያ ቤት ተላለፎ፡ ያን መምሪያ፡ ተግባራዊ ለማድረግ፡ በባለሥልጣኑ በኩል ሙከራው፡ በከፍተኛ ኃይልና ጥድፊያ ይካኼድ ጀመር::

የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የኾኑት: እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባቸው: በጌምድርና ጎጃም: ከባዕዳን ጠላቶች ዘንድ ከሚገኘው: ከማናቸውም ሥጋዊ ብልጽግና ይልቅ: የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸው መታወቂያ የኾነውን: የቅዱሱ ኪዳን አምላካቸውን: እግዚአብሔርንና የድህነት ነፃነታቸውን በመምረጥ: ጠርጥረውና ጨክነው: "ከአዲሱ የባዕዳን ሥርዓት ይልቅ: የራሳችን: የጥንቱ ይሻለናል!" ያሉበት: ያ: ከላይ የተገለጸው ምክንያት: አሁን ግልጽ እየኾነ መጣ! እነርሱም: ፈርተውት የነበረው: ይህንኑ ነበር!

"የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው: ኢትዮጵያ: ከቤተ ምልክናውና ከቤተ ሕዝቡ ጋር: አንድ አካል የኾነችው: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: ራሷ: በእንግድነት እየተቀበለች እንዳስተናገደቻቸው: ባዕዳን ሃይማኖቶች ታይታና እንደእነርሱ ተቈጥራ: እርሷ: ለዚያ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥትና ለኢትዮጵያ ሕዝብ: ሌላው ቢቀር: በመንፈሳውያት ምግባራቷ አማካይነት ለምትሰጠው አገልግሎት: የሚገባትን ድርሻ ተነፍጋ እያለች: ይህ አንሦ: አሁን ደግሞ: ወደባዕድነት ደረጃ: ዝቅ እንድትል በማዋረድ: 'ለራሷ መንግሥት ግብር ትክፈል!' መባሉ: ተገቢም፥ ትክክልም፥ ሕጋዊም አይደለምና: ትእዛዙ ይነሣላት!" የሚል: ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮችን ያከለ ማስታወሻ: ከቤተ ክህነቱ: ለአጼው ቀረበ።

እርሳቸውም: እንደተለመደው: ጉዳዩ የሚመለከታቸው: ምሉካን (ministres ሚኒስትሮቻቸው): በአባልነት በሚገኙበት: "ይጠና!" ብለው: ስላዘዙ: እኔ: በቤተ ክህነቱ ስም: በአስረጅነት እየተቀመጥኩ: ጉዳዩ ተመርምሮ ሲያበቃ: የውሳኔው አሳብ: ለአጼ ኃይለ ሥላሴ እንዲቀርብ ተላለፈ። እርሳቸው: በዙፋናቸው በተቀመጡበት እንዲታይ በተቀጠረበት ቀን: በስተቀኝ: በቤተ ክህነቱ ወገን: እጨጌ ቴዎፍሎስ: የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የኾኑትን ሊቃነ ጳጳሳት ይዘው፥ በስተግራ: በቤተ ምልክናው ወገን: ጸሓፌ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተ ወልድ: የምሉካኑን (ministres ሚኒስትሮች) ምክር ቤት አባሎች ይዘው በተገኙበት: እኔ ጭምር: በዚያ ታላቅ ጉባዔ እንድሣተፍ ተፈቅዶልኝ ባለሁበት: ያ: ቤተ ክህነትን በሚጎዳ መልክ የተዘጋጀው: የውሳኔ አሳብ ተነበበ። ቀጥሎ: ከኹለቱም ወገኖች መሪዎች: አንዳንድ ትችትና አስተያየት ከተሠነዘረ በኋላ: ሌሎቹ: የጉባዔው ተሣታፊዎች: በተለይም: ከሊቃነ ጳጳሳቱ መካከል: የውሳኔውን አሳብ በመቃወም: ይናገራሉ ብዬ ስጠባበቅ: ኹሉም ዝም አሉ።

## የስቅላቱ ገመድ:
## ማነቆው ሲታገድ።

የጉባዔው አካኼድ: ከዚህ ደረጃ ደርሶ: አጼ ኃይለ ሥላሴ: የውሳኔውን አሳብ በማጽደቅ: የመጨረሻ ቃላቸውን ሊያሰሙ በተዘጋጁበት አፍታ: ልቆጣጠረው ያልቻልኩትና ከዓቅሜ በላይ የኾነ: ኃይል: ከውስጤ ገፋፍቶኝ: ማንም ሳያስበው: ድንገት ብድግ ብዬ: "ጃንሆይ! እንድናገር ይፈቀድልኝ!" አልኳቸው። እርሳቸውም: ከአንደበቴ ሊወጣ የተዘጋጀውን ቃል ባለማወቅ: "ደግ! ተናገር!" አሉኝ። በኋላ ካየሁት ኹኔታ: ለመገምገም እንደቻልሁት: የምናገረውን አውቀውት ቢኾን ኖሮ: አይፈቅዱልኝም ነበር። የፈቀዱልኝ: እርሳቸው የፈለጉትን የምናገር መስሏቸው ሳይኾን እንዳልቀረ ገምቻለሁ።

በዚያን ጊዜ: አሁን ለቀረበው የውሳኔ አሳብ; መነሻ የኾነው ያ ማስታወሻ: የመነጨው: ከማን እንደኾነና ምን ኃይለ ቃል እንደያዘ እንደዘነጉት ታወቀኝ::

የተናገርሁትም: ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት: በዚህ ፹ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠውን ሐተታ: በአጭር ቃል አጠቃልዬ በማቅረብ ነበር:: እስከዚያች ቀን ድረስ: ለአገሪቱ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር አገልግሎት፥ የነጻነት ህልውና፥ የማኅበራዊ ኑሮ፥ የበጎ አድራጎት፥ የፍትሕ አያያዝ፥ የትምህርት አሰጣጥ፥ የሥነ ጥበብና የኪነ ጥበብ ዕድገት፥ የጤና ጥበቃ፥ የሰላም ስፍነት፥ የፀጥታ ሕይወት፥ የሥነ ፍጥረት እንክብካቤ፥ የባህል ምንጭነትና የታሪክ ባለአደራነት፥ ለመሳሰሉት ይዘቶች ኹሉ: መሠረታዊው ምክንያት: የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት መኾኗን አስረዳሁ:: በዚህ ረገድ: ቤተ ክህነት: ለአገሪቱ፥ ለመንግሥቱና ለሕዝቡ ለሰጠችውና ለምትሰጠው አገልግሎት: የሚገባትን ድጋፍ እንዳላገኘችና ለወደፊትም ልታገኝ እንደሚገባት: በጉባዔው ላይ ለነበሩት: በሚገባቸው ቋንቋ አብራራሁ:: "ስለዚህ: ይህ: የኢትዮጵያ የዘውድ መንግሥት ጸንቶ እስካለ ድረስ: አቋሙም፥ ሥርዓቱም፥ ሕጉም የማያስኬድና የማይፈቅድ ስለኾነ: ቤተ ክህነት: በምንም መንገድ: ግብር ከፋይ መኾን እንደማትችል: መታወቅ አለበት!" በማለት: በመንፈሳዊ ስሜትና በኃይለ ቃል ያሰማሁትን ንግግር: እጅ በመንሳት አበቃሁ::

ይህ ንግግሬ: በኹለቱም ወገኖች በኩል የነበሩትን: የጉባዔውን ተሣታፊዎች ብቻ ሳይኾን: የአጼ ኃይለ ሥላሴንም ልብ የነካ መሰለኝ፤ ምክንያቱም: የነበረው የደስታ ገጽታ: ከፊታቸው ተለይቶ: ከአንደበታቸው ለጥቂት ሊያወጡት የነበረውን ውሳኔያቸውን እንዲያግዱ አደረጋቸውና: "ጉዳዩ ይቆይ!" ብለው: በቁጣ ድምፅ: ጉባዔው እንዲያበቃ አዘዙ! ተሣታፊዎቹም: በተለይ ጳጳሳቱ: በጃንሆይ ቁጣ ተደናግጠው፥ ምሉካኑም: ጉዳዩ: እንደጠበቁት ሳይወሰን በመቅረቱ ተከዘው: ኹላችንም: እጅ እየነሣን ተመለስን::

## ኢትዮጵያ:
## የአጼዋን፥ የጳጳሳቷንና የምሉካኗን
## ሃይማኖትና ምግባር ስትፋረድ!

በዚህ ጉባዔ ላይ በኾነውና: ቀደም ብለው በደረሱ ተመሳሳይ የቤተ ክህነት ጉዳዮች የተነሣ: የእግዚአብሔርን እውነት በመያዝ ብቻ፥ ደግሞም: "በፍቅር ፍርሃት የለምና": ማንንም፥ የምወድዳቸውን: አጼ ኃይለ ሥላሴን ሳይቀር: በምንም ሳልፈራ: ለዚያን ጊዜ ተጠሪ አገልጋይዋ ኾኜ እንድቆምላት ለተሠየምኩላት: ለኢትዮጵያ ቤተ ክህነት: ያበጀሁ፥ ፈጣሪዬን ብቻ ሳይኾን: ሺሚዎቼንም ጭምር ያስደሰትኩ እየመሰለኝ: ስለምሟገትላትና ስለምከራከርላት: ለካ! እንደዛሬው ኹሉ: እኔ ሳላውቀው: ብዙዎችን አሳዝኜ ኖሮ: በተለይ በዚህ ጉባዔ ላይ በተናገርሁት ቃል ምክንያት: በከፍተኛ ደረጃ: ተግሣፅና ጥቃት ደረሰብኝ! እኔ ግን: ከዚያ አቋሜ: ላርመው፥ ላስተካክለውና ላሻሽለው የምችል: አንዳችም ነጥብ ስላልነበረኝ: ተግባሬን ከማከናወን: ወደኋላ ሳልል: በዚያው አካሂዴ: ሥራዬን ቀጠልኩ::

በዚያን ጊዜ፡ በማደርገው ኹሉ፡ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀኝና እንደሚመራኝ በመታመኔ፡ ያንኑ ሥራዬን የቀጠልኩት፡ ከተጣለብኝ ኃላፊነት አኳያ፡ ትክክልና ተገቢ እንደኾነ አድርጌ በማመን ነበረ፡፡ እንዲሁም፡ በየኃላፊነቱ ቦታ ላይ በሹመት የተመደብሁት፡ በእኔ ጥያቄና ፍላጎት ሳይኾን፡ ሳላስበው፡ ድንገት እየተጠራሁ በመኾኑ፥ ፈጣሪዬ ብቻ ሳይኾን፡ ሿሚዎቼም ጭምር፡ ከእኔ የሚጠብቁት፡ ለተሰጠኝ ኃላፊነት፡ ፍጹም ታማኝ ኾኜ፡ ግዳጄን መፈጸሜን መኾኑንም በእጅጉ አምንበት ነበር፡፡

## የተግሣፁ ምልክትነት፡፡

ዳሩ ግን፡ በኹሉም ወገን የገጠመኝ፡ እኔ እንደጠበቅሁት ሳይኾን ቀረ! በእኔ በኩል፡ ጥረቴና ድካሜ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት፡ ከተከተለው፡ ከሰፊው የጥፋት ጐዳና፡ ራሱን፡ በንስሐ መልሶ፡ ጥንቱኑ፡ የገባውን ቃል ኪዳን ተከትሎ፡ በጠባቢቱ የእግዚአብሔር መንገድ በመጓዝ፡ ከውድቀትና ከመፈራረስ እንዲድን ለማገዝ ነበር፤ ዳሩ ግን፡ በሌላው በኩል፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ ያ ጥረቴና ድካሜ የታየው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘንድ ሳይቀር፡ በተቃራኒ ገጽታ መኾኑን በግልጽ አወቅሁት! ይህንንም የተረዳሁት፡ ወደመጨረሻው ጊዜ፡ "የሾምንህ፡ የመንግሥታችንን ሥራ ልታደናቅፍ አልነበረም!" የሚለውን፡ ከባድ የተግሣፅ ቃል፡ ከግርማዊነታቸው አንደበት፡ በመስማቴ ነበር፡፡ ይህም ከኾነ በኋላ፡ በእኔ በኩል፡ በእርሳቸውም ኾነ በመንግሥታቸው፥ በፍቅሬም ኾነ በተግባሬ፡ አንዳችም ለውጥ ሳይኖረኝ፡ የተለመደ ሥራዬን ከማካሄድ ወደኋላ አላልሁም፡፡

ሰው፡ ከተፈጥሮ ሕፁፅነቱ የተነሣ፡ አለማወቁ እንጂ፡ ያን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን፡ ገናና መንግሥት፡ እኔ ደካማው ፍጡር፡ እንዴት ሥራውን ላደናቅፍ እችላለሁ? የራሱ፡ የኃጢአቱ ጽዋ ከሞላና ከዚያ ኃጢአቱም፡ በንስሐ አልመለስ ካለ፡ ማደናቀፍ ብቻ ሳይኾን፡ ሊያፈርሰውም የሚችል፥ ሊፈርስ ይገባል ብሎ የሚወስንና እንዲፈርስ የሚያደርገውም፡ ታላቁ ዳኛ አለ አይደለምን? እርሱም፡ የኢትዮጵያውያን፡ የቃል ኪዳን አምላክ የኾነው፡ እግዚአብሔር ነው፡፡ ታዲያ፥ ይህ፡ እንዴት ሳይታወቅ ቀርቶ ነው፡ እኔ፡ ያን በመሰለ ቃል የተገሠፅኩት? አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ያን የመሰለውን ተግሣፅ፡ በእኔ ላይ ሲሠነዝሩ፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ፡ ራሳቸው ሲመለከቱት የኖሩትን፥ በየጊዜያቱም ሲነበብና ሲተረጐም ይሰሙት የነበረውን፡ የነቢያቱን፡ የሳሙኤልንና የኤልያስን፥ ደግሞም፡ የእስራኤልን ነገሥታት፡ የሳዖልንና የአክዓብን ታሪክ፥ እንዲህ ከሚለው፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር፡ ዘንግተውት ይኾን?

በመጀመሪያ፡ *"ንጉሡ፡ ሳዖልም፡ ነቢዩን ሳሙኤልን፡ 'የእግዚአብሔርን ትእዛዝና የአንተን ቃል በመተላለፍ፡ ሕዝቡን ስለፈራሁ፥ ቃላቸውንም ስለሰማሁ፡ በድያለሁ፤ አሁንም፡ እባክህ፡ ኃጢአቴን ይቅር በለኝ! ለእግዚአብሔርም እሰግድ ዘንድ፡ እባክህ ተመለስ!' አለው፡፡ ሳሙኤልም፡ ሳዖልን፡ 'አንተ፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንደናቅህ፡ እግዚአብሔርም፡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ እንዳትኾን፡ ንቆሃልና፤ ከአንተ ጋር አልመለስም' አለው፡፡ ሳሙኤልም ሊኼድ ዘወር ሲል፡ ሳዖል የልብሱን ጫፍ ያዘበት! ልብሱም ተቀደደ! ሳሙኤልም፡ 'እግዚአብሔር፡ የእስራኤልን መንግሥት፡ ዛሬ፡ ከአንተ ቀደዳት!' አለው፡፡"* የሚለው ነው፡፡

*ቀጥሎ: "ንጉሡ አክዓብ: ነቢዩ ኤልያስን ሊገናኘው መጣ:: አክዓብም ኤልያስን ባየው ጊዜ: 'ጠልና ዝናምን ከልክለህ: እስራኤልን እንዲህ የምትገለባብጥ አንተ ነህን?' አለው:: ኤልያስም: 'እስራኤልን የምትገለባብጡ: የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ: ጣዖታችሁን በኣሊምን የተከተላችሁ: አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ: እኔ አይደለሁም!' አለው::*[፻፷፬]

አዎን! እግዚአብሔር: ለዚያ እምቢተኛ: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የተደገሠለት: ምን እንደኾነ እያወቀ: በዚያ ታላቅ ጉባዔ: ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ኹሉ ያሰባሰበው: እያንዳንዱ: የጉባዔው ተካፋይ: ምን እንደሚል ሊሰማና ሊታዘብ፥ ሊፈርድም መኾኑ: ተከታትሎ በደረሰው አሳዛኝ ፍጻሜ ታይቷል::

## ኢትዮጵያ: ምንኵስናንና ጵጵስናን ስትፋረድ!

ለእኔ: ያ ጊዜ: ባንድ ወገን: ከውጭ: በቤተ ክህነት ላይ የሚወርደውን ይህን የመሰለውን: ከባድ ፈተና ለመቋቋም የምታገልበት ሲኾን: በሌላው ወገን ደግሞ: ሌሎቹን የኃላፊነት ግዴታዎቼን ከመወጣት ጋር: የቤተ ክህነትን የውስጥ አስተዳደር: በዘመናዊ መልክ በማሻሻል: በገቢም ረገድ: ራሷን እንዲያስችል ታስቦ: በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት: በዚያን ጊዜ: ለአዲስ አበባ ከተማ: ኹለገብ የሕዝብ መገልገያ እንዲኾን: በቤተ ክህነት የተዘጋጀውን: ባለብዙ ደርብ ታላቅ ሕንፃ በማሠራትና በአጠቃላይ: ለቤተ ክህነት ችግሮች ኹሉ: መፍትሔ ይኾናል ተብሎ: በቃለ ዐዋዲ የታወጀውን: የሰበካ ጉባዔ: በአዲስ አበባና በየክፍለ ሀገሩ እየተዘዋወርኩ በማቋቋም: የምጣደፍበት ወቅት ነበር::

በዚያን ጊዜ የነበረብኝ ችግር: ከውጭው ይልቅ የውስጡ እየከፋ መኼዱን የሚያመለክቱ ኹኔታዎች እየተከሠቱ ነበር:: ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን እንድጠቅሳቸው የሚያስፈልግ ይመስለኛል:: የሰበካ ጉባዔ መመሪያና ደንብ: በቃለ ዐዋዲ ታውጆ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት: በቅድሚያ: የቤተ ክህነትን ጠቅላላ አቋምና አመራር: በኹለንተናው: ማሻሻል አስፈለገ፤ ስለዚህ: ለሃይማኖታዊው ወገን: ጳጳሳቱ: በቋሚ አባልነት የሚገኙበት: "ሲኖዶስ" የተባለው መንፈሳዊ ጉባዔና ለሥጋዊው ወገን ደግሞ: በረዥም ጊዜ አገልግሎታቸው: ያካበቱት የሥራ ልምድ እየታየ: በመንግሥት ተጠሪነት ጭምር: የተመረጡ ምእመናን: በአባልነት የሚገኙበት: የአስተዳደር ጉባዔ: ኹለቱም ጉባዔያት: በየግላቸውና በጋራ የሚመሩበት ሥርዓት ተሻሽሎ ወጣ፤ የቤተ ክህነቱ ዋና መሥሪያ ቤት: በመምሪያዎች ተከፋፍሎ: ለኃላፊዎቹ ሙሉ የተጠያቂነትና የተጠሪነት ሥልጣን በመስጠት: ሥራው: እስከዘርፍ ጽሕፈት ቤቶች ድረስ: በቅልጥፍናና በሠመረ ይዞታ እንዲካኼድ የሚያስችል አቋምና መምሪያ ደንብ ተሰጠ፤ የቤተ ክህነትን: ዓመታዊ የገቢና የወጪ ድልድል (budget ባጀት) በዘመናዊ የሒሳብ ስልትና ሥርዓት እንዲያዝ ተደረገ፤ አቋሙና አመራሩ: በዚህ መልክ ተሻሽሎ መካኼዱን ስለቀጠለ: በኃላፊነቴ: ሥራውን: በበላይነት ለመምራትና ለመቆጣጠር፥ በተለይም: የሰበካውን ጉባዔ ለማቋቋም: በየቦታው ለመዘዋወር ችግር አልነበረብኝም::

## የጳጳሳት የተሳሳተ ቅሬታና ሕገወጥ ድርጊት፡፡

ይኹን እንጂ፡ በተሻሻለው የአመራርና የአስተዳደር ሥርዓት፡ ጳጳሳቱ፡ በሲኖዶሱና በአስተዳደሩ ጉባዔያት አባልነታቸው፡ ያላቸው የቤተ ክህነት ሥልጣን፡ ሕግ አውጪነት ስለኾነ፡ በዚህ ሥልጣናቸው እየሠሩ፡ በተጨማሪ፡ ያወጧቸው ሕጎችና ደንቦች፥ የሰጧቸው ትእዛዞችና ውሳኔዎች፥ የፈቀዷቸውም መመሪያዎችና የገንዘብ ድልድሎች፡ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጇ በሚመራውና እስከሀገረ ስብከት በሚደርሰው፡ በአስፈጻሚው ዘርፍ፡ በትክክለኛ ተግባር ላይ መዋላቸውን በበላይነት መቆጣጠር እንጂ፡ በየሀገረ ስብከታቸው፡ ራሳቸው፡ እንደሥራ አስኪያጆች እየኾኑ፡ በአስፈጻሚነቱ ኃላፊነትና ተግባር ውስጥ ጣልቃ እንዳይገቡ ስለተደረገ፡ አንዳንዶቹ፡ የቆየው ሥልጣናቸው፡ በዚህ መልክ እንደተወሰደባቸው ሲያስተውሉ፡ ቅሬታቸውን፡ ቀስ በቀስ ማሳየት ጀመሩ፡፡

ነገር ግን፡ ይህን የተሻሻለውን የአሠራር ሥርዓት፡ እጅግ አስፈላጊ ያደረገው፡ ሌላ አማራጭ የሌለው፡ ርትዕነቱና መሠረታዊነቱ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ "ጳጳሳቱን፡ ከሚያሳፍርና ከሚያዋርድ ችግር ማዳን ይገባል" የሚለው አስተሳሰብ ጭምር ነበረ፤ ይህንኑም፡ ገና ቀደም ብሎ፡ መመሪያውን ሥርዓት፡ ራሳቸው እንዲያጸድቁት በቀረበላቸው ጊዜ፡ ተረድተው የተስማሙበት መኾናቸውን፡ በየጽሑፍ ኪዳናቸው አረጋግጠውታል፤ ስለዚህ፡ አሁን ለማስረዳት እምብዛም አዳጋች አልኾነም፤ "ጳጳሳቱን፡ ከሚያሳፍርና ከሚያዋርድ ችግር ማዳን" ማለት፡ በሥራ አስፈጻሚነቱ ኃላፊነት ውስጥ ጣልቃ መግባት፡ በአስተዳደር ጉድለትና በአፈጻጸም ጥፋት፡ ተጠያቂነትን ማስከተሉ ስለማይቀር፡ በአስተዳደር ጉባዔ ላይ መቅረብንና፡ ወይም በፍርድ ቤት፡ በወንጀለኛነት መከሰስን፥ ከዚያም፡ በየመልኩ የሚወሰኑትን ቅጣቶች ከመቀበል የሚያደርስ መኾኑ ታውቆ የተሰጠ ውሳኔ ነበር፡፡

በሌላው ወገን ደግሞ፡ የሰበካ ጉባዔ መቋቋም፡ ቤተ ሕዝቡን አጠናክሮ፡ የየቤተ መቅደሱን አስተዳደርና አገልግሎት በሥርዓት እንዲካኼድ ያደረገ በመኾኑ፡ በተለይም፡ በገቢና በወጪ ረገድ፡ የማያፈናፍን ኾኖ በመገኘቱ፡ ከቁስ ገበዝ አንሥቶ፡ በአለቃው አልፎ፡ እስከ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳሳት ድረስ፡ በምሥጢር የተዘረጋውን የጥቅም ሰንሰለት፡ በዚህ አሠራር ስለተበጣጠሰ፡ በእኔ ላይ የነበረውና ዛሬ ድረስ ያለው ቅሬታና ተቃውሞ፡ እንዲህ በቀላሉ የሚገመት እንዳልኾነ፡ ለእኔም ይሰማኛል፤ ሌላውም፡ አስተዋይ ተመልካች አይስተውም፡፡

ታዲያ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት እንደሌለ በተቆጠረበት፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ጳጳሳቱም፡ "የገበያ ግርግር፡ ለሌባ ያመቸዋል!" እንደተባለው ኹሉ፡ በዚህ አጋጣሚና አመቺ ወቅት በመጠቀም፥ በኢትዮጵያ፡ እንኳንስ እውን ኾኖ ሊፈጸም ይቅርና፡ "ሊታሰብ እንኳ አይሞከርም" የሚባለውን አሠራር፡ ማለትም፡ "ቤተ ሕዝቡንና ቤተ ምልክናውን፡ ምንም የሚያገባቸው ነገር የለም!" በሚል፡ በማናለብኝነት ድፍረት በመተላለፍ፡ በቤተ ክህነቱ አመራር ውስጥ እየሠሩ ያሉትን፡ ይኸው፡ ኹሉም፡ አዚም እንደያዘው ሰው፡ ዝም ብሎ፡ በገሃድ ይመለከታል፡፡

ይኸውም፡ ራሱን ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን የሚያስገኘውን፡ ቤተ ሕዝቡን፡ ማለትም የሰበካ ጉባዔውን፡ በይፋ በማግለል፡ ጳጳሳቱ፡ ብቻቸውን፡ ራሳቸው፡ የቤተ ክህነቱ ሕግ አውጪዎችና ወሳኞች፥ ራሳቸው፡ ሕግ ፈጻሚዎችና አስከባሪዎች፥ ራሳቸው፡ ሕግ ተርጓሚዎችና ፈራጆች ኾነው፡ ሦስቱንም፡ የሥልጣኑን ዘርፎች፡ ለእየራሳቸው ተከፋፍለው ይዘው፡ ከሕግና ከሥርዓት ውጪ፡ በይፋ የሚፈጽሙት ተግባር ነው። ይኹን እንጂ፡ ይህን የመሰለው ሕገ ወጥ አሠራር፡ ከላይ እንደተጠቀሰው፡ ነገ፡ አስተዳደርን ኾነ ፍርድ ቤትን በሚመለከት፡ በቤተ ሕዝቡ አማካይነት፡ ሊቀርብባቸው የሚችል፡ በኃላፊነት የመጠየቅ ጠንቅ መኖሩን፡ ያስተዋሉት አይመስልም።

ይህ የጳጳሳቱ ድርጊት፡ ጥንት ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ፡ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያን ሥርዓተ መንግሥት ብቻ ሳይኾን፡ በአዲስ ኪዳን፡ በሐዋርያት የተሠራውን ሥርዓት ሳይቀር በይፋ ያፈረሰ መኾኑን ለማረጋገጥ፡ ሌላ ማስረጃ አያስፈልግም፤ በመላው ዓለም ሕዝብ ዘንድ፡ ዘወትር ከሚነበበው፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ክፍል፡ እንዲህ የሚለውን ቃል መጥቀስ ይበቃል።

*"በዚህም ወራት፡ ቤተ ሕዝቡ እየበዙ ሲኼዱ፡ ከአረማውያን አገር መጥተው የነበሩት ምእመናን፡ በይሁዳ ኖረው በነበሩት ምእመናን ላይ አንጐራጐሩባቸው፤ በየቀኑ፡ በተሠራው አገልግሎት፡ መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና። አሥራ ኹለቱም ደቀ መዛሙርት፡ መላውን ቤተ ሕዝቡን ጠርተው፡ እንዲህ አሏቸው፦ 'የእግዚአብሔርን ቃል ማገልገልን ትተን፡ በሥጋዊ አስተዳደር እንጠመድ ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም። ወንድሞች ሆይ! በመልካም የተመሰከረላቸውን፥ መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች፡ ከእናንተ ምረጡ! ለዚህ ጉዳይ እንሾማቸዋለን! እኛ ግን፡ ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን!፡ ይህም ቃል፡ ቤተ ሕዝቡን ኹሉ ደስ አሰኛቸው። ሃይማኖትና መንፈስ ቅዱስ የሞላበትን ሰው፡ እስጢፋኖስን" እና ከእርሱ በቀር፡ ሌሎች ስድስት ሰዎችን፡ "መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሟቸው፤ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው። የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ፥ በኢየሩሳሌምም፡ የቤተ ሕዝቡ ቁጥር እጅግ* [፲፮] *እየበዛ ኼደ! ከካህናትም፡ ብዙዎች፡ ለሃይማኖት የታዘዙ ኾኑ!"*

በዚህ ኹኔታ፡ ከውጭና ከውስጥ ይካሄድብኝ የነበረውን ተቃውሞ፡ በትእግሥት እየተቀበልሁ በማሳለፍ፡ ትኵረቴን በሥራዬ ላይ ብቻ አድርጌ፡ ተልእኮዬን በመቀጠሌ፡ ታላቁ ግዳጄ አድርጌ እቆጥረው የነበረውን የሰበካ ጉባዔን፡ በአዲስ አበባና በመላው የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የማቋቋሙ ተግባር፡ በባለቤቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ቸርነትና በቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ረድዔት፡ ሊከናወን ቻለ!

በዚያን ጊዜ፡ በተለይም ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ከገባ ጀምሮ፡ በቤተ ክህነት አካባቢ ይካኼድ የነበረው ድርጊት ያስገርመኝ ነበር። ይኸውም፡ እኔ፡ በዚሁ ግዳጄ፡ በየክፍለ ሀገሩ ስዋትት ሰንብቼ፡ ወደአዲስ አበባ ስመለስ፡ በመሥሪያ ቤቴ ይጠብቀኝ የነበረው ኹኔታ ነበር። በዘመኑ፡ የቤተ ክህነት ተጠሪ፡ በእጩጌ ቴዎፍሎስ መሪነትና በጳጳሳቱ ተባባሪነት፡ የቤተ ክህነቱ ሠራተኛ፡ በእኔ ላይ በአድማ እንዲነሣሣ ለማድረግ፡ ይካኼድ የነበረው ጥረት ነበር። ነገር ግን፡ በቤተ ክህነት ልፈጽመው ከእግዚአብሔር የተፈቀደልኝን ተልእኮ ከግብ ከማድረሴ በፊት፡ ምንም ማድረግ የማይቻላቸው ኾኖ፡ ባለቤቱ ያቀደው እንደተከናወነ፡ ወደሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነት፡ በሹመት ተዛወርኩ።

በጃንሆይ ቃል: "ይቆይ!" የተባለውም: ያ የቤተ ክህነት ጉዳይ: እንደገና ሳይነሣ: የመለኮታዊው የቁጣ ቀን ደረሰና: ኹሉም ወደየተዘጋጀለት ጽዋ እየተጠራ ኼደ!

በዚያ ከባድ የእንጥልጥል ጊዜ: ከሥራዬ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ምክንያት: ከደረሱት ኹኔታዎች መካከል: ዛሬ ድረስ የሚያስበረግገኝና የሚያሠቅቀኝ: አንድ ነገር ቢኖር: እኔ በተካፈልሁበት: በዚያ ታላቅ ጉባዔ ላይ: ያን የመሰለ: ቤተ ክህነትን በከፍተኛ መጠን የሚጎዳ ውሳኔ ሊሰጥ ዝግጅት በተደረገባት: በዚያች ቀውጢ ወቅት: "የቤተ ክህነት ዓበይት ተጠሪዎች ናቸው" ተብለው የሚገመቱት ጳጳሳት: ለምን ዝም እንዳሉ ሊገባኝ ያለመቻሉና "እኔስ ባልገኝ ኖሮ!" የሚለው ሐሳባዊ ጥያቄ ነው::

እነርሱ: ማለትም: ጳጳሳቱ: ያ ውሳኔ: ቤተ ክህነትን በብርቱ እንደሚጎዳት፥ በዚህም ነገር: በቤተ ሕዝቡ ዘንድ ብቻ ሳይኾን: በይበልጥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስጠይቃቸው መኾኑን እያወቁ: ዝም ያሉት: በሌላ ምክንያት ሳይኾን: የየራስ ጥቅማቸው፥ ክብራቸውና ዓላማቸው እንዳይነካባቸው ፈርተው: ወይም ብዙ የግል ውለታ ያደረጉላቸውን አጼ ኃይለ ሥላሴን ላለማሳዘን ብለው እንደኾነ ጥርጥር የለውም:: ከእነርሱ ዝምታ የተነሣ: እኔ: በመንፈስ ተገድጄ ከመናገሬ በፊት: እያንዳንዳቸው: ወይም ኹሉም: ብድግ ብለው: "ይህ: የውሳኔ አሳብ የሚጸድቅ ከኾነ: ሥራችንን እየለቀቅን ወደየገዳማችን እንመለሳለን" ይላሉ ብዬ ጠብቄ ነበር:: ይኼ ቀርቶ: እንዲያውም: "በዚህ ልጅ ንግግር ምክንያት: ጃንሆይን አሳዘንናቸው!" በሚል ቅሬታ እንደተሰናበቱ: በኹኔታቸው ይታወቅ ነበር::

## ኢትዮጵያ: 'የዛሬውን እጨጌ: አባ ጳውሎስንና መሰሎቻቸውን ስትፋረድ!

የጳጳሳትን ኹኔታ የታዘብኩት: ከላይ: በየቦታው በተወሱት: በእነዚያ ጊዜያት ብቻ አልነበረም! የእሥራትና የግዞት ዘመኔን ከፈጸምሁ በኋላ: የስደቱን መስቀል: በእግዚአብሔር ፈቃድ፥ በራሴም ፍላጎት: ቀደም ብዬ: በኬንያ፥ ቀጥሎ: በአሜሪካ ተቀብዬ: ባሳለፍኩት ዘመን ነበር እንጂ::

## ገለልተኛው አገልግሎት: የተጀመረበት ሥራ::

ከደርግ እሥር ተፈትቼ በነበርሁበት ጊዜ: ከቤተ ክህነቱም ኾነ ከቤተ ምልክናው: ራሱን ነጻ አድርጎ: በገለልተኛ አቋም ይካኼድ የነበረውን፥ በመቋቋሙም ተባባሪ የነበረውን: የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለምን ትምህርት ቤት: በበላይነት እንዳስተዳድርና እንድመራ: የትምህርት ቤቱ ባለአደራ ምርፋቅ ጠይቆኝ: ለኹለት ዓመታት ካገለገልሁ በኋላ: የእኔ አያያዝና አሠራር: ከጊዜው የአገዛዝ ፍልስፍና ጋር የማይጣጣም ኾኖ በመገኘቱ: በትምህርት ቤቱ ላይ: ችግር መፈጠር ጀመረ:: እንዲህ በኾነበት ሰዓት: ሊቪንግ ባይብል ኢንተርናሽናል (Living Bible International) ከሚባልና የአፍሪቃ መሥሪያ ቤቱ: በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ከኾነ: ከአንድ: ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ድርጅት: ባልጠበቅሁት ኹኔታ: የሥራ ዕድል ቀረበልኝ! ሥራውም: ቅዱሳት መጻሕፍትን: ከእንግሊዝኛ ወደ ኢትዮጵያኛ መተርጐምና የድርጅቱን የአካባቢ ክፍል አህጉር አስተዳደር: በሥራ አስኪያጂነት መምራት ነበር::

እኔም፡ "ለትርጉሙ መሠረትና መደበኛ የማደርገው ምስክር፡ በቋንቋ በኩል፡ 'ግእዙን'፥ በሃይማኖት በኩል ደግሞ፡ 'ተዋህዶን' ነውና፡ ሥራውን የምቀበለው፡ በዚህ ከተስማማን ነው" ብዬ ያቀረብኩትን አሳብ፡ ይኸው ድርጅት ስለተቀበለኝ፡ እንዲህ ከኾነ፡ በዚህ መልክ ተዘጋጅተው የሚወጡት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ሳንባቢው ሕዝበ ክርስቲያን እንደሚጠቅሙ በማመን፡ ውሉን አጽንቼ፡ የትርጉሙን ሥራ ጀመርኩ።

እኔ የሠራሁትን ትርጉም፡ በሃይማኖቱ በኩል፡ በዚያን ጊዜ፡ በሲኖዶስ ውግዘት ከቤተ ክህነት ተባርረው የነበሩት አቡን ገብርኤል፥ በሥነ ጽሑፉ ረገድ ደግሞ፡ አቶ መንግሥቱ ለማ፥ በአጠቃላይና በኹለንተናው አቀራረቡም ረገድ፡ አለቃ ሴም ከበደ ተመልክተው፡ ትክክለኛነቱን እንዲያረጋግጡ፡ በአማካሪነት ደረጃ ተቀጥረው ሠርተዋል። በቅድሚያም፡ የመዝሙራቱ ሥራ፡ በከፍተኛ፡ የሃይማኖት ትግል ከተጠናቀቀ በኋላ፡ በቀሩት መጻሕፍት ላይ ሊቀጥል የሚገባው የትርጉሙ ሥራ፡ በስምምነታችን መሠረት ሳይኾን፡ ከዚያ ውጪ፡ ጎጂ በኾነ ስልት እንዲካኼድ፡ በድርጅቱ በኩል የመፈለግ አዝማሚያ ስላየሁ፡ ሥራውን ለመልቀቅ፡ ካንድም፡ ኹለት ጊዜያት፡ የውሳኔ አሳብ ማቅረቤን፥ ዳሩ ግን፡ ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው የሥራው ተባባሪዎች በሽምግልና እየገቡ፡ ለጊዜው፡ ሥራው፡ እንደስምምነታችን ሊቀጥል ቢችልም፡ በመጨረሻ፡ ድርጅቱ፡ በዚያ አዝማሚያው ሊገፋበት መወሰኑን ስረዳ፡ ሥራውን በፈቃዱ መልቀቄን፡ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ያሉት፡ እኒሁ የሥራ ተባባሪዎች ያውቁታል።

ታዲያ! በአዳዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ውስጥ፡ "ኢትዮጵያ" የሚለውን ስም፡ "ሱዳን" በሚል ቃል እየለወጡ የተኩትን፡ የኢትዮጵያን ጠላቶች የተንኰል ግብር፡ የእኔ ተቃዋሚዎች፡ ከዚያ፡ ከእኔ የትርጉም ሥራ ጋር እያስታከኩና እኔ እንደፈጸምሁት እያስመሰሉ፥ እንዲሁም፡ በዚህ ሥራ ምክንያት፡ ብዙ ገንዘብ እንዳገኘሁ እያደረጉ፡ የሐሰት መርዛቸውን ሲረጩ፡ እኒያ የትርጉሙ ሥራ ተባባሪዎቼ፥ በተለይም፡ በዛሬው ሲኖዶስ ውስጥ አባል የኾኑት፡ አባ ገብርኤል ምን ብለው አስረድተው ይኾን? ወይስ ዝም አሉ? ወይስ የሐሜቱ ተባባሪ ኾኑ?

በዓለማውያን ዘንድ፡ በገንዘብና በሌላው፡ ሥጋዊ ጥቅም ረገድ፡ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውን፡ ያን የመሰለ፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ፡ የላቀ ክብር የሚያስጠውን፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥራ፡ በፈቃዴ የለቀቅሁት፥ ደግሞም፡ በስደት ዓለም ሣለሁ፡ ሌሎች ተመሳሳይ ዕድሎች፡ እየቀረቡልኝ፡ "አልቀበልም!" ያልኩት፡ ዛሬ በተራ፡ ከያግጣጫውና ከተለያዩ ወገኖች፡ ልዩ ልዩ የፈተና ፆሮችን የምቀበልባትን፡ ይህችኑ፡ ኢትዮጵያዊት ሃይማኖታችንን፡ ለድርድር ላለማቅረብና አሳልፌ ላለመስጠት ስል መኾኑን፡ እዚህ ላይ ማውሳቱ አግባብ ኾኖ አግኝቼዋለሁ።

## በስደቱ መግቢያ፡ በናይሮቢ የተፈጸመ ግዳጅ።

በዚያ የትርጉም ሥራዬ ምክንያት፡ ወደናይሮቢ በኼድሁበት፡ በመጀመሪያው ጉብኝቴ ጊዜ፡ በሰንበተ እሑድ፡ ወደቤተ ክርስቲያን ለመኼድ ብጠይቅ፡ በዚያ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለመኖሩን፥ ከዚህም የተነሣ፡ በዚያ አገር፡ በስደትና በሥራ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ችግር ያለባቸው መኾኑን፡ አቶ መኰሪያ ወርቁ ከተባሉት ኢትዮጵያዊ ምእመን ተረዳሁ።

በዚህም ነገር፡ እጅግ አዘንሁ፤ ያዘንሁትም፡ ደርግ ሥልጣን ከመያዙ በፊት፡ እኔ ራሴ፡ በቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያሃጅነቴ፡ ወደናይሮቢ ኼጄ፡ ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ እንዲውል፡ በቤተ ክህነት ስም፡ በመኻል ከተማ፡ ከኬንያ መንግሥት ተረክቤው የነበረ ቦታ መኖሩን ስለማውቅ ነው፤ በዚያን ጊዜ የነበረኝ እምነት፡ በዚያ ቦታ፡ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶበት፡ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ብዬ ነበረ። ነገር ግን፡ እንደእምነቴ ሳይኾን ቀረ! ኋላ ጉዳዩን ስከታተል፡ ቦታው፡ ምንም ዓይነት ሕንፃ ሳይሠራበት፡ ለረዥም ጊዜ በመቆየቱና ከቤተ ክህነትም አንዳችም ተከታታይ ባለመኖሩ፡ እንደጠፍ ተቆጥሮ፡ ለሌላ አገልግሎት መዋሉን ከኬንያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ተረዳሁ። ከዚህ በኋላ፡ ጉዳዩን ማንቀሳቀስ ጀምሬ፡ ስማቸው ከላይ በተጠቀሰው፡ በአቶ መኰሪያ አማካይነት፡ በናይሮቢ የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን ምእመናንን፡ በሰበካ ጉባዔ አዋጅ ተሰባስበው እንዲቋቋሙ አደረግሁ፤ ቀጥሎ፡ የሚመለከታቸውን የኹለቱን መንግሥታት፡ ማለትም፡ ናይሮቢ የሚገኘውን የኢትዮጵያን እንደራሴና የኬንያን ባለሥልጣኖች አገናኘቼ፡ በተሰጠ ፈቃድ፥ አዲስ አበባ የሚገኙትንም የቤተ ክህነት መሪዎች አነቃቅቼ፡ ከውጭ በተገኘ የቤተ ክህነት የገንዘብ እርዳታ፡ በቤተ መቅደስነት ሊያገለግል የሚችል ሕንፃ ያለበት ሌላ ሰፊ ቦታ፡ በናይሮቢ ከተማ ሊገዛ ተቻለ፤ በዘመኑ የቤተ ክህነቱ እጨጌ በነበሩት፡ በአባ ተክለ ሃይማኖት፡ ፈቃድና ትእዛዝ፡ አባ ኤልያስ የተባሉትን ጳጳስና ሌሎችን ካህናት፡ ወደናይሮቢ አንጉዘን፡ እነሆ፡ በታሪክ፡ ቀዳሚት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፡ በናይሮቢ ከተማ ተቋቁማ አገልግሎት መስጠት ጀመረች።

በስደት ዘመኔ፡ በተልእኮዬ ምክንያት፡ አልፎ አልፎ፡ ወደናይሮቢ የምኼድባቸው ጊዜያት ስለነበሩ፥ እኔም፡ በእነዚያ ጊዜያት፡ በዚችው ቤተ ክርስቲያን እየተገኘሁ አገለግል ስለነበረ፡ እኒያ፡ አባ ኤልያስ የተባሉት ጳጳስ፡ ምን እንደተጠናወታቸው አላውቅም፡ በእኔ ላይ የነበራቸው አስተያየትና አቀባበል፡ ፈጽሞ ተለዋውጦ አየሁ። በዚህ ጊዜ፡ "ምን ነክቷቸው ይኾን?" እያልኩ ሳወጣ ሳወርድ፡ የኋላ ኋላ፡ በዘመኑ እጨጌ፡ በአባ መርቆርዮስ ሰብሳቢነት፡ እኒሁ ጳጳስና መሰሎቻቸው የተሰባሰቡበት የደርግ ሲኖዶስ፡ በእኔ ላይ፡ "ሰጠ!" የተባለውንና በገጽ ፻፺፩ ላይ የሠፈረውን ምሥጢራዊ ውሳኔ ሳገኘው፡ ያ ኹኔታቸው ለምን እንደነበረ ተረዳሁት፤ ስለዚህ፡ ያ፡ የቀደመ ድርጊታቸው፡ የማያስደንቀኝ ኾነ!

## የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ውጥን።

ለዚያ የስደት ኑሮ ምክንያት የኾነኝ ጉዳይ፡ ከእሥር ቤት ከወጣሁ በኋላ፡ ተሠማርቼበት የነበረው፡ የድርሰትና የትርጉም ሥራዬ አነቃቅቶኝ የተነሣሣሁበት፡ ከተልእኮዬና ከሙያዬ ጋር የተያያዘው ተግባር ነበር፤ ይኸውም፡ በተለይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉም የሚመለከተው ነው።

አጼ ኃይለ ሥላሴ ባስተረጎሙት የመጨረሻው መጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ውስጥ፡ አባሎች ኾነው ካገለገሉት ተርጓሚዎች መካከል፡ ፀረ ማርያም ፈረንጆች፡ በቀንደኛነት ተካፋዮች ኾነው ስለነበሩ፥ እነርሱም፡ ለትርጉሙ ሥራ፡ መሠረትና መነሻ፥ ምስክርም ያደረጉት፡ ግእዙን ሳይኾን፡ ዕብራይስጡንና ግሪክኛውን በመኾኑ፡ ኢትዮጵያኛው (ዐማርኛው) ትርጉም፡ "የተስተካከለና የተሟላ ነው" ብሎ ለመቀበል አስቸጋሪ ኾኗል።

ይህ ችግር የተፈጠረው፡ አባ ቴዎፍሎስና እርሳቸውን የመሰሉት፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት፡ ስለትርጉሙ መዛባት፡ የተሰማቸውን ቅሬታ፡ ቀደም ብለው፡ በአባልነታቸው፡ እዚያው፡ እተርጓሚው ጉባዔ ላይ፡ እስከመጨረሻው ተከራክረው በማሳመን ፈንታ፥ ወይም ተቃውሟቸውን በይፋ አሳውቀው፡ የትርጉሙ ሥራ እንዲታገድ በማድረግ ፈንታ፡ አኩርፈው፡ ከጉባዔው በመቅረታቸው መኾኑ ስለተነገረ፡ ይኸው አድራጎት፡ ለባዕዳኑ ዓላማ መሳካት፡ እንደተባበሩና አስተዋጽዖ እንዳደረጉ አስቆጥሩዋቸዋል።

ይህን ከመሰለው፡ የተቃወሰ አቋም በመነሣት፡ "ዛሬ፡ በዕብራይስጡም ኾነ በጽርኡ (በግሪኩ) ተጽፈው የተገኙት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በየዘመናቱና በልዩ ልዩ ምክንያት የተቈነጻጸሉ ስለኾኑ፡ እምነት ሊጣልባቸው አይቻልም፤ ስለዚህ፡ በዕብራይስጡና በጽርኡ፡ የበላይ ምስክርነት፡ የግእዙ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ግእዛቸው፡ እየተስተካከለ፡ ወደኢትዮጵያኛው (ዐማርኛው) ሊተረጐሙ አይገባም፤ ይልቅስ፡ በቅድሚያነቱም ኾነ፡ በጥንታዊነቱ፥ እንዲሁም፡ በጥንቃቄ ተጠብቆ በመኖሩ፡ እርሱ፡ ግእዝ፡ ለእነርሱ ምስክር ሊኾን ይገባዋል" በሚል እምነት፡ የግእዙን ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ያለሌላ ምስክር፡ በቀጥታ ወደእንግሊዝኛ በመተርጎም፡ ለእንግሊዝኛ ተናጋሪው የዓለም ሕዝብ ለማቅረብ እንዲያስችል፡ አንድ የሥራ ውጥን አዘጋጀሁ።

ያንንም የሥራ ውጥን፡ በግብር ላይ ለማዋል፡ አግባብ ካላቸው፥ ተቋማት ጋር በመወያየትና በዚያን ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ላሉት የቤተ ክህነት ኃላፊዎች በማሳወቅ፡ "ቫንደርቢልት" በተባለ መካነ አእምሮ (Vanderbilt University) አማካይነት፡ ዕቅዱ፡ ፎርድ ፋውንዴሽን (Ford Foundation) ለተባለው ደጋፊ ድርጅት እንዲቀርብ ተደርጎ፡ ተቀባይነትን ስላገኘ፡ ለውጥኑ ሥራ በተመደበው የገንዘብ ወጪ፡ የመጀመሪያው ጥናት፡ በእግዚአብሔር ቸርነት ሊከናወን ቻለ! ተከታዩና ኹለተኛው የውጥኑ ዕቅድ ግን፡ ለመልካሙ ፍሬ እንዳይበቃ፡ በተለመደው የውስጥና የውጭ ፀረ ኢትዮጵያ ወገኖች ደባ፡ በበቀለው እሾህ፡ ታንቆ እንዲቀር ተደረገ፤ ስለዚህም ደባቸው፡ ለኹሉ፡ ዋጋውን የሚከፍለው፡ የእርሻው ባለቤት፡ በሚገለጽበት፡ በመከሩ ጊዜ፡ ክፉ አድራጊዎቹ መልስ ይሰጡበታል።

## መሥዋዕትነት የተከፈለበት ሽምግልና።

በአንድ ወገን፡ ያን፡ የቅዱሳት መጻሕፍት የትርጉም ውጥን ተግባር እያከናወንሁ ሣለሁ፡ በሌላ ወገን ደግሞ፡ በስደትና በልዩ ልዩ ምክንያት፡ በዚያ በአሜሪካ አገር የሚኖረው፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኅብረተሰብ የኾኑት፡ ምእመናኑም፥ ካህናቱም፥ ራሳቸው ጳጳሳቱም ሳይቀሩ፡ እርስ በርሳቸው፡ ተለያይተውና ተከፋፍለው፡ መናቆራቸውን ስለተረዳሁ፥ ራሴም አይቼ ስላረጋገጥሁ፡ "በኹሉም መካከል፡ ሰላም ተመልሶ፡ ያስደቱ ጽዋ፡ ከእያንዳንዳችን የሚፈልገውን ተልእኮ በአግባቡ ለመፈጸም የሚያስችለንን፡ የዕርቁን መንገድ፡ እግዚአብሔር ቢረዳኝ፥ እኔም ግዳጄ ነውና፥ እነርሱም፡ ከእኔ የበለጠ የሚያስቡበት ጉዳያቸው ነውና፡ እስቲ በጳጳሳቱ ልጀምረው!" ብዬ፡ በቅድሚያ፡ በዚያን ጊዜ፥ በዚያው አገር ላይ ይኖሩ የነበሩትን፡ ሦስት ጳጳሳት፡ በስልክ ብቻ ሳይኾን፡ ወደየሚኖሩበትም ክፍለ አገር፡ በራሴ ወጪ እየኼድሁና እየተዘዋወርሁ፡ ቃል ለቃል በመገናኘት፡ በሰፊውና በተደጋጋሚ አነጋገርኳቸው።

እኒያ ሦስት ጳጳሳት፡ እኔ፡ በደርግ እሥር ቤት ሣለሁ፡ ኹሉም፡ በደርግ ዘመን የተሾሙ ናቸው። እነርሱም፡ በጵጵስና ስማቸው፡-

የመጀመሪያው፡ አባ ጳውሎስ ይባላሉ። እርሳቸውም፡ ካጳጳሷቸው እጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር፡ በየካቲት ወር፥ ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. በደርግ ታሥረው፡ ከ፰ ዓመታት በኋላ፡ በደርግ ተፈትተውና በቤተ ክህነት፡ የኃላፊነት ሥራ ተሰጥቷቸው፡ በዚያ ሲሠሩ ቆይተው፡ ጀምረውት የነበሩትን ትምህርት ለማጠናቀቅ እንዲፈቀድላቸው አመልክተው፡ በደርግ ፈቃድ፡ ወደሚያውቁት፡ አሜሪካ፡ እንደገና ኼደው፡ በከፍተኛ ተማሪ ደረጃ፡ በምቾት ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ፡ ደርግ ሲወገድና ዛሬ ያለው መንግሥት ሲቋቋም፡ መጥተው፡ ለእጨጌነት የበቁ ናቸው።

ኹለተኛው፡ አባ ይስሓቅ ይባላሉ። እርሳቸውም፡ በደርግ ዘመን፡ በአሜሪካ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ተጠሪ የነበሩና የደርግ አገዛዝ ሲወድቅ፡ ዕድል ፊንታቸው፡ ከእርሱ ጋር በመኾኑ፡ "እውቅና የምሰጠው፡ ለደርጉ እጨጌ፡ ለአባ መርቆሬዎስ እንጂ፡ ላዲሱ ተተኪ እጨጌ፡ ለአባ ጳውሎስ አይደለም" በማለት፡ ኃላፊነታቸውን ለቅቀው፡ ዛሬ፡ በዚያው፡ በአሜሪካ፡ በስደተኛነት የሚኖሩ ናቸው።

ሦስተኛው፡ አባ ማትያስ ይባላሉ። እርሳቸውም፡ በኢየሩሳሌም፡ የኢትዮጵያ ጳጳስ ኾነው፡ ደርግን ሲያገለግሉ ቆይተው፡ ኋላ ደግሞ፡ ከዚያ "ከዳሁ!" ብለው፡ በስደተኛነት፡ አሜሪካ እየኖሩ፡ ለስለላ ድርጅቶችና በውጭ ላሉ የደርግ ተቃዋሚዎች፡ አፈ ቀላጤ በመኾን አገልግለው፡ የደርግ አገዛዝ ተውግዶ፡ ያሁኑ አገዛዝ ሲተካ፡ ወደኢትዮጵያ ተመልሰው፡ ካባ ጳውሎስ ጋር ከታረቁ በኋላ፡ በአሜሪካ የቤተ ክህነት ተጠሪ ኾነው የተመደቡ፥ በመጨረሻም፡ ከሾሟቸው ከእጨጌ ጳውሎስ ጋር መግባባት ሳይኖራቸው የሚገኙ ናቸው።

ገና፡ ቀደም ብሎ፡ በ፲፱፻፶፬-፶፰ ዓ. ም. አካባቢ፡ በዘመኑ፡ የእጨጌው እንደራሴና የውጭው ጉዳይ ኃላፊ በነበሩት፡ በአባ ቴዎፍሎስ አማካይነት፡ አቡን ጳውሎስ፡ አባ ገብረ መድኅን፥ አቡን ይስሓቅ ደግሞ፡ አባ ላዕከ ማርያም ይባሉ በነበረበት ጊዜ፡ ለትምህርትና ለአገልግሎት፡ አሁን ወዳሉበት፡ ወደምዕራቡ ክፍለ ዓለም ተልከው ስለነበረ፥ እኔም፡ በዚያን ዘመን፡ በቤተ ክህነቱ፡ የትምህርት ክፍል ኃላፊ ስለነበርሁ፡ የኋላ ኋላም፡ ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ሣለሁ፡ በሥራ ምክንያት፡ ወደዚያ የመኼድ ዕድል ሲያጋጥመኝ፡ እጠይቃቸው ስለነበረ፡ ኹለቱንም፡ በግንባር አውቃቸዋለሁ፤ አባ ማትያስን ግን፡ በደርግ ጊዜ፡ እኔ እሥር ቤት እያለሁ፡ ወደአዲስ አበባ እስኪመጡ ድረስ፡ በቆዩበት፡ በአንድ የትግራይ ገዳም ውስጥ ሣሉ ጀምረው፡ እኔን፡ በዝና ያውቁኝ እንደነበረ፡ ኋላ፡ ራሳቸው ከነገሩኝ በቀር፡ እኔ፡ በግል አላውቃቸውም።

እነዚህን ጳጳሳት፡ እያንዳንዳቸውን፡ በግል፡ አሉበት ድረስ እየተጓዝሁና እየኼድሁ ሳነጋግራቸው፡ በተለይ፡ በማውቃቸው፡ በኹለቱ ላይ የነበረኝ እምነት፡ ምንም ዓይነት እንከን ያልነበረበት ነበር። ለእኔ፡ እያንዳንዳቸው፡ በቃል ኪዳን የክህነት ታማኝነታቸው፥ በምንኵስና ተልእኳቸው፥ በትሕትና አቋማቸውና በአጠቃላይ፡ በማንነታቸው፡ ያው፡ "ቀድሞ የማውቃቸው ናቸው" ብዬ ከማሰብ በቀር፡ እነርሱን የምጠራጠርበት፡ አንዳችም ምክንያት አልነበረኝም። እንዴት ብዬ ልጠራጠራቸው!?

## ሰብአዊ ማንነት ሲለዋወጥ።

በእኔ ዘንድ፡ እንኳንስ የእነርሱን፡ የማንንም ጨዋ ኢትዮጵያዊ፡ ወይም ክርስቲያን፡ ያን የማውቀውን ማንነቱን፡ ከሃይማኖት በቀር፡ ጊዜ÷ ሹመት÷ ማዕርግ÷ ጥቅም÷ የኑሮ ደረጃና ኹኔታ÷ ወይም ዓላማ÷ ሊላውም ኹሉ፡ ምክንያት ኾኖ፡ በምንም መንገድ፡ "ያን ማንነቱን፡ ይለውጠዋል" ብዬ አላስብም። ምክንያቱም፡ አንድ በሚያደርገን "የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታችንና በእርሱ ላይ በተመሠረተው ኢትዮጵያዊነታችን"፡ እነርሱም÷ እኔም፡ አንድ ነንና! ለምሳሌ፡ የዛሬው እጨጌ ጳውሎስ፡ ለእኔ፡ ያው የማውቃቸው፡ አባ ገብረ መድኅን ናቸው፤ የማዕርግ ዕድገታቸው፡ በእኔ ዘንድ የማውቀውን፡ ያን ማንነታቸውን አይለውጠውም፤ አለዚያማ! ወደዚህ ማዕርግ ከፍ በማለታቸው፡ ያ፡ እኔ የማውቀው ማንነታቸው፡ አሁን በተጐናጸፈው ክብር ምክንያት ተለውጦ፡ ከፍ የሚል ከኾነ፡ ምናልባት፡ ካሉበት ማዕርግ፡ እንደሌሎቹ፡ የሚወርዱ ቢኾን፡ በዚያን ጊዜ ደግሞ፡ በእኔ ዘንድ፡ ቀድሞ የማውቀው ማንነታቸው፡ "አብሮ ይዋረዳል÷ ይለወጣል" ሊባል ነው።

አይደለም! የመከባበሩ መጠንና ዓይነት፡ እንደየማዕርጉ፡ ይለያይ ይኾናል እንጂ፡ ማንነት፡ በምንም መንገድ፡ ከቶ ሊለወጥ አይችልም፤ አይገባምም። ያ ሰው፡ በደካማነቱ፡ ራሱን፡ ወይም ማንነቱን ቢለዋውጥም፡ እኔ፡ የዚያን የማውቀውን ሰው ማንነት አልለውጠውም። እውነተኞች (ጻድቃን)፡ የፈተናንና የመከራን ዘመን የሚፈልጉት፡ ለዚህ እኮ ነው! በዚያ ፈተናቸው፡ ማለትም፡ በነፍስና በመንፈስ በሚቀበሉት መከራ÷ ወይም፡ በዚያ መከራቸው፡ ማለትም፡ በሥጋቸው አካል በሚደርስባቸው ሥቃይ፡ በመጀመሪያ፡ የራስን ማንነትና ዓቅም÷ ቀጥሎ፡ የሌላውን ሰው፡ ማለትም፡ ለምሳሌ፡ የቤተሰብን÷ የተወላጅን÷ የዘመድን÷ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ጓደኛን÷ ወዳጅንና አማካሪ መምህረ ንስሓን ማንነትና ጽናት÷ በመጨረሻም፡ "ይቅር ይበለኝ!" የራሱን የእግዚአብሔርን ማንነትና ታማኝነት፡ ሳይቀር፡ ለይቶ ለማወቅና ለማረጋገጥ የሚያስችላቸው በመኾኑ ነው። በአሁኑ ዘመን፡ ብዙዎች ሰዎች፡ በይበልጥም፡ ኢትዮጵያውያን፡ ለዚህ ዕድል ተጋልጠው እንደሚታዩት ማለት ነው!

ታዲያ! እነዚህን ጳጳሳት፡ ያውም በስደት ዓለም እያለን፡ እንዴት ልጠራጠራቸው!? በተለይም፡ በደርግ እሥር ቤት ቆይተው የተፈቱትን፡ አባ ጳውሎስን፡ እንዴት አድርጌ፡ ልጠራጠራቸው!? እነርሱ፡ በእኔ ዘንድ፡ የነበራቸው መታመን፡ ለእግዚአብሔር መላእክት ከምሰጠው ደረጃ የተቃረበ እንደነበረ፡ አሁን ልሸሽገው አልችልም። ምክንያቱም፡ የእግዚአብሔርን እንተወውና! እኔ እንኳ ባቅሜ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" ከሚለኝ፡ ከአንድ ክርስቲያናዊ ምእመን የምጠብቀው፡ "ኢትዮጵያዊ ምእመን ነኝ" ስላለኝ ብቻ፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ ሊኖር የሚገባውን፡ እውነተኛነትና ታማኝነት ነው። ስለዚህ፡ እርሱን እንኳ፡ ልጠራጠረው ያዳግተኛል። እነርሱንማ፡ ከክርስቲያንነቱና ከሥልጣነ ክህነቱ በላይ፡ ምንኵስናን÷ በመጨረሻም፡ ጵጵስናን ያህል ማዕርግ የተቀበሉትን፡ እንዴት፡ የመላእክትን ያህል አላምናቸውም!?

ኹላችንንም፡ በተዋህዶ ሃይማኖታችን፡ ፍጹም አንድ የሚያደርገንን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንንማ፡ ፈጽሜ ከተያቄና ከጥርጣሬ ውስጥ አላስገባሁትም፤ ምክንያቱም፡ በተለይ፡ በእኔ በኩል፡ ስለእነርሱ፡ ከነበረኝ ግምትና በእነርሱም በኩል ከነበራቸው፡ ከዚያ አቋማቸው የተነሣ፡ በዓላማም፥ በተግባርም፡ "ፍጹም አንድ ነን" ብዬ አምኜበት ነበራ!

በዚህ እምነትና መንፈስ ኾኜ ነበር፡ ወደእነርሱ የኼድሁት! በልቤ ያለውንም፡ አንድ ሳላስቀር፡ ወይም ሳልሸሽግ፡ ለእግዚአብሔር እንደምነግር፡ ያነጋገርኳቸው! በጽሑፍ ያሠፈርኩትንም የሰጠኋቸው! ጉዳዩ፡ ኹላችንም፡ ለእግዚአብሔር፡ ቃል ኪዳን የገባንበት የሃይማኖታችን፥ የአገራችንና የወገናችን ጉዳይ ስለኾነ፡ እንዴት አድርጌ፡ ከእነርሱ የምሸሽገው ነገር ይኖራል!?

የግንኙነቴ ዓላማ፡ አንድ ብቻ ነበር፤ እርሱም፡ ከላይ እንደገለጽኩት፡ "በአገር ውስጥ ያሉትን፥ በዓለሙ ኹሉ የተበተኑትንም ወገኖቻችንን በመርዳት፥ በደርግ አማካይነት፡ በአገራችን የሰፈነውን፡ እግዚአብሔር አልባ የአገዛዝ ሥርዓት (Communismን ኮሚዩኒዝምን)፡ ለመቋቋም እንችል ዘንድ፡ ወደውጭ ለመውጣት ዕድሉን ያገኘን ኹላችን፡ በእግዚአብሔር ሰላም እንሰባሰብ! በያለንበትም፡ በፍቅር ኾነን፡ ተገቢና አስፈላጊ የኾነውን ተግባራችንንና ተልእኳችንን እንፈጽም! ለዚህም፡ መሠረቱ፡ የእናንተ መስማማት ነውና፡ እኔ አሁን፡ በግል ሥራዬ ምክንያት፡ እዚህ አገር ከተገኘሁ፡ ፈቃዳችሁ ኾኖ፡ በእኔ አማካይነት አንድ ጊዜ ተገናኝታችሁ በመወያየት፡ በቅድሚያ፡ በመካከላችሁ ያለውን አለመግባባትና ቅሬታ አስወግዱ! ከዚያ ቀጥሎ፡ በካህናቱና በምእመናኑ መካከል ለተፈጠረው ችግር መፍትሔውን መፈለግ ቀላል ይኾናል" በማለት ነበር።

እንዲህ አስብና አምን፥ እናገርም የነበርሁት፡ ለካ፡ እኔ ብቻ ነበርሁ! እኔ፡ ያን ያህል ስደክም፡ አሳቤን የመቀበል አዝማሚያ እያሳዩኝ፥ የተለያየም ምክንያት እያቀረቡልኝ ይሸነግሉኝ ነበር እንጂ፡ ግልጽ የኾነና የተቀረጠ ምላሽ አይሰጡኝም ነበር። በዚህ አካኼድ ያደረግሁት ጥረት፡ እንኳንስ፡ ወደቀጣዩ የዕርቅ ደረጃ፡ መሸጋገርን ሊያስከትል ይቅርና፡ የእነርሱን፡ የሦስቱን ጳጳሳት ግንኙነት እንኳን ሊያስገኝ ሳይችል ቀረ!

## ከአሜሪካኑ ነዋሪዎች ጳጳሳት የተመለሰ፡ ያልተጠበቀ ውለታ።

ሦስቱን ጳጳሳት ለማስታረቅ፡ እኔ፡ ወዲያ ወዲህ እያልኩ በምባክንበት ጊዜ፡ እነርሱ ደግሞ፡ በእኔ ላይ ያካኼዱት የነበረው ድርጊት፡ እንኳንስ ለእኔ፡ ጥቃቱ ለደረሰብኝ ይቅርና፡ ለማንም ሰሚ፡ ለማመን፡ እጅግ ያዳግታል። እኔ የማላውቀው፥ እነርሱና እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቁት፡ ያ እውነተኛ ማንነታቸው፡ በእኔ ዘንድ እየተገለጸ መታወቅ የጀመረው፡ በዚያን ጊዜ ነበር። ጥቂት ቆይቶ፥ እንዲያውም "ይግረምህ!" ብለው፡ በተለይ አባ ይስሐቅና አባ ማትያስ፡ በእኔ ላይ፡ በሥውር ሲያካኺዱ የነበረውን፡ ሐሳዊ የስም ማጥፋት ዘመቻ፡ ገሃድ አደረጉት።

ይህም፡ በፈቃዳቸው መንነው፡ ማለትም፡ "ዓለሙን ንቀን ትተነዋል" ሳሉ፡ መነኰሳትና ጳጳሳት፡ ምናቸውም ባልኾነው፡ በሥልጣንና በገንዘብ፡ እርስ በርሳቸው እየተካሰሱ፡ በዓለማውያን ባዕዳን፡ የአሜሪካ ፍርድ ቤቶች በመጓተት፡ በአገሬው ሕዝብ ዘንድ፡ መሣቂያ+ መሣለቂያ በኾኑባቸው ጊዜያት፡ የደረሰ ኹነታ ነው፡፡

በዚያን ጊዜ፡ በእኔ በኩል፡ "እንግዴህ፡ እኔን እምቢ ካሉ፡ ምን አደርጋለሁ?" ብዬ፡ በዚህ ምክንያት፡ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይታጎልና ምእመናኑ እንዳይበተኑ በማሰብ፡ ለምሳሌ፡ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ከተማ፡ በአንድ ዕለተ እሑድ፡ እስከሦስት አብያተ ክርስቲያን ድረስ፡ በየተለያዩ ሰዓቶች እየተዘዋወርኩ ሳገለግል ሣለሁ፡ በማናለብኝነት ዕብሪት፡ በእኔ ላይ በፈጸሟቸው አሳዛኝ አድራጎቶቻቸው አማካይነት፡ ያ፡ ባዕድ ተልእኳቸው ተከሠተ! ይህን እንግዳ ኹኔታቸውንም ለማስረዳት፡ ለእያንዳንዳቸው፡ አንድ አንድ ምሳሌን ብቻ በመጥቀስ እወሰናለሁ፡፡

በመጀመሪያ፡ አባ ይስሐቅ፡ ጉዳዩ፡ እርሳቸውንና ሌሎቹን እንጂ፡ ክህነታዊ አገልግሎትን በማበርከት ላይ ያለሁትን እኔን፡ በምንም የማይመለከተኝ በመኾኑ፡ እንድቀርብ እንኳ ሳያስፈልግ፡ ዳኞች በዘጉት፡ በቤተ ክርስቲያናቸው የእርስ በርስ ክርክር፡ እኔን ጭምር፡ በፍርድ ቤት እንድከሰስ ማድረጋቸው፡ አንዱ አሳዛኝ ድርጊታቸው ነው፤ ከዚህ ጋር የተያያዘው ደግሞ፡ ደርግ፡ የሞት ፍርድ ወስኖብኝ የነበርሁትን እኔን፡ እግዚአብሔር፡ ከሰባት ዓመታት እሥራት በኋላ፡ በቸርነቱ ስላተረፈኝ፡ "ለስደተኛ ወገኔ፡ በተልእኮዬ፡ የሚገባኝን አገልግሎት ላበርክት!" ብዬ፡ ዘወትር እሑድ በየአብያተ ክርስቲያኑ መገኘቴ ያላስደሰታቸው አባ ማትያስ፡ እንደግላቸው ወደቆጠሩት ቤተ ክርስቲያን መምጣቴን እንዳቆም የሚያስገድዱኝ መስሏቸው፡ ምሥጢሩን፡ የትኛው የስለላ ድርጅት እንደነገራቸው፡ ራሳቸው ይናዘዙት፡ እኔን "የደርግ ሰላይ ነው!" በማለት፡ ስሜን በሐሰት ማጥፋታቸው ሌላው አሳዛኝ ድርጊታቸው ነው፡፡ በዚህም ረገድ፡ ስለተፈጸመው በደልና ግፍ፡ እውነቱንና ሐሰቱን ለይቶ የሚያውቀው እግዚአብሔር፡ በጊዜው የሚሰጠውን ዳኝነቱን እጠብቃለሁ፡፡

በአንድ ወገን፡ እኔ፡ በስደት አገር በነበርኩበት፡ በአሜሪካ አገር፡ በዚያ ይኖሩ ከነበሩት፡ ከእኒህ ሦስት ጳጳሳት፡ ይህን የመሰለ በደል እየተፈጸመብኝ ሣለ፡ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በዚያኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ምድር ከሚኖሩት መሰሎቻቸው ጳጳሳት፡ ይካኼድብኝ የነበረውን የማጥቃት ዘመቻ፡ እዚህ ላይ፡ ባጭር ማውሳቱ፡ አግባብ ኾኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

## ከደርጉ "ሲኖዶስ" የተላለፈ፡ "ምሥጢራዊ ውለታ"፡፡

"እግዚአብሔር የለም" በሚል የ"communism የኮሚዩኒዝም" ሥርዓት ሥር፡ ተጨቁና የነበረችውን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊት ሃይማኖታችንን፡ ከደርግ አገዛዝና ከእርሱ ጋር ተባባሪ ኾኖ ከነበረው "ሲኖዶስ" ከሚባለው፡ የቤተ ክህነት አመራር ጉባዔ ጠብቆ ለማዳንና ደግፎ ለማቆየት በማሰብ፡ በአሜሪካ፡ በተለይም፡ በዋሽንግተን፡ ዲ. ሲ. አካባቢ፡ ነዋሪዎች ከነበሩ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ጋር፡ "የኢትዮጵያ ቅዱስ ኪዳን ቅርስ ተቋም" በሚል ስያሜ፡ አንድ ያገልግሎት ድርጅት አቋቁመን እሠራ ነበር፡፡

ቮይስ ኦፍ አሜሪካ (Voice of America) በተባለው: በአሜሪካ ድምፅ መለፈፊያ ጣቢያ: አልፎ አልፎ: እየተጋበዝሁ: አስተላልፈው በነበረው ትምህርታዊ መልእክትና በተለይም: ጾመ ነነዌን: "'ጾመ ኢትዮጵያ' እያልን ልንጾማት ይገባናል" በማለት: በሰጠሁት ማሳሰቢያ ምክንያት: ያንን አገልግሎት: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስታውሰው ሲኾን፥ በዚያ ተቋም አማካይነት የምሠራውንም ሁሉ: ቤተ ክህነት እንዲያውቅ አደርግ ስለነበር: አገልግሎቴ: ከዚያ የጳጳሳት ጉባኤም የተሠወረ አልነበረም።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት: ሃይማኖቷና ምግባርዋ፥ ሥርዓቷም: ማናቸውም መሥዋዕትነት ተከፍሎ: በጥንቃቄ እንዲጠበቅ በማድረግ ረገድ ካልኾነ በቀር: ያን የመሰለ አገልግሎት የምሰጥበት ተቋም: ስያሜው እንደሚያመለክተው: በሌላ ነገር: ከኢትዮጵያ "ኦርቶዶክስ" ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያገናኝ ምንም ነገር አለመኖሩ: በገሃድ ይታወቅ ነበር። ታዲያ፥ ነገሩ ኹሉ እንዲህ ኾኖ ሣለ: በደርግ ጊዜ የነበረውና ከእርሱ ጋር አባሪ ተባባሪ በመኾኑ: አብሮ የተወገደው፥ ባሁኑ ጊዜም: ያልቀረለትን: የስደት ጽዋ: በግዱ የተቀበለው: ያ: እነአባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ: ጳጳስ ከኾኑ በኋላ: በቀንደኛነት ይመሩት የነበረው: "ሲኖዶስ" የተባለው የጳጳሳት ጉባዔ: ለምን: በእኔ ላይ: አንድ ውሳኔን ወስኖ: እኔ ሳላውቅ: በምሥጢር አስተላለፈ? ውሳኔው: "ኢትዮጵያ ትቅደም!" በሚል የደርግ መፈክር የተላለፈውም: በዚያን ጊዜ: በውጭ አገር: የደርግ ተከታዮች ለነበሩት ጳጳሳትና በግልባጭ ደግሞ: ለኢትዮጵያ መንግሥት: ጠቅላይ ምሉክ (Ministre ሚኒስትር) ጽሕፈት ቤት፥ ላገር ውስጥ ጉዳይ ምልክና (Ministere ሚኒስቴር)፥ ለውጭ ጉዳይ ምልክናና ለባህል ምልክና ነበር።

የጳጳሳቱ ጉባዔ: ለውሳኔው: መንሥኤ ያደረገው: ከላይ ከጠቀስኩት: ከግእዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ከተያያዘውና በመላው ዓለም እዘዋወርበት ከነበረው፥ ዓለም አቀፍ ይዞታም ከነበረው አገልግሎቴ የተነሣ: ከደርግ መምሪያ ተሰጥቶት፥ ወይም ሲኖዶሱ: ለደርግ ያለውን ታማኝነት ለማሳየት ሲል: አሳቡን ከራሱ አንቅቶ፥ ወይም: ጳጳሳቱ: በእኔ አገልግሎት ላይ በተነሣሣባቸው: የቅንዓትና የጥላቻ ስሜት፥ ወይም የተቋሙን ያገልግሎት እንቅስቃሴ ለመቃወም፥ ባጠቃላይ: ከእነዚህ: በአንዳቸው ወይም በኹሉም ምክንያት ካልኾነ በቀር: በሌላ: በምን ሊኾን ይችላል?

ደርግ: በፀረ ሃይማኖታዊነቱና በክርስቶስ ተቃዋሚነቱ: የነበረውን የክህደት ሰይጣናዊ አቋም: ያፈራረሰችበትን፥ እርሱንና ግብረ አበሮቹን ጳጳሳት: ከመንበራቸው: ገልብጣ ያስወገደችውን: የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ረቂቅ ኃይል: በምሥጢር ያገዱ፥ በዚህም ድርጊታቸው: የጌታቸውን የደርግንና የራሳቸውን የሥልጣን ዘመን: ያረዘሙ መስሏቸው: ጳጳሳቱ: ያስተላለፉት: ያ ውሳኔያቸው: "ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ: ከሀገራቸው የወጡት: በግል ሥራቸው: በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አማካይነት ሲኾን: ያንን ሥራቸውን ትተው: ቤተ ክርስቲያን ሳትልካቸው: የላከቻቸው በመምሰል: የሚያካኺዱት ሥራ: ቤተ ክርስቲያንን አሳዝኗታል። ስለዚህ: ማንኛውም መንፈሳዊ ድርጅት: የእኚህን ቄስ መልእክት: 'ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተላከ ነው' ብሎ እንዳይቀበል!" የሚል ነበር።

የዚህን ምሥጢራዊ የሲኖዶስ ውሳኔ ቅጂ፡ ውሳኔው፡ ተላልፎለት ከደረሰውና በዚያ፡ በባዕድ አገር ከሚኖር፡ ከአንድ ተቈርቋሪ ኢትዮጵያዊ አግኝቼ፡ ለውሳኔው አሰጣጥ መነሻ የኾኑት ምክንያቶች፡ ፈጽሞ እውነትነት የሌላቸው፡ የሐሰት አባት ከተባለው፡ ከዲያብሎስ የመነጩ መኾናቸውን፡ በእግዚአብሔር እውነት በማብራራት፡ "ውሳኔውን ሰጠ" ለተባለው፡ ለራሱ፡ ለጳጳሳቱ ጉባዔና እርሱ፡ ግልባጭ ሳደረገላቸው ክፍሎች ኹሉ፡ ተገቢው የማስተካከያ መልስ እንዲደርሳቸው አደረግሁ።

እንግዴህ፡ የእኔ ተቃዋሚዎች፡ እኒህ፡ የአሜሪካ ነዋሪዎቹ ብቻ ሳይኾኑ፡ የደርግ የክህደት ሥርዓት ተባባሪ በመኾናቸው፡ ተልእኮዬ ያስበረገጋቸው፡ እነዚያ፡ በኢትዮጵያ፡ የሲኖዶስ አባሎች የነበሩት ጳጳሳት ጭምር እንደነበሩ፡ ይህ፡ የተጠቀሰው ውሳኔ፡ በሚበቃ ያስረዳል።

## የጳጳሳቱ "እውነተኛ ማንነት"፡ እየተጋለጠ ሲወጣ!

በመጨረሻ፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ የተረፈውን ሰው ማንነት፡ በተራው፡ ለይቶ የሚያስታውቀው፡ ያ፡ ቀን ደርሶ፡ ደርግ፡ ሲባረርና የዛሬው አገዛዝ፡ ሥልጣን ሲይዝ፡ በአገር ውስጥም፥ በውጭ አገርም የነበሩት፡ የእያንዳንዳቸው ጳጳሳት፡ እውነተኛ ማንነትና ምንነት፡ በይበልጥ፡ በትክክል ታወቀ! በተለይም፡ በአሜሪካ የቆዩት፡ የእኒህ፡ የሦስቱ ጳጳሳት፡ የእያንዳንዳቸው ምንነትና ማንነት ብቻ ሳይኾን፡ ምን ዓላማ እንደነበራቸውም፡ ራሳቸው፡ በአገራችንም፥ በአሜሪካም፡ እየተዘዋወሩ በገሃድ በፈጸሙት ተውኔታዊ ትርኢት ተገለጠ! እኔ አላወቅሁም፥ አልጠረጠርሁም እንጂ፡ ለካ እነርሱ፡ በምትሐታዊ አስተሳሰባቸው፡ እኔነቴን ለውጠው፡ በሌላ መልክ ገምተውኝ ኖርዋል! እኔ፡ ለእነርሱ፡ እንዲያ ግልጽ ኾኜ፡ ገሃድ የነበረውን፡ አሳቤንና ዓላማዬን፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፡ በጽሑፍ ጭምር ሳቀርብላቸው፡ እነርሱ ግን፡ ይህን እውነተኛ ማንነታቸውንና ዓላማቸውን፡ ከእኔ ደብቀው፡ በእኔ ላይ፡ ያን ኹሉ ሸንገላና ተንኰል፡ ከበስተኋላዬ፡ በንቀትና በፌዝ ይፈጽሙብኝ የነበረው፡ ያለምክንያት እንዳልነበረ፡ በየራሳቸው ሥራ ተከሠተ! እኔም ተረዳሁት።

ያን ኹሉ ኹኔታቸውንና ድርጊታቸውን፡ ወደኋላ መለስ ብዬ ሳስታውሰው፡ "ለካ፡ ሦስቱም ጳጳሳት፡ ዘረኞች ኖረዋልና! ማለትም፡ እንደእኔ፡ በኢትዮጵያዊነታቸው ሳይኾን፡ በትግሬነታቸው ብቻ የሚያምኑ ኖረዋልና!" ብዬ በማሰብ፡ በእኔ ዘንድ ታውቆ የኖረው ማንነታቸው፡ በእነርሱ ዘንድ፡ ፈጽሞ ተለውጦ አገኘሁት። አዎን! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በድንግል እናቱና በራሱ ሰውነት፡ መሥርቶ ባጸናው፥ እኔም፡ ያገሬን ሰዎች ብቻ ሳይኾን፡ በዓለሙ ውስጥ የሚኖሩትን፡ የሰውን የዘር ዓይነቶች ኹሉ፡ በአንድ ዓይን እንዳያቸው ባበቃኝ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ለማምነው፡ ለእኔ፡ ለኢትዮጵያዊው አገልጋይ፡ እነርሱ እውነተኛ ማንነታቸውንና ዓላማቸውን፡ ለእኔ፡ ቀደም አድርገው መግለጥ ያልፈለጉት፡ በዚሁ ምክንያት መኾኑን አረጋገጥሁ።

## ዘረኛነት ወይም ጐሠኛነት ባለበት፡ ኢትዮጵያዊነት አይኖርም!

እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የሴምንና የካምን፥ የያፌትንም ነገዶች ባዋሃደው በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ ሰውነትና ኹመት ተገልጾ፡ ሰው የኾነበት፡ አንዱ ዋናው ምክንያት፡ መላውን የሰውን ዘር፡ ማለትም፡ የዓለምን ሕዝብ ኹሉ፡ በሥጋና በዘር ሳይቀር፡ አንድ ለማድረግ መኾኑን፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!" በሚለውና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ በየቦታው፡ በሚበቃ ተብራርቷል።

ይኹን እንጂ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ፡ በተለይም በቤተ ምልክናው ውስጥ፡ ያለይሉኝታና ያለኃፍረት፡ በይፋ ሲደረግ እንደሚታየው፥ ለእያንዳንዱ ብሔረ ሰብ፡ "የዕጣ ድልድል (quota ኰታ) ተመድቧል" በሚልም ተጨማሪ ምክንያት፡ እንደየክልሉ ስያሜ፡ አፋር፥ ትግሬ፥ ኦሮሞ፥ ...ወዘተ. እየተባለ፥ ዐማራም እንደጐሣ ተቆጥሮ፡ ዘርና ቋንቋ፡ ኹለንተናዊና ወሳኝ መሥፈሪያ ኾኖ፡ እነሆ፡ በሕገ መንግሥት ሳይቀር እንዲጸና ተደርጎ፡ ሲሠራበት ይታያል።

ይህን በሚመለከት የተሰጠው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ በፍጹም አክብሮትና ጥንቃቄ ሊጠበቅባት በሚገባው በቤተ ክህነትና በኃላፊዎቿ ዘንድ፡ ይኸው መለኮታዊ ሥርዓት ሲፈርስና ሃይማኖታዊ አቋሙም ሲፋለስ ማየት ደግሞ፡ እጅግ ያሳዝናል። "እግዚአብሔር፡ ራሱ ሰው ኾኖ፡ በነገድና በቋንቋ የተለያየውን የሰውን ዘር፡ በዚያ ሰውነቱ፡ አንድ ስላደረገው፡ ይህን አንድነት፡ ራሱ ሰው፡ ወይም ሌላው አይለየው!" የሚለውን ቃል በመተላለፍ፡ በዘርና በጐሣ መለያየትን መፍጠር፡ እጅግ ከባድ ኃጢአት ነው። እንኳንስ፡ በዚህ፡ በመለኮታዊው ምሥጢር በተፈጸመው አንድነት ይቅርና፡ በሃይማኖት አንድ በኾኑ ወገኖች መካከል እንኳ፡ በሰዎች ስም ምክንያት፡ መለያየት እንዳይኖር፡ እንዲህ የሚለው፡ የሐዋርያው ቃል ያስረዳል። *"እያንዳንዳችሁ፡ 'እኔ፡ የጳውሎስ ነኝ!' 'እኔ፡ የአጵሎስ ነኝ!' እኔ ግን፡ የኬፋ ነኝ!' 'እኔስ፡ የክርስቶስ ነኝ!' ትላላችሁ። ክርስቶስ፡ ተከፍሏልን? ጳውሎስስ፡ ስለእናንተ ተሰቀለን?"* ይህም የሐዋርያው ቃል፡ *"አንተ አባት ሆይ፡ በእኔ እንዳለህ፥ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ፡ በእኛ አንድ ይኾኑ*[፲፩] *ዘንድ እለምናለሁ!"* ባለው በኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ ለፍጹምነት በቅቷል።

ታዲያ! ዛሬ፡ የቤተ ክህነቱን፡ የእጨጌ ሥልጣን የያዙት አባ ጳውሎስ፡ አድርገውት እንደታዩት፡ ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው፡ "የለም! ትግሬ ነኝ!" ካሉ፥ አመራራቸውንም፡ በዚሁ እምነታቸው ላይ መሥርተው፡ ተግባራቸውን የሚፈጽሙ ከኾነ፥ እንዲሁም፡ ትናንት፡ ከእርሳቸው በፊት የነበሩት፡ አባ መርቆሬዎስ፡ በገሃድ አድርገውት እንዳለፉት፡ "ጎንደሬዎች ነን እንጂ፡ ኢትዮጵያውያን አይደለንም!" ከሚሉት ግብረ አበሮቻቸው ጋር፡ ይህንኑ በመሰለ መልክ፡ የጐሠኛነት መስመርን ተከትለው፡ የሠሩ ከኾነ፥ ከዚያም በስተያ፡ የእጨጌውን መንበር ይዘው የነበሩት፡ አባ ቴዎፍሎስ፡ እንዲሁ፡ ከኢትዮጵያዊነታቸው ይልቅ፡ በጎጃሜነታቸው አምነው፡ ሠርተው ያለፉ ከኾነ፥ ደግሞ፡ ከኹሉም ቀደም ብለው፡ የነበሩት፡ እጨጌ ባስልዮስ፡ ኢትዮጵያዊነትን በማጣጣልና ለሸዌነት ቅድሚያን በመስጠት፡ አመራራቸውን አካኺደው ከኾነ፡ በእርግጥ፡ በአሁኑ ትውልድ ስም፡ ትልቁ፡ የክህደት፥ የዓመፅና የአመንዝራነት በደልና ኃጢአት ተፈጽሟል ማለት ነው።

እንዲህማ ከኾነ: ኢትዮጵያን: ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያዊ/ትን: ኢትዮጵያዊ/ት የሚያሰኘው: የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት "ከንቱ ኾነ!" ወይም "የለም!" ሊባል ነው! በአጠቃላይም: የኢትዮጵያዊነትን ምሥጢር በሚመለከት: እግዚአብሔር: በመጀመሪያውና በመካከለኛው፥ ይልቁንም: አማናዊውና ዘለዓለማዊው በኾነው: በመጨረሻው መልከ ጼዴቅ: በኢየሱስ ክርስቶስ የወጠነው፥ ያካኼደውና የፈጸመው መለኮታዊ ዕቅዱ "ፍሬ አልባ ኾኖ ቀረ!" ሊያሰኝ ነው! ነገር ግን: አይደለም! ይህንንማ አይበለው! ይህ: እንኳንስ በድርጊት ሊፈጸም ቀርቶ: በአሳብ እንኳ ታስቦ ከኾነ: በቅድሚያ: ከቃል ኪዳን እናታችን ጋር ታርቀን፥ ከዚያ በኋላ: በእርሷ አማላጅነት: የቃል ኪዳን አምላካችንን ኢየሱስ ክርስቶስን: በታላቅ ንስሐ: ይቅርታ ጠይቀን: ስርየትን ልናገኝበት የሚገባን ግዳጅ ይኾናል:: ስለዚህ: ይህ ሰይጣናዊ እምነትና ግብር: በዚህ መንገድ: በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣንና ኃይል: ፈጽሞ ሊወገድ ይገባዋል::

በመነኰሴውና በእጨጌው አባ ጳውሎስ ሰውነት ውስጥ ሠርጾ የሚሠራውና በአካላዊ ኹለንተናቸው ላይ አይሉ የሚታየው መንፈስ: የኢትዮጵያዊነት ሳይኾን: የትግሬነት መኾኑ በቀላሉ ይታወቃል:: ይህን እውነት ካረጋገጡት: የኋላ ድርጊቶቻቸው መካከል: ለማስረጃ ያህል: እስቲ: አንዳንዶቹን: በምሳሌነት ልጥቀስ!

-የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ: ደርግን አሳድዶ እንዲያስወጡ: ጽናቱንና ኃይሉን ሰጥቶ: መሣሪያው ያደረጋቸው: የትግሬ ተወላጆች ያቋቋሙት፥ እነርሱም የሚበዙበትና የሚመሩት አንጃ: ሥልጣን በያዘ ጊዜ: አባ ይስሐቅ: የደርግ ተሿሚ በመኾናቸውና ሥልጣናቸው ሊቀጥል እንደማይችል በማወቃቸው: እርሳቸው ብቻ: በዚያው በአሜሪካ ሲቀሩ: በዕቅድና በቀጠሮ እንደተካኼደ በሚያስመስል ዝግጅት: አባ ጳውሎስና አባ ማትያስ: ከአሜሪካ ወደኢትዮጵያ: ባስቸኳይ በርረው መጥተው: በአዲስ አበባ ተገኝተዋል::

፥አባ ጳውሎስ: በኢትዮጵያ: ባንዳንድ አስፈላጊ ቦታዎች እየታዩ: ጥቂት ቀይታን ካደረጉ በኋላ: ወደነበሩበት አሜሪካ ተመልሰው: በየሥፍራው እየተዘዋወሩና በዚያ ያሉትን: የትግራይን ተወላጆች: በይፋ እያሰባሰቡ: እስከዚያን ጊዜ ድረስ: በእርሳቸው መሪነትና አማካይነት: በቤተ ክርስቲያን ሲሰጥ የነበረው አገልግሎት: በትግርኛ ሳይኾን: በዐማርኛ ቋንቋ: እንዲካኼድ ሲያደርጉ በመቆየታቸው: ተገልጋዩን ሕዝበ ክርስቲያን ይቅርታ ከመጠየቅ ጋር: ለወደፊቱ ግን: ይህ አሠራር ተቀይሮ: አገልግሎቱ: በትግርኛ ብቻ የሚካኼድ መኾኑን አስታውቀው፥ ለትግራይ ተወላጆች የሚኾነውንም: ሌላውን ዝግጅት አከናውነው: ወደአዲስ አበባ ተመለሱ:: በእጨጌነቱም መንበር ላይ ተቀመጡ::

-አባ ጳውሎስንና አባ ማትያስን: እንደሥርዓታችን: በእግዚአብሔር ስም ላቀራርባቸው፥ ላገናኛቸውና ላስታርቃቸው: ያን ያህል ጥረት በማደርግበት ጊዜ: በመካከላቸው ሊኖር ከማይገባው ቅያሜና ጥላቻ የተነሣ: እንኳንስ ተገናኝተው: ዓይን ለዓይን ለመተያየት፥ ተወቃቅሰው ለመታረቅ ይቅርና: በስልክ እንኳ ለመነጋገር: በቁርጥ: "ፈቃደኞች አይደለንም" ያሉኝ ሰዎች: ዛሬ: በአብዛኛው: የትግሬ ተወላጆች በሚገኙበት አንጃ የሚመራው መንግሥት: ሥልጣን መጨበጡን ሲያረጋግጡ: በአዲስ አበባ ተገናኝተው: "ታርቀናል!" ተባባሉ::

-ወዲያው ደግሞ: አባ ጳውሎስ: በእጨጌነቱ መንበር ላይ ሲቀመጡ÷ አባ ማትያስ ደግሞ: በእርሳቸው ተሹመው: ወደፈለጉት የምቾች መኖሪያቸው: ወደአሜሪካ እንዲመለሱ ተደረገ:: ታዲያ! በእነዚህ ጳጳሳት ድርጊት: ለኢትዮጵያ ምእመናንና ለውጭው ዓለም የተላለፈው መልእክት: በሰዎች መካከል: የእግዚአብሔርን ዕርቅ ለመፈጸምና ሰላሙንም ለማስገኘት: ያውም: ለመነኰሳትና ለጳጳሳት: የተለየ ጊዜና ቦታ÷ የሰው ዓይነትና የተመቸ ኹኔታ ያስፈልጋል የሚል: ኢክርስቲያናዊ መኾኑን መገንዘብ የሚያዳግተው ሰው: ከቶ ይኖራልን?

-አባ ጳውሎስ: በእጨጌነት መንበር ላይ እያሉ: በተለይ በደቡቡ: የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ባሉት: “ዐምሐራ” በተባለው: የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብና አብያተ ክርስቲያን ላይ: በሌሎች ተቃራኒ ሃይማኖታውያን ብሔረሰቦች ታላቅ እልቂት ሲፈጸምባቸው÷ እንዲሁም: ሥፍር ቁጥር የሌላቸው የመኻል አገር ኢትዮጵያውያን: ከኤርትራና በቀሩት የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር ከሚገኙት መሥሪያ ቤቶች እየተባረሩ: መድረሻ አጥተው ሲሠቃዩ÷ በየአደባባዩም ወድቀው ሲታዩ: የሰበካ ጉባዔዎች እንዲቋቋሙ ከተደረገባቸው ዓላማዎች መካከል: አንዱ: ይህን የመሰለውን ችግር ለመቋቋም መኾኑ እየታወቀ: በእነዚያ አሳዛኝ ኹኔታዎችና ጊዜያት: ስለችግረኞቹ በመናገርና እርዳታን በማበርከት የሚገባቸውን አልፈጸሙም::

-አባ ጳውሎስን ከሚቃወሙት የሲኖዶስ አባሎች መካከል: በተሽከርካሪ መጓጓዣ አደጋ: የሞት ጽዋቸውን እየተቀበሉ በማለፍ: በየተራ የተወገዱት: ከቀደሙት: ከአባ ጎርጎርዮስ ጀምሮ: እስከእነአባ ዮሴፍ÷ አባ ኤልያስና አባ ያዕቆብ ድረስ ያሉት ሊቃነ ጳጳሳት: ቁጥራቸው: አነስተኛ አለመኾኑ÷ ድርጊቱም በተከታታይነትና በተመሳሳይነት: እየተደጋገመ የቀጠለ ሲኾን: አደጋዎቹ የደረሱባቸውን ምክንያቶች: በትክክል ለማወቅ: ተገቢው ምርመራ አለመካኼዱ÷ ምርመራው ተካኺዶ ከኾነም: ውጤቱ: ለቤተ ሕዝቡ እንዲቀርብ አለመደረጉ: “ሟቾቹና ከአንደኛው አደጋ: በተአምር የተረፉት: እነሊቀ ትጉሃን ዳኛቸው ካሣሁንና እነሊቀ ጉባዔ አበራ በቀለ: ኹሉም: ከዐምሐራው ወገን ብቻ በመኾናቸው ይኾን?” የሚል: ከፍተኛ ጥርጣሬን አስከትሏል::

-ጥር ፩ ቀን÷ ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. የቅዱስ እስጢፋኖስ የዓመት በዓል: በአዲስ አበባ በተከበረበት: በቤተ ክርስቲያኑ ዓውደ ምሕረት ላይ: በታቦቱና በሕዝቡ÷ በአባ ጳውሎስም ፊት: በጥይት ተደብድቦ የፈሰሰው የባሕታዊ ፊቃደ ሥላሴ ደም: ያለው አሳዛኝና አሳሳቢ ኹኔታ ከምን ደረጃ እንደደረሰ: ጮኾ ይናገራል:: ከዚህ ኹሉ ጋር: በቤተ ክህነት ውስጥና የእርሷ በኾኑት ዘርፎች: በየመልኩ የሚፈጸመው የሠራተኛ አስተዳደርና የሹማምንት አመዳደብ: ይኸው: የጐሠኝነት አዝማሚያ ይታይበታል::

በእኔ በኩል: እነዚህን ሦስት ጳጳሳት: አያቸው የነበርሁት: ከላይ እንደተገለጸው: በዚያው: ራሳቸው: “ነን” ብለው: ራሳቸውን: በመንፈሳዊው ቃል ኪዳናቸው: ለእግዚአብሔር ባረጋገጡበት÷ በልብስና ቆባቸውም: ለዓለሙ: በይፋ ባሳወቁበት: በዚያው: በምንኵስናቸውና በጵጵስናቸው: “መነኰሳት÷ ጳጳሳት ናቸው” ብዬ እንጂ: እንደዓለማውያን አስመሳዮችና ሥጋውያን ፈሊጠኞች (politicians ፖለቲከኞች) በሰዎች የሥነ መንግሥት አካኼድ÷ ወይም በሹመትና በሥልጣን ፍትወት: “ማንነታቸውን: እንዲህ የሚለዋውጡ ይኾናሉ÷ ከኹሉም በላይ ደግሞ: ለኢየሱስ ክርስቶስ: ተልእኮ ብቻ እንጂ: ለሰዎች ዓላማ: ተገዢዎችና አገልጋዮች ይኾናሉ” ብዬ አልጠረጠርሁም ነበር::

አሁንም፡ መነኩሳት ናቸውና፥ ያውም ለእጨጌነት ሳይቀር የበቁ ጳጳሳት ስለኾኑ፡ “እንዴት ብዬ ልጠርጥራቸው!?”

ለእያንዳንዱ፡ የሚገባውን ዋጋ የሚከፍለው እውነተኛው ዳኛ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ፡ ኹሉም፡ በየራሱ፥ በየምርጫውና በየእምነቱ፡ የወደደውን ለመከተልና ለማድረግ ሥልጣንና መብት፡ ከፈጣሪው ተሰጥቶታልና፡ “ለምን እንዲህ አደረግህ?” ብሎ አንዱ አንዱን ለመጠየቅ፥ ወይም አንዱ በሌላው ለመፍረድ አይቻለውም። ስለዚህ፡ እኔም፡ እነርሱን፡ “ለምን እንዲህ አደረጋችሁ?” ብዬ ልጠይቃቸው፥ ወይም ልፈርድባቸው አልቃጣም። ነገር ግን፡ እኔ፡ እንደዚያ፡ የጋራ ግዴታችንንና ተልእኳችንን በሚመለከት ጉዳይ፡ በእግዚአብሔር ስም ቀርቤአቸው፡ በእርሱ እውነት፡ ራሴን ግልጽ አድርጌ ሳነጋግራቸውና ስማጸናቸው፡ እነርሱም መቼም፡ መነኩሳትም፥ ጳጳሳትም ናቸውና፡ እንደእኔው ግልጽ ኾነው፡ የተደበቀና የታቀደ ዓላማቸውን ሊያስታውቁኝ፥ ወይም፡ በአሳቤ የማይስማሙ፥ እኔንም የማይፈልጉኝ ከኾነ፡ ይህንኑ፡ ያለምንም ይሉኝታና ፍርሃት ሊነግሩኝ ይገባቸው ነበር፤ ይህን ማድረግ ቢሣናቸውም እንኳ፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ “አትድከም!” የምትለዋን ቃል ብቻ አሰምተው፡ ቢያሰናብቱኝ፡ ምን ቸግሩዋቸው ኖርዋል? እኔን ያን ያህል ያደከሙኝ?

ነገር ግን፡ እጅግ ያሳዝናል፥ እንደዚያ ሳይኾን ቀረ!፡ እኔም፡ በዚያን ጊዜ፡ “ለካ፡ የአሁኖቹ አባ ጳውሎስና አባ ይስሐቅ፡ ቀድሞ፡ ከሃይማኖታችንና ከተልእኳችን፥ ከኢትዮጵያዊነታችንም የተነሣ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ አንድ ስለኾንን፡ በማንነታቸውና በምንነታቸው፡ 'አውቃቸዋለሁ!' ብዬ፡ በመተማመን፡ ደፍሬ እናገርላቸው የነበርሁት፡ እኒያ፡ እኔ የማውቃቸው፡ አባ ገብረ መድኅንና አባ ላዕከ ማርያም፡ አይደሉምና!” ብዬ እርሜን አውጥቼ ዝም አልሁ።

## ኢትዮጵያ፡
## ዘመናውያን፡ ባለማዕርግ ምሁራንን
## ስትፋረድ!

የዛሬው እጨጌ፡ አባ ጳውሎስ፡ ከቀሩቱ፡ ከእነዚያ፡ ኹለት ጳጳሳት የሚለያቸውና ለእኔ፡ ማንነታቸውን የለወጡበት፡ ሌላው፡ ተጨማሪ ምክንያት ቢኖር፡ ምናልባትም፡ ከባዕዳኑ፡ ዓለማውያኑ አሜሪካኖች ያገኙት፡ Doctorate የሚለው (ዶክቶሬት፡ “ሊቀ ምሁር” የሚያሰኘው) የትምህርት ማዕርግ ሊኾን ይችላል። እርሳቸው፡ ያን፡ የማውቀውን ማንነታቸውን፡ ለእኔ የለወጡብኝ፡ “እኔ ጳጳሱና ይህን የመሰለ የሊቀ ምሁርነት ማዕርግ ያለኝ እያለሁ፡ ይኼ አንድ ቄስ፡ ወይም የአኮስም ንቡረ እድ፡ እኔንና እኔን የመሰሉትን ማስታረቅና ማሰባሰብ እንዴት ይችላል?” በሚል የንቀት አስተሳሰብ ከኾነ፥ በዚህም አቋም ከሌሎቹ ሥጋውያን ሰዎች የተለዩ ሊኾኑ ያስቸግራቸዋልና፡ በእርግጥ፡ አያስገርመኝም። ምክንያቱም፡ ይህ፡ የባዕዳን የትምህርት ማዕርግ፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ተከትለው ይኖሩና ያገለግሉ እንደነበሩት፡ እንደቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት፡ ለትሕትናና ለአገልግሎት የሚውል ሳይኾን፡ ባለንበት ዘመን፡ ከገንዘብና ከሥልጣን በላይ፡ የሚያስመካ፥ አስከባሪና ጠቃሚ፡ ባለማዕርጉንም፡ ለትዕቢትና ለዕብሪት የዳረገ በመኾኑ፡ እንደእርሳቸው ላለ መንፈሳዊ መሪ፡ አደገኛነቱ አከራካሪ አይደለም።

አዎን! ይኸው የትምህርት ማዕርግ፡ በፈሪሀ እግዚአብሔር ላይ ተመሥርቶ፡ ሙያው፡ ለመልካም አገልግሎት እንዲውል ሲደረግ፡ አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ፡ እጅግ ከፍተኛ መኾኑ አያጠያይቅም። ነገር ግን፡ በተለይ ባሁኑ ጊዜና በአገራችን፡ ይህ ቀርቶ፡ በአብዛኛው፡ ለሥልጣን ማግኛ፥ ለገንዘብ መሰብሰቢያና ለትምክህት ማዳበሪያ እንዲውል በመደረጉ፡ የመሠረታዊ ዓላማውን ፈር የለቀቀ መኾኑ በግልጽ ይታያል። ለዚህም፡ ወደሥጋውያኑና ወደዓለማውያኑ ርቀን ሳንኼድ፡ መንፈሳውያንና ገዳማውያን በተባሉት፡ በመነኰሳቱ፥ ይልቁንም በጳጳሳቱ ዘንድ እየተፈጸመ ያለውን አሳዛኝ ኹኔታ፡ ስለእጨጌው ስለአባ ጳውሎስ፡ በየጊዜው፡ በጦማረ ሕዝብ፡ ከነማስረጃው እየተጋለጠ የሚወጣው ጽሑፍ አረጋግጦታል። ደግሞም፡ የDoctorate (ዶክቶሬቱ) ክብር፡ በባለማዕርጉ ዘንድ ብቻ ሳይኾን፡ በኅብረተሰቡም ዘንድ፡ ከመመለክ ደረጃ የደረሰ በመኾኑ፡ በተለይ በእግዚአብሔር እውነትና ሥርዓት ለሚኖር ግለሰብ፥ ቤተሰብና ኅብረተሰብ፥ ይልቁንም፡ በመለኮታዊው የቃል ኪዳን መንግሥት ለምትመራው ኢትዮጵያ፡ እጅግ አሳሳቢ መኾኑ አይጠረጠርም። ይህም፡ ያለምክንያት አለመኾኑን፡ ከዚህ በታች የተሰጠው ሐተታ፡ በመጠኑ ያስረዳል።

## የሰዎች ትምህርት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንዳይሠለጥን።

በመጀመሪያ ደረጃ፡ የሰዎች ትምህርት ምንድር ነው? ሰብአዊው ትምህርት፡ "እግዚአብሔር፡ ሰውን በአርአያው፥ በመልኩ ፈጠረው" ባሰኘው የነፍስ ባሕርዩ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ ያገኘውን የተፈጥሮ እውቀት፡ ለመገላለጥና ለማዳበር የሚረዳው ዘዴ ነው። ከዚህ አልፎ፡ መለኮታዊዉንና ተፈጥሮአዊዉን እውቀት አጥፍቶ፡ በቦታው፡ የሰዎች የኾነውን፡ ለመተካት ታቅዶ የሚሰጥ ወይም የሚቀበሉት ከኾነ፡ ያን የመሰለው ትምህርት፡ አፍራሽና ጎጂ ገጽታው ተከሠተ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ፡ ለሰይጣናዊ ዓላማ ማራመጃ መሣሪያ ኾኖ ሊያገለግል እንደሚችል፡ መታወቅ አለበት። እስካሁን፡ በሰዎች ሕይወት ደርሶ እንደተረጋገጠውና በዘመናችን፡ ሲካኼድ እንደሚታየው፡ ይህ ኹኔታ መኖሩን፡ ኢትዮጵያውያን በብርቱ ሊጠራጠሩ፥ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ከመኾናቸው የተነሣም፡ በከፍተኛ ንቃት ተነሣሥተው፡ ተገቢውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

እንግዲህ፡ የፈረንጆቹ፥ ወይም የማነኛውም፡ ባዕድ የትምህርት ተቋም፡ በእውነተኛው መስመር ተደክሞበት የሚገኘውን፡ ይህን የDoctorate (ዶክቶሬት) ክብር ሲሰጥ፡ ያ፡ የማዕርጉ ተቀባይ፡ የሚያቀርበው የእውቀት መመዘኛ ጽሑፍ፡ የዚያን የትምህርት ተቋም እምነትና አስተሳሰብ የተከተለ መኾኑን፡ በቅድሚያ ያስተማምናል። ምናልባት፡ በዚያ ጽሑፍ ውስጥ፡ የዚያን፡ የማዕርግ ሰጪውን ተቋም፡ እምነትና አስተሳሰብ፡ የሚቃረን፥ ወይም ተቋሙ የማይቀበለው፡ አንዳች ነገር ቢኖር፡ ያ ነገር፡ እንደገና በራሱ፡ በጽሑፍ አቅራቢው ተስተካክሎ መቅረብ አለበት። በዚህ መልክ የቀረበውን ጽሑፍ፡ ማዕርግ ተቀባዩ አምኖበት፡ በሕይወቱ ሙሉ በሥራ ላይ የሚያውለው መኾኑን፡ በተቋሙ የሊቃውንት ጉባዔ ፊት ቀርቦ፥ በቃሉና በጽሑፍ ኪዳኑ ያረጋግጣል። የማዕርጉ አሰጣጥ፡ በባዕዳኑ በኩል፡ ይህን በመሰለ ዓላማ ተካኺዶ የሚፈጸም መኾኑን፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ በትክክል ተረድቶ፡ የበኩሉን ተገቢ ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል።

Doctorate (ዶክቶሬት) የሚለው የእውቀት ማዕርግ፡ እንደየሙያው ይለያያል። የሕክምና ሲኾን፡ M.D. (Doctor of Medicine ዶክተር ኦፍ ሜዲሲን) ማለትም፡ የሕክምና ሊቀ ምሁር በሚለው ምኅፃረ ቃል፡ ተለይቶ ይታወቃል። ከዚህና ከተመሳሳይ ሙያዎች በቀር፡ ሌላው ኹሉ፡ Doctor of Philosophy (ዶክተር ኦፍ ፊሎዞፊ ወይም፡ በምኅፃረ ቃል PhD. ፒ.ኤች. ዲ.) ማለትም፡ የፍልስፍና ሊቀ ምሁር በሚል አጠራርና አጻጻፍ ይለያል። እንግዴህ፡ ይህን የመሰለውን የእውቀትና የሙያ ማዕርግ ለማቀዳጀት ሥልጣን ያለው፡ የትምህርት ተቋም፡ ለዚያ ግለሰብ፡ ያን ማዕርግ የሚሰጠው፡ ተቋሙ፡ ራሱ፡ የሚከተለውን ፍልስፍና ወይም እምነት፡ ያ ግለሰብ፡ መቀበሉን ሲያረጋግጥ ብቻ ነው። አለዚያ አይሰጠውም፤ እምኖ እስኪቀበልም ድረስ፡ ምክንያት ሰጥቶ ያሰናብተዋል። ይህን የመሰለው ዕድል የገጠማቸው እውነተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መኖራቸውን፡ እዚህ ላይ ማስታወስ ይቻላል።

ከዚህ የተነሣ፡ ይህ ኹኔታ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን አገር የኾነችውን ኢትዮጵያንና የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የኾኑትን፡ ኢትዮጵያውያንን፡ እጅግ ሊያሳስባቸውና ሊያሠጋቸው ይገባል። ምክንያቱም፡ ያለፈውን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት፡ ያን ከመሰለ ታላቅና አሳዛኝ ውድቀት ላይ የጣለው፡ አንደኛው ጠንቅ፡ ይህ በመኾኑ ነው። የዚያን ጊዜውን ኾነ፡ ከዚያ በኋላ በተከታታይ የተተኩትን የሰዎች መንግሥታት፡ በአማካሪነትና በአስፈጻሚነት የሚያካኺዱት ባለሥልጣኖች፡ ይህን የመሰለውን ማዕርግ የያዙት መኾናቸው፡ ለማንም የተሠወረ አይደለም።

እንግዴህ፡ ያ፡ የዚያ ማዕርግ ተቀባይ፡ በኼደበትና በተመደበበት በማናቸውም የኃላፊነት ሥራ፡ በተግባር ላይ የሚያውለው እኮ፡ በአሁኑ ጊዜ፡ ከአምልኮ ደረጃ የደረሰውን፡ ያን፡ ማዕርግ ያገኘበትን እምነት፡ መሠረትና መርኅ አድርጎ እንጂ፡ የአገሩን ወይም የኅብረተሰቡን እምነትና ፍላጎት ተከትሎ ስላይደለ፡ "ይህ ጉዳይ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው!" ያሰኘው፡ ስለዚህ ነው።

## የጃፓኑ ታሪካዊ "እያድርስ" ምሳሌነት።

ለዚህም፡ የጃፓንን ታሪካዊ ድርጊት ማስታወሱ ይጠቅማል። ራሱን የቻለ፡ ጥንታዊ፡ የሃይማኖትና የምግባር ሥርዓትና ባህል ያላት ጃፓን፡ የአውሮጳውያንን ሥልጣኔ ወደአገሩዋ ለማስገባት ፈልጋ፡ ቀላሉና ፈጣኑ መንገድ፡ ልጆቿን ወደአውሮጳ አገሮች ልካ፡ እነርሱ፡ ተምረውና ሠልጥነው እንዲመለሱ ማድረግ መኾኑን በማመን፡ በዚሁ መሠረት ተፈጽሞ፡ የተማሩትና የሠለጠኑት ልጆቿ ወደአገራቸውና ወደወገኖቻቸው ተመለሱ። ነገር ግን፡ ያሳዝናል! እኒያ፡ ወደአገራቸውና ወደወገኖቻቸው የተመለሱት ባለሙያዎች፡ ጃፓኖች ሳይኾኑ፡ ከጃፓናዊነት፡ ወደአውሮጳዊነት የተለወጡ ሰዎች ኾነው ተገኙ! በእምነትና በአስተሳሰብ፥ በባህልና በምግባር፡ ፈጽመው፡ ከኅብረተሰባቸው ጋር ሊጣጣሙ፥ ወይም እነርሱ፡ ራሳቸውን፡ ወደቀድሞው ጃፓናዊነታቸው ሊመልሱ የማይቻላቸው ኾነ! ለእነርሱ ሲባል፡ መላውን የጃፓንን ሕዝብ፡ ባንድ ጊዜ፡ ወደአውሮጳዊነት እንዲለወጥ የመሞከሩ ነገር ደግሞ፡ እንዴት ሊታሰብ ይቻላል? አይቻልም።

ስለዚህ: ለሕዝቡ የነበራቸው ምርጫ አንድ ዘዴ ብቻ ኾኖ ተገኘ! ያም ዘዴ: በአንድ በኩል: አውሮጳውያን ኾነው የተመለሱትን ባለሙያዎች ጃፓናውያንን: ኹሉንም: በአንድ ጊዜ: ፈጽሞ ያስወገደ: እጅግ አሠቃቂ ሲኾን: በሌላ በኩል ደግሞ: ሌሎች ጃፓናውያን ወጣቶች: ከጃፓናውያን ሞግዚቶችና መምህራን ጋር: እንደገና ወደአውሮጳ ተልከው: የተፈለገውን የሥልጣኔ እውቀት ቀሥመው: ጃፓናዊነታቸውን እንደጠበቁ: ወደሀገራቸው እንዲመለሱ ያስቻለ: የብልህነት ውሳኔ ነበር:: ጃፓን: ያው: ጥንታዊቷ ጃፓን ኾና: ህልውናዋን: በዛሬው የሚያስቀና አቋሟ ለመቀጠል የቻለችው: አውሮጳውያን ኾነው በተመለሱት በቀድሞዎቹ ልጆቿ ላይ በተፈጸመው ፍርድ: ምንም እንኳ አሠቃቂ ጭካኔ የታየበት ቢኾን: ቆራጥ የኾነውን: ያን የመሰለ ውሳኔ: በሥራ ላይ በማዋሏ ነው::

በዚህ መሠረት: የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያም: የዚህ ትምህርት ማዕርግ ባለቤቶች የኾኑትን: ወንዶችና ሴቶች ምሁራን ልጆቿን: በሕክምናውም ኾነ በሌላው ሙያ የሠለጠኑትን ጭምር: በሙሉ: በኃላፊነት ቦታ ተቀምጠው ሥልጣን እንዲይዙ ለማድረግ: በቅድሚያ: የትምህርታቸው ማዕርግ ካስገኘላቸው: የባዕዳን እምነትና ፍልስፍና: ራሳቸውን አጽድተውና አስተካክለው: በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር የሚኖሩ፥ ወይም ሊኖሩ የሚፈልጉ መኾናቸውን ማረጋገጥ ያሻል:: እንዲህ ካልኾነ ግን: ከባድ አደጋንና ጽኑ ውድቀትን: በቅዱስ ኪዳኒቱ አገር ላይ የሚያስከትል ስለኾነ: ቤተ ሕዝቡ: በብርቱ ሊያስብበትና ሊጠበብበት ይገባል::

የዚህም ምክንያት ግልጽ ነው:: አዎን! የትምህርቱ ማዕርግ: በይበልጥ: በሥጋዊው ፍልስፍናና እምነት ላይ የተመሠረተ ስለኾነ: ባዕዳኑና የኢትዮጵያ ተፃራሪዎች፥ ዲያብሎስም: ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ: በቀላሉ ለማፈራረስና በመጨረሻም ለመደምሰስ: ፍቱን መሣሪያቸው አድርገው: ሊጠቀሙበትና ሊገለገሉበት ያዘጋጁት፥ ተጠቅመውበትና ተገልግለውበትም: ውጤት ያገኙበት: ረቂቅና ኃይለኛ ዘዴያቸው: በዚሁ የማዕርግ አሰጣጣቸው አማካይነት: በየዕርከኑ የሚያበቃው: ይኸው ትምህርታቸው መኾኑ: በማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ሊታወቅ ያስፈልጋል:: ይህ: Bachelor (ባቸለር) ማለትም: "የትምህርት ሎሌ" ወይም "ደቀ መዝሙር" የሚል ትርጉም ካለው: ከዝቅተኛው ጀምሮ: Doctor (ዶክተር) ማለትም: "ሐኪም" ወይም "ሊቀ ምሁር" እስከሚለው: እስከከፍተኛው ደረጃ ድረስ ደልድለው: ለተማሪው የሚሰጡት ማዕርግ: እርሱ: በእነርሱ ዘንድ: ላለው: ለትምህርቱ ብቻ ሳይኾን: ለታማኝነቱም ጭምር: መለኪያና መያዣ፥ መታወቂያና ማረጋገጫ: ምልክት ኾኖ እንዲያገለግላቸው መኾኑ: ሊዘነጋ አይገባም::

ይኸው ዛሬ: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ደርሶ እንደሚታየው: ባዕዳን: የአንድን አገር ማንነትና ምንነት በቀላሉ ለመለወጥ: በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ የሚያተኩሩት: በዚህ ምክንያትና ለዚህ ዓላማቸው ማከናወኛ እንዲረዳቸው ጭምር አስበውበት መኾኑን: ቤተ ሕዝቡ: በብርቱ ሊገነዘበው ይገባል:: መገንዘብ ብቻ ሳይኾን: በዚህ ረገድ: ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ: የነቃ ትኩረትና ብርቱ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባውም: እዚህ ላይ አበክሬ ማሳሰብ እወድዳለሁ::

## የአባ ጳውሎስ፡ የባዕዳኑ የትምህርት ማዕርግ፡ እንዳያዘናጋ!

በፍጹም አሜሪካዊነቱ ከታወቀው፡ Princeton University ፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ ከተባለው፡ የአሜሪካ ቤተ አእምሮ፡ በፍልስፍና፥ በነገረ መለኮት፣ ወይም በሥነ መንግሥት፡ በየትኛውም ትምህርት ይኹን፡ የDoctorate የዶክቶሬቱን ማዕርግ፡ ያገኙት፡ የዛሬው እጨጌ፡ አባ ጳውሎስም፡ ከሌሎቹ ባለማዕርጎችና ባለሙያዎች ተለይተው ሊታዩ አይቻልም። በዚህ፡ በባዕዳኑ የትምህርት ማዕርጋቸው ምክንያት፡ እንዲያውም፡ የእርሳቸው የእምነትና የአስተሳሰብ አቋም፡ ከኢትዮጵያዊነቱ መሠረት ተነዋውጦና ተለዋውጦ፡ ከኹሉ በባሰ ኹኔታ፡ የከፋ ውጤትን ሊያስከትል ይችላል። ምክንያቱም፡ ይኸው፡ በየድርጊታቸው ተደጋግሞ እንደሚታየው፡ መቼም፡ አይኹንላቸውም እንጂ፡ የቅዱሱ ኪዳን ጥንታዊት ኢትዮጵያን፡ በመንፈሳዊ መሪነታቸውና ሃይማኖታዊ ሥልጣናቸው ሽፋን በመጠቀም፡ ከአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ይልቅ፡ እጅግ በተጠናከረና በተራቀቀ ይዘት፡ ከሥር መሠረቷ መነጋግሎ ለማጥፋት፡ ባዕዳን ጠላቶቻችን፡ ላቀዱትና ለሚያካኼዱት፡ ጽኑ ዘመቻ፡ ከእርሳቸው የተሻለ ፍቱንና ሥውር መሣሪያ ሊያገኙ ስለማይችሉ ነው።

ለዚህ ነገር፡ በርካታ የተለያዩ ማስረጃዎችን ማቅረብ የሚቻል ቢኾንም፡ እውነታውን በቀላሉ ለማረጋገጥ፡ ለዓይነት ያህል፡ አንዳንድ፡ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። ይህም፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ባለመብት በኾነችባቸው ቦታዎችና መሬቶች ላይ፡ ሌሎች ሃይማኖቶች፡ የየራሳቸውን እምነት ለማራመድና የጥቅም አውታራቸውን ለመዘርጋት በሚያስችላቸው መንገድ፡ ግሃድ በኾነ ድፍረት ሳይቀር፡ ሕጋዊ መብቷን እየገፈፉ በሚንሠራፉበት ጊዜ፡ ለአገዛዙ ክፍል በማመልከት፡ መብቷን ማስከበር ሲችሉ፡ "ነገሩ፡ ከመንግሥት ጋር ያጣላናል" በማለት፡ ለአስጠቂው ባለሥልጣንና ለሕግ ተላላፊዎቹ አጋርና ተገን እየኾኑ፡ በሚፈጽሙት ፍቱን መሣሪያነታቸው በግሃድ የሚታየውን፡ ኹሉም ይመለከተዋል።

ለዚህም፡ እኔ ራሴ አረጋግጬ በማውቀው፡ በአዲስ አበባ ከተማ፡ የመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ርስት በኾነው ቦታ ላይ፡ ራሱ፡ ደብሩ፡ በሰበካ ጉባዔው አማካይነት፡ ለአገልግሎቱ አስፈላጊ የኾኑትን ሕንፃዎች ለመሥራት፡ ከረዥም ጊዜ ጀምሮ፡ የተዘጋጀበት መኾኑ እየታወቀ፡ ይኸው ቦታ፡ በግፍ ተወስዶ፡ ሌሎች፡ እንዲሠሩበት መደረጉ፡ በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችል፡ አንዱ ድርጊት ሲኾን፡ ሌላው ደግሞ፡ በደብረ ብርሃን ከተማ የሚገኘው፡ የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ አደባባይ ጉዳይ ነው። ይኸውም፡ ለአያሌ ዘመናት፡ ባለመብቷ፡ ቤተ ክህነት ኾና፡ የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ሲካኼድበት የኖረው ይኸው አደባባይ፡ ለሌሎች ባለገንዘቦች ጥቅም ይውል ዘንድ፡ በአገዛዙ ባለሥልጣኖች በኩል ለሽያጭ መቅረቡ አግባብ አይደለም በማለት፡ ቤተ ሕዝቡ፡ የአቤቱታ ትግል እያደረገ ሣለ፡ የክፍሉ ጳጳስ፡ አባ ኤፍሬም፡ "የፈረምኩት ተገድጄ ነው" በማለት፡ በአደባባዩ ላይ ያለውን፡ የባለቤትነቱን መብት ማዛወራቸውና የቤተ ክህነቱ የጳጳሳት ጉባዔ አባሎች፡ አብዛኞቹ፡ የቤተ ሕዝቡን የተቃውሞ አቤቱታ በሚደግፉበት ጊዜ፡ እጨጌው፡ አባ ጳውሎስና ረዳታቸው፡ አባ ገሪማ፡ "ይህ ጉዳይ፡ ከመንግሥት ጋር ያጣላናል" በማለት የጉባዔውን ውሳኔ መቃወማቸው ነው።

እነሆም: እጨጌውና ጳጳሳቱ: በየመንበሮቻቸው ላይ የተቀመጡት: የቤተ ክህነትን መብት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፥ ግዳጆቿንም: ለመፈጸምና ለማስፈጸም ሳይኾን: ለሌሎች መሣሪያነትና አገልጋይነት መኾኑን: እነዚህ: በምሳሌነት ተጠቅሰው የቀረቡት ኹኔታዎችና ድርጊቶች: በሚበቃ ያመለክታሉ።

## ኢትዮጵያ:
## ጳጳሳቷን ስትፋረድ!

ለጵጵስና እየተመረጡ: በዚያ ደረጃ የሚሾሙት መነኮሳት: ያን መንበር ከተቀመጡበት በኋላ: የሚኾኑት ኹኔታና የሚፈጽሙት ድርጊት ሲታይ: ያ ሹመታቸው: ለምን እንደኾነ: "አላወቁት ይኾን? ወይስ በትክክል አልተረዱት ይኾን?" የሚል ጥያቄን የሚያስከትል ኾኖ ይገኛል፤ አውቀውትና በትክክል ተረድተውትም ከኾነ: ሹመቱን የተቀበሉት: መንፈሳዊ ተልእኳቸውን ለመፈጸም ሳይኾን: ሕይወተ ሥጋቸውን: በተድላና በግብዝነት ለማሳለፍ ዐቅደው እንደተቀበሉት ያስረዳል። ይህን ትችት መነሻ በማድረግ: እዚህ ላይ: ጥቂት ማብራሪያን ልሰጥ እወድዳለሁ።

### የጵጵስና ሹመት ዓላማና ተግባር

መጀመሪያ ነገር: ሲጳጳሱ: ተጠሪነታቸውና ተጠያቂነታቸው፥ ኃላፊነታቸውም: ለማን መኾኑን የሚዘነጉ ይመስላል! ማለትም: በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ: ሊቀ ካህናታቸውና ንጉሠ ነገሥታቸው ለኾነው: ለኢየሱስ ክርስቶስ እና ለቅድስት እናቱ ለድንግል ማርያም ብቻ መኾኑን ይረሱትና: ታዛዥነታቸው: ለዚያ: ደመወዛቸውን በጊዜው ለሚከፍላቸው፥ ወደፊትም ሲያረጁ: የጡረታ አበላቸውን ለሚከፍላቸው፥ መኖርያ ቤትና መጓጓዣ ተሽከርካሪ ለሚሰጣቸው፥ ሌላውንም ሥጋዊ ፍላጎታቸውን ለሚፈጽምላቸው የሰዎች መንግሥት ይኾናል።

የተሾሙት: በኢየሱስ ክርስቶስ ለተገለጸችው: ለእግዚአብሔር እውነት፥ ቀጥሎ: የሥራ ባልደረቦቻቸውን ካህናትን፥ መምህራንንና ሊቃውንቱን ለያዘችው ቤተ ክህነት፥ እንዲሁም: በቤተ ምልክናው ውስጥ: በሥጋዊው የአገልግሎት መስክ ላይ የተሰማሩትን ልኡካን ሠራተኞችን ላቀፈችው ለቤተ ምልክና፥ ይልቁንም: ጠቦቶቻቸውን፥ በጎቻቸውንና መንጎቻቸውን ምዕመናንን ላሰባሰበችው ለቤተ ሕዝቡ፥ ባጠቃላይ: የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ለኢትዮጵያ: በማናቸውም መልክ: ተዋርደውም፥ ተሠቃይተውም ቢኾን: በቀዳሚነት: ለማሰብ፥ ለመናገርና ለመሥራት፥ ከዚያም ቢያልፍ: በሰማዕትነት ሞት ለመሠዋት አይመስላቸውም። አብዛኞዎቹ: የተሾሙት: በሰው ዘንድ ለመከበርና በገንዘብ ለመክበር ብቻ ይመስላቸዋል። በተለይም: ሹመቱን ያገኙት: ተመኝተውትና ፈልገውት ከኾነ: "ሹመቱና በሹመቱ ምክንያት የሚገኘው ሥጋዊ ጥቅም ይቀርብናል" የሚለው ሥጋት የበለጠ ሊጸናባቸው፥ ከፈጣሪያቸውና ከቤተ ሕዝቡ የሚጠበቅባቸውንም ተገቢ ተልእኮ ከመፈጸም ሊያግዳቸው ይችላል።

ከዚህ የተነሣ፡ ስለጽድቅ፡ ማለትም ስለእውነት፡ መራብንና መጠማትን፥ ማጣትንና መዋረድን፥ መታሠርንና መሰደድን፥ በሌሎቹም የፈተናና የመከራ ዓይነቶች መሠቃየትን፡ እጅግ አድርገው ይፈሩታል፤ ይሠቀቁታል፤ መገደልንማ፡ ሊያስቡትም እንኳ አይፈልጉም፤ በእውን ሲያስቡት፡ በድንጋጤ ያባንናቸዋል፤ ይህም ጉድ፡ በታሠሩትም፥ ባልታሠሩትም ዘንድ፡ በገሃድ ታይቷል።

## በደርግ በታሠሩትና ባልታሠሩት "አባዎች" ዘንድ የታየ ጉድ!

በዚህ ረገድ፡ ከታዩት ኹነታዎች መካከል፡ ከእያንዳንዱ ወገን፡ አንዳንድ ድርጊትን፡ ለምሳሌ ያህል እጠቅሳለሁ። ይኸውም፡ ከታሠሩት ወገን፡ በ፩ኛ ክፍለ ጦርና በታላቁ ቤተ መንግሥት የደርግ እሥር ቤት ውስጥ ሣለን፡ ቀደም ብሎ፡ ማናቸውም መጽሐፍ፡ የጸሎት ጭምር፡ ተሰብስቦ፡ ከእሥር ቤቱ እንዲወጣ በታዘዘበት ጊዜ፡ በዚያ፡ በአንደኛው ክፍል የነበሩት፡ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም የተባሉት መነኵስ፡ በዚህ ውሳኔና ትእዛዝ የተደናገጡትን ሌሎቹን እሥረኞች እያጽናኑ በማበረታታት ፈንታ፡ እንደሕፃን ልጅ ያለማቋረጥ እየጮኹ በማልቀስና በተገላቢጦሽ፡ የእሥረኞቹን ማጽናናት፡ አልቀበል ብለው በማስቸገር፡ እየተንሰቀሰቁ ያፈሰሱት እንባና ያሳዩት ፍርሃት ነው።

ካልታሠሩት ወገን ደግሞ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስ፡ ገና በመንበረ ሥልጣናቸው ላይ ሣሉ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በዚያው፡ በደርግ እሥር ቤት እንዳሉ፡ በግፍ መገደላቸው እየታወቀ፡ በሕመም እንዳረፉ ኹኖ፡ ለወገኖቻቸው፡ መርዶው፥ ለባለጊዜዎቹ ግን፡ "ዜናው"፡ በይፋ በተነገረ ጊዜ፡ እጨጌውና ጳጳሳቶቻቸው የፈጸሙትን ድርጊት የሚመለከት ነው። እነዚህ ጳጳሳት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን፡ ታሥረው በነበረበት ጊዜ፡ በሕይወተ ሥጋ እያሉ፡ ሊያደርጉላቸው የሚገባቸውንና ለእርሳቸውም እጅግ ያስፈልጋቸው የነበረውን የመናዘዝ (የማጽናናት) በጎ ምግባር ሳይቀር እንደነፈጓቸው በኹሉ ዘንድ ይታወቃል።

"ዐረፉ!" በተባለበት ጊዜ ግን፡ ከሞታቸው በኋላ፡ በበድናቸው ላይ ጸሎተ ፍትሐት ለማካኼድ ይችሉ ዘንድ፡ እንዲፈቀድላቸው ለማመልከት፡ አባ መቃርዮስ በተባሉት መሪነት፡ ጥቂቶች ሊቃነ ጳጳሳት፡ ያለሃፍረት ወደደርግ ተላኩ። በመሠረቱ፡ ተገቢውን ጸሎተ ፍትሐት፡ ያለምንም ጥያቄ፡ በራሳቸው ውሳኔ ብቻ፡ በቀጥታ ማድረግ ሲችሉና ሲገባቸውም፡ ነገር ግን፡ ይህን ማድረግ ትተው፡ ከይሉኝታና ከፍርሃት የተነሣ ብቻ፡ የደርግን ፈቃድ ለመቀበል፡ ወደእርሱ እንደመጡ፡ አንድ የደርግ አባል ተቀብሎ፡ በቁርጥ ቃል "አይቻልም!" ብሎ መልስ በመስጠት፡ ሠይፍ መዝዞ፡ "ይህን ታዩታላችሁ? ይህ ሠይፍ፡ በኹለት ፊት ስለት ያለው ስለኾነ፡ በኹለት ወገን የሚመጡበትን ተቃዋሚዎቹን ይቆርጣል! ደግሞ ማንንም አይመርጥምና፡ ኹለተኛ በዚህ ጉዳይ እንዳትመለሱ!" በሚል ኃይለ ቃል፡ የተሰነገለውን ሠይፍ እያወዛወዘ ባስጠነቀቃቸው ጊዜ፡ በድንጋጤ እየተንቀጠቀጡና ሊወድቁ እየተርበተበቱ፡ እጅ በመንሣት፡ በጥድፊያ የሸሹበት፡ ሌላው ትርኢት ነው።

## “ብፁዕ!” እና “ቅዱስ!” ለመባል: የሚያስፈልጉት መሥፈርታት::

ይህን የመሰለውን ድርጊት ኹሉ: በገሃድ እየፈጸሙ: ጳጳሳቱ: አሁንም: “ብፁዕ” ወይም “ቅዱስ” መባልን: እጅግ አድርገው ይፈልጉታል! ይወድዱታልም:: እነዚህን የመንፈስ ቅዱስ ማዕርጋት የሚያሰጡት ምግባራት ደግሞ: እንደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል: እነዚያ: እነርሱ የሚፈሩዋቸውና የሚሠቀቋቸው የገድል ዓይነቶች ናቸው፤ “ማዕርጋቱ ይገባቸዋል!” ተብሎ: በመለኮታዊው ውሳኔ የሚሰጣቸውም ሰዎች: እነዚያን የገድል ምግባራት: በደስታና በትዕግሥት ተቀብለው ድል ያደረጉ: የሃይማኖት ጀግኖች ናቸው::

በእኛዎቹ አቡኖች ዘንድ ግን: ነገሩ: የተገላቢጦሽ ነው:: የምንኵስናቸውንና የጵጵስናቸውን: ስሙንና ክብሩን፥ ሥልጣኑንና ጥቅሙን እንጂ: ጵጵስናው: ከእነርሱ የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት የመክፈሉን ግዳጅ አይፈልጉትም:: በስም የሚመስሏቸው፥ በግብር ግን የማይስማሟቸው፥ በፋሺስቱ ጣልያን እጅ: የሰማዕትነት ጽዋቸውን የተቀበሉትንና እስካሁን የቅዱስነት ማዕርግ ሳይሰጣቸው የቆዩትን ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን: የመሰሉት: እኒያ: እውነተኞቹ መንፈሳውያን ተጋዳዮችና አርበኞች: የሚፈልጉትንና የሚወድዱትን: እኒህ አይፈልጉትም፤ አይወዱትምም:: እኒያ: የማይፈልጉትንና የማይወድዱትን ደግሞ: እኒህ ይፈልጉታል፤ ይወድዱታልም::

መሪያቸውና አርአያቸው አድርገው ሊከተሉት የሚገባው: ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ: ያዘዘውን ቃሉን እንኳ መፈጸም አይፈልጉም፤ እንዲያውም ይጠሉታል! ያንንም: የሚተላለፉትና የሚያፈርሱት: በድፍረትና በገሃድ ነው፤ ለዚህም: ትንሿን ምሳሌ ብጠቅስ ይበቃል:- እርሱም: *“ወኢትስምዩ አበ በዲበ ምድር! እስመ አሐዱ ውእቱ አቡክሙ ሰማያዊ፤ ወኢትረስዩ እግዚአ በዲበ ምድር! እስመ አሐዱ ውእቱ እግዚእክሙ ክርስቶስ!”* ማለትም: *“አባታችሁ: አንዱ፥ እርሱም: የሰማዩ ነውና: በምድር ላይ: ማንንም 'አባት!' ብላችሁ አትጥሩ! ጌታችሁ አንድ: እርሱም: ክርስቶስ ነውና: በምድር ላይ: ማንም ጌታ አይኑራችሁ!”* ያለውን ትተው: ለሌላ ጌታ፥ ለገንዘብና ለሥልጣን፥ ለሥጋዊዉም ሊቅነት ከመገዛት እንዳልዳኑ: ግብራቸው ይመስክራል:: ከዚህም ጋር: “አቡነ!” ማለትም: “አባታችን!” ተብለው ሲጠሩ: በዚህ ስም መጠራትን ደስ ብሏቸው ተቀብለው: በዚሁ እንዲቀጥሉ ምእመናንን ከማበረታታት በቀር: “የለም! ይህ ቃል: የሰማዩ አባታችን: እግዚአብሔር ብቻ እንዲጠራበት የተሰጠ ስያሜ ነውና: ጌታችንም: በዚህ ስም 'አትጠሩ!' ብሏልና: 'እኔን በዚህ አትጥሩኝ!' የሚል አንድም ጳጳስ እንደሌለ: ይኸው የሚታይ ነው:: ለአጠራራቸውም: *“ከእናንተ የሚበልጠው: አገልጋያችሁ ይኹን!”* ባለው: በጌታ መምሪያ መሠረት: እያንዳንዳቸው: “ለእኔ: 'አባ እከሌ!' ተብዬ: በስሜ መጠራት ይበቃኛል!” ማለት በተገባቸው ነበር:: ሊያከብራቸው የፈለገ ምእመን ቢኖር፥ እነርሱም: ይህንኑ ሊቀበሉት ከወደዱ: “ብፁዕነትዎ!” ወይም “ብፁዕነታቸው!” የሚለው የአክብሮት አጠራር፥ “አቡነ” ከመባልም: በሕዝባዊው አጠራር: “አቡን” መባሉ በበቃ:: አለዚያ: ያው ከጥንት የተለመደውና ሲያያዝ የመጣው: “የኔታ!” የሚለው የአክብሮት ቃል: አለ አይደለምወይ?

እንዲያውም፡ አንዳንድ ምእመናን ባለማወቅ፡ ከጳጳሳቱ፡ ከየእግራቸው ላይ ወድቀው፡ እንደአምላክ ሲሰግዱላቸው፡ *"ወአነ ዮሐንስ፡ ዘርኢኩ+ ወዘሰማዕኩ ዘንተ፡ ሰገድኩ ቅድመ እገሪሁ፡ ለውእቱ መልአክ፡ ዘአርአየንዮ ለዝንቱ:: ወይቤለኒ፡ 'ኢትስግድ ሊተ! ዑቅ! ዮጊ፡ ገብረ አጋእዝቲከ አነ+ ወዘአኃዊከ ነቢያት+ ወዘእለ የዐቅቡ ቃለ ዝንቱ መጽሐፍ:: ወአንተሰ፡ ለእግዚአብሔር ስግድ!"* ማለትም፡ *"ይህን የሰማሁትና ያየሁት፡ እኔ ዮሐንስ ነኝ! ይህንንም ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ:: እርሱም:: 'ለእኔ እንዳትሰግድልኝ ተጠንቀቅ! እኔም እኮ፡ ከአንተና ከወንድሞችህ ሐዋርያት+ የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር፡ አብሬ፡ የፈጣሪህ ባሪያ ነኝ:: አሁንም፡ አንተ፡ ለእግዚአብሔር ስገድ!' አለኝ::"* ያለውን፡ የመልአኩን ቃል እንኳ አስታውሰው፡ "ተዉ እንጂ! ለእኔ ሳይኾን፡ ለእግዚአብሔር ስገዱ!" ብለው፡ እኒያን ምእመናን በማስተማርና በመገሠፅ ፋንታ፡ አድራጎታቸውን፡ ዝም ብለው ተቀብለው፡ በማጽደቅ፡ መስቀላቸውን ከማሳለም በቀር፡ የሚናገሩት አንዳችም ነገር፡ ከቶ የለም::[፲፩]

ለጽጽስና ተመርጦ መሾም፡ በራስ ፍላጎትና ምኞት ላይ የተመሠረተ÷ ወይም፡ በተለይ፡ በአሁኑ ዘመን፡ ከጽጽስና ሹመት የሚጠበቀውን ግዳጅ ሳያውቁትና ሳይረዱ፡ ለክብሩና ለጥቅሙ ብቻ ሲሉ የሚቀበሉት የኾነ እንደኾነ፡ በተሿሚው ላይ፡ ፍጻሜው፡ የቱን ያህል ከባድና አሳዛኝ ኾኖ እንደሚገኝ የሚያስገነዝብ፡ አንድ የቅርብ ጊዜ ኹነታን፡ እዚህ ላይ አወሳለሁ:: ይህ ኹነታ፡ ሲያወጉት፡ ለጊዜው ፈገግ ያሰኛል፤ መልእክቱ ግን፡ ለተነሣንበት ቁም ነገር፡ ፍጹም ተገቢነትና ተስማሚነት አለው::

## የሆሣዕናው ሥርዓት አርአያነት::

በርእሰ አድባራት አኵስም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን፡ የሆሣዕና በዓል፡ በከፍተኛ ድምቀትና ሕያውነት ባለው መንፈሳዊ ሥርዓት ይከበራል::

ያን፡ በአኵስም የሚፈጸመውን ሥርዓት፡ አዲስ አበባ በሚገኝ፡ በአንድ ደብር፡ ለማክበር ታስቦ፡ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፡ በበዓሉ ዕለት፡ በግምጃና በወርቅ የተንቈጠቈጠ ልብሰ ተክህኖን ተጎናጽፎ÷ በሙሉ የኮርቻ ዕቃ በተጫነች÷ በጥልፍ ግላስ÷ በተጌጠ መረሻትና በተዋበ መጣብርም በተሸለመች በቅሎ ላይ ተቀምጦ÷ የወርቅ ድባብ ተዘርግቶለት፡ በዑደተ ሆሣዕና ሥርዓት፡ የዘንባባ ዝንጣፊ በያዙ፡ ካህናትና ምእመናን ታጅቦ÷ "ሆሣዕና በአርያም!" እየተባለ÷ በማኅሌት÷ በዕልልታና በሆታም እየተወደሰ፡ በጌታችን ምሳሌ፡ ቤተ ክርስቲያኑን የሚዞረው ካህን፡ ታዲያ፡ "ማ ይኹን?" እየተባለ ምርጫው በሚካኼድበት ጊዜ፡ ከካህናቱ መካከል፡ ብዙዎቹ፡ "እኔ ልኹን! እኔ ልኹን!" እያሉ አስቸገሩ:: ከመራጮቹ አንዱ፡ "አውቃችሁታል? በሆሣዕና ዕለተ እሑድ፡ የወርቅ አክሊል ደፍቶ÷ በወርቅ ልብስ ተሸልሞ÷ በወርቅ ዕቃ በተሸለመች በቅሎ ላይ ተቀምጦ፡ "ሆሣዕና በአርያም!" እየተባሉ÷ በውዳሴና በይባቤም እየተመሰገኑ መዞር ብቻ እኮ አይደለም! በሚመጣው ዕለተ ዓርብ፡ ተገርፎ መሰቀልም እኮ አለ!" አላቸው:: በዚህ ጊዜ፡ ያ ኹሉ ሽሚያ ቀረና፡ ኹሉም፡ ወደኋላው አፈገፈገ! በመጨረሻ፡ ከመካከላቸው፡ አንዱ ተለምኖ፡ ራሱን በመንፈሳዊ ትሕትና ለዚህ አገልግሎት አቀረበ!

## የጵጵስና ሕይወት፡ መንፈሳዊነቱን እንዳይለቅ።

የዛሬዎቹ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት፡ የምንኵስናና የጵጵስና ሕይወታቸውን የሚኖሩት፡ እንደኢትዮጵያውያን ባህልና ሥርዓት፡ በመንፈሳዊነት ሳይኾን፡ እንደሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት፡ ዘመናውያን ጳጳሳት፡ ወደ ሥጋዊው አኗኗር የሚያዘነብል አዝማሚያ በሚታይበት መልክ በመኾኑ፡ ይህ ኹኔታቸው፡ ማዕርጉንና ሥልጣኑን ከአሳሳቢ ደረጃ ላይ አድርሶታል። የሌሎቹን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጳጳሳትና መነኮሳት ትተን፡ ለእኛዎቹ፡ "የቅርብ አርአያ ይኾናሉ" የሚባሉትን፡ የግብፃውያኑን፡ የቀረውን ድርጊታቸውንና የማናውቀውን ለእግዚአብሔር በመተው፡ በገሃድ የሚፈጽሙትን ብቻ ስንመለከት፡ ለኢትዮጵያውያን ሕይወትና ሥርዓት፡ የሚያሠቅቅ ኾኖ ይገኛል። ለዚህም፡ ከብዙው መካከል፡ አንዳንዶቹን፡ ማለትም፡ ጫማ አድርገው ወደቤተ መቅደስ የመግባትና ትንባሆ በይፋ የማጤስ ልማዳቸው፡ ምሳሌ ኾኖ ሊጠቀስ ይቻላል።

ይህን የመሰለውን ድርጊት በግብፃውያኑ ላይ ለሚመለከት ኢትዮጵያዊ፡ የዛሬዎቹ የኢትዮጵያውያኑ መነኩሳትና ጳጳሳት የኹኔታቸውና የድርጊታቸው አዝማሚያ፡ አያስደንቀው ይኾናል። ምክንያቱም፡ ለእየራሳቸው ሕይወት መመሪያ ይኾናቸው ዘንድ፥ ደግሞም፡ ምክር፥ ማስጠንቀቂያና ተግሣፅ ይኾናቸው ዘንድ፡ በትርጓሜና በሐተታ ሳይቀር፡ ተብራርቶ በተዘጋጀላቸው መጽሐፍ ውስጥ፡ ስለእነርሱ አካኼድ፡ ከመነሻው እስከመድረሻው፡ አስቀድሞ፡ በትንቢት የተነገረና በይፋ የታወቀ በመኾኑ ነው። ይህም መጽሐፍ፡ "ማር ይስሐቅ፥ ፊልክስዩስና አረጋዊ መንፈሳዊ" የተባሉትን፡ ሦስት ታላላቅ ክፍሎች የያዘው፡ መጻሕፍተ መነኮሳት ሲኾን፡ ከዚህ ውስጥ፡ የአንዷቱን ዓምድ ክፋይ እንኳን፡ ጠቀስ አድርገን ብንመለከተው፡ በመልእክቱ ትክክለኛነትና እውንነት፡ እጅግ ተገርመን፡ በአንክሮ እንዋጣለን።

## የመጻሕፍተ መነኮሳቱ ትንቢት፡ ደርሶ ማየት።

ይህን ርእሰ ነገር የሚመለከተው፡ የዚሁ መጽሐፍ፡ አንዱ ኃይለ ቃል፡ "ፊልክስዩስ" በተባለው ክፍል፡ በመቅድሙ ውስጥ ተጽፎ ይነበባል። ሲነበብም፡ መንፈሳዊው ሕይወት፡ በማናቸውም መልኩና ደረጃው፡ ማለትም፡ በብሕትውናው ኾነ በገዳማዊነቱ ጭምር፡ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን፡ እንግዳ ነገር ሳይኾን፡ ከቀድሞዎቹ፡ ከነኄኖክና ከነመልከ ጼዴቅ ጀምሮ፡ እስከቅርቦቹ፡ እነአጼ ካሌብና እነአባ ተክለ ሃይማኖት ድረስ የኖርንበት፡ ጥንታዊ ሥርዓታችን መኾኑን በመገንዘብ ሊኾን ይገባል። ይህ፡ እየተፈጸመ የሚታየው፡ የትንቢት ቃል፡ የምንኵስናንና የገዳማዊነትን የኑሮ ሥርዓታት፡ በግብፅ በረሃ፡ ለግብፃውያን፡ "መሠረቱ!" የሚባሉት፡ ግብፃውያኑ ጳውሊ፥ እንጦንስ፥ መቃርስና ጳኩሚስ፡ ገና በሥርዓታቱ ውጥን ላይ ሣሉ፡ በተለይ፡ ጳውሊና እንጦንስ፡ ስለመነኩሳትና ጳጳሳት፡ የተወያዩበትን፡ የራእይ ምሥጢር የሚመለከተው ሲኾን፡ እርሱንም፡ መላው የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፡ ያውቀው ዘንድ፡ እነሆ ቀርቧል።

የዚያ ራእይ እውንነት፡ እስካሁን በኾነውና አሁንም፡ እየኾነ በሚታየው ኹነታ፡ በእርግጥ ደርሶና ተፈጽሞ በመገኘቱ፡ ከማስደነቁ ጋር፡ ያስደነግጣል። ይኸውም፡ በመጀመሪያው ዘመን፡ የነበሩት፡ የእንጦንስ ተከታዮች መነኰሳት፡ በነጫጭ ርግቦች፥ በመካከለኛው ዘመን የኖሩት ደግሞ፡ በዥጉርጉሮች አሞሮች፥ ዛሬ፡ በመጨረሻው ዘመን ያሉትም፡ በጥቋቁር ቁራዎች ተመስለው የነበሩ በመኾናቸው ነው። *"የማያዩ እንዲያዩ፥ የሚያዩም እንዲታወሩ፡ እኔ፡ ወደዚህ ዓለም፡ ለፍርድ መጣሁ!"* የሚለውና የማይታበለው የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል የሚጸናባቸው ካልኾነ በቀር፡ በዚህ ረገድ የሚታየውን፡ የትንቢቱን ፍጻሜ፡ ራሳቸው፡ የዛሬዎቹ መነኰሳትና ጳጳሳት፡ ከማንም የበለጠ፡ በየራሳቸው በሚኾነው ጭምር እየተገነዘቡት፡ በቀላሉ ሊያስተውሉት አይቸግራቸውም።[፻፷፰]

ይህን የሚመስለውን ምንነታቸውን የሚገልጸው፡ የመጻሕፍተ መነኮሳቱ ጥቅስ እንዲህ ይላል፡- "*ጳውሊና እንጦንስ፡ (ጳውሎስና እንጦንዮስ)* ተጫዋውተው ሲያበቁ፡ *ጳውሊ፡ ለእንጦንስ፡* ባጠገቡ፡ ለብቻው በዓት ሰጠው፤ *እርሱም፡* ከዚያ ኾኖ፡ ጉዳዩን ሲያደርግ ዋለ። *ለጳውሊ፡* ወትሮ፡ መንፈቀ ኅብስት ይወርድለት የነበረ፡ ማታ፡ ምሉእ ኅብስት ወረደለት። *እንጦንስ፡* በፈቃደ እግዚአብሔር፡ ወደእርሱ መምጣቱን፡ ያን ጊዜ አወቀው። ወዲያው፡ ያን ኅብስት፡ ከኹለት ገምሶ፡ እኵሌታውን አስቀርቶ፡ እኵሌታውን፡ *ለእንጦንስ* ሰጠው። ያን ተመግበው፡ ሌሊት፡ ኹሉም፡ በየሥራቸው፡ ክብራቸው ተገልጾ፡ ሲተያዩ አድረዋል። ጳውሊ፡ ዓሥር ጣቶቹ፡ እንደፋና ኾነው እያበሩለት፡ አራቱን ወንጌል ሲያደርስ፥ እንጦንስም፡ እንደዓምደ ብርሃን ተተክሎ፡ ሲያበራ ተያይተዋል። በዚያች ሌሊት፡ ከዚያች ቦታ፡ ጨለማ ጠፍቶ አድሩአል።

"በነጋው፡ እንዲህ ሠለስት እላፌ ሲኾን፡ ጉዳያቸውን አድርሰው ሲያበቁ፡ ተገናኝተው ሲጫዋወቱ፡ *ጳውሊ፡ የእንጦንስን፡* ቆቡን አይቶ፡ 'ይህን ከማን አገኘኸው?' አለው።

"እርሱ፡ ባለቤቱ ሰጠኝ!" አለ *እንጦንስ፡*

"እርሱም፡ (ጳውሊ)፡ የጌታን ቸርነት ያደንቅ ዠመረ፤ '*እግዚአብሔር፡* ቀድሞ፡ ሰውን ፡ይጠቀም!፡ ብሎ፡ በሕገ ልቡና ፈጠረው። *ሰው ግን፡* በዚያ መጠቀም ባይኾንለት፡ ሕገ ኦሪትን ሠራለት። ኋላ ደግሞ፡ *ሰው፡* በዚያ መጽደቅ ባይቻለው፡ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፥ ከእመቤታችን ተወልዶ፥ ሰው ኾኖ፥ *ሥጋ* ለብሶ፡ ሕገ ወንጌልን ሠራ፤ *ሥጋውን* ደሙን ሰጠ። ዛሬ ደግሞ፡ ለሰው መጽደቂያ፡ እንዲህ ያለ፡ ምክንያተ ድኅን አመጣ!? ይህን ያህል፡ ቸርነት!' ብሎ አደነቀ።

"*እንጦንስም፡ 'ይህ ቆብ፡* እስኪ፡ በእኔ ብቻ የሚቀር እንደኾነ፥ ለሌላም የሚያልፍ እንደኾነ፡ ወደእግዚአብሔር አመልክትልኝ!?' አለው፡ *ጳውሊን።*

"*ጳውሊም፡ ወደእግዚአብሔር* አመለከተ*።* ወዲያው ተገለጸለት። 'ወአክሞሰሰ' ይላል፤ ደስ አለው።

"*እንጦንስም፡* 'ምን አየህ?' አለው።

"'ጻዕድዋን አርጋብ (ነጫጭ ርግቦች)፡ በጠፈር መልተው፡ አንተ እየመራሃቸው፡ ተከትለውህ ሲኼዱ አየሁ!' አለው፡ *ጳውሊ።*

"'ታዲያ፡ ይህ ያየኸው ምንድር ነው?' ቢለው፡ እንጦንስ፡

"'እሊህማ፡ በዚህ፡ በቆቡ የምትወልዳቸው፡ እውነተኞቹ ንጹሓን ልጆችህ ናቸው' አለው።

"'ኹለተኛ አመልክትልኝ!' አለው።

"አመለከተ። 'ወደመነ ገጹ' ይላል፤ አዘነ! ጳውሊ።

"እንጦንስም፡ 'ምነው?' ቢለው፥

"'ከክንፋቸው፡ ጥቁር ተቀላቅሎባቸው አየሁ!' አለ።

"'ምንድር ናቸው?' ቢለው፡ እንጦንስ፥

"'ጽድቅና ኃጢአት እየቀላቀሉ የሚሠሩ ልጆችህ ናቸው!' አለው።

"'ሦስተኛ አመልክትልኝ!' አለው፡ እንጦንስ እንደገና።

"አመለከተ። 'ገዐረ፤ ወበከየ!' ይላል፤ ቃሉን፡ ከፍ አድርጎ ጮኸ!

"እንጦንስም፡ 'ምነው?' አለው፡ ጳውሊን።

"'አርጋብስ፡ አርጋብ! (ርግቦችስ፡ ርግቦች ናቸው!) ነገር ግን፡ እንደቁራ ጠቁረው አየኋቸው!' አለ ጳውሊ።

"'ምንድር ናቸው?' ቢለው፡ እንጦንስ፥

"'ኃሣሥያነ ሢመት' (ሹመት ፈላጊዎች)፥ 'መፍቀርያነ ንዋይ' (ገንዘብ ወዳጆች)፥ 'እለ ይሠርዑ በነግህ፡ ማዕደ፡ ምስለ መኳንንት' ይላቸዋል፡ (ከዓለማውያን፡ ሥጋውያን ባለሥልጣኖች ጋር ማልደውና ተግተው፥ ተመሣጥረውና ተባብረው፡ በማናቸውም የምግብና የተግባር ማዕድ ላይ፡ ጠም ሳይቀር እየገደፉ፥ ማናቸውንም ኃጢአት አብረው እየፈጸሙም፡ የሚሳተፉ) በፍጻሜ ዘመን የሚነሡ፡ ኃጥአን ልጆችህ ናቸው!' አለው፡ ጳውሊ።

"በዚህ ጊዜ፡ እንጦንስ፡ 'አምላኬ፡ እሊህን፡ ያለንስሓ ባይጠራቸው (እንዳይጠራቸው) እስኪ አመልክትልኝ!?' አለው።

"ጳውሊም፡ ወደእግዚአብሔር አመለከተ። ነገር ግን፡ የዚህ ምላሽ አልመጣለትም። መምህር ገብረ መድኅን ግን፡ መጥቶለታል፤ 'አልጠራቸውም!' ብሎታል፡ ይላሉ።"[፻፷፱]

እኒህ ኹሉ፡ ከላይ፡ በተራ የተገለጹት፡ ያለፉትና የቅርቦቹ ድርጊቶች፡ ለዛሬዎቹም ኾነ ለወደፊቶቹ ካህናት፥ መነኰሳት፥ ጳጳሳትና እጨጌዎች፡ ትምህርት ኾኗቸው፡ ራሳቸውን ሊያርሙና ሊያስተካክሉ፥ በመልካም አርአያነታቸውም፡ ለሌሎች በጎ ምሳሌዎች ሊኾኑ የሚገባቸው ይመስለኛል።

## ኢትዮጵያ፡
## ስለአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የተቀባ ሰውነት፡
## ስትፋረድ!

ቀደም ብሎ፡ በየቦታው በተገለጸውና ያን በመሳሰለው፡ አሳዛኝና አሳፋሪ ተግባር ተመልተው ያሉት፡ የቀደሙት ጳጳሳትና የዛሬዎቹ ተተኪዎቻቸው፡ አመቺ የሥነ መንግሥት አገዛዝ የሠፈነበት ዘመን እስኪመጣላቸው ድረስ፡ ለሃያ አምስት ዓመታት ሲጠባበቁ ከቆዩ በኋላ፡ ልክ፡ ያ፡ የፈለጉት ወቅት ሲደርስላቸው፡ በአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ የፈጸሙትን፡ አሳፋሪ ድርጊት እስቲ እንመልከት!

ይኸውም፡ "ደርግ" አጼ ኃይለ ሥላሴን ገድሎ፡ በየትኛው ቦታ እንደቀበረው ያልታወቀውንና በድናቸው ለመኾኑ በፍጹም እምነት፡ ያልተረጋገጠውን ዐፅም፡ ወደቤተሰብ መቃብራቸው እንዲገባ ለማድረግ፡ በጊዜው የአጋጣሚ ኹኔታ በመጠቀምና የጉዳዩ ባለቤቶች ለመኾን በመሞከር፡ የዛሬዎቹ አቡኖች፡ በተረኛው እጨጌ፡ በአባ ጳውሎስ መሪነት፡ ከሌሎቹ ዓለማውያን ተወዳዳሪዎቻቸው ጋር ያሳዩት፡ ይሉኝታ ያጣው የከንቱ ውዳሴ እሽቅድድማቸው ነው። በታዕካ ነገሥት በዓታ ለማርያም መካነ መቃብር ውስጥ በክብር እንዲያርፍ የተደረገውን፡ ይህንኑ ዐፅም፡ ወደመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የማዛወሩን ተግባር፡ ቅርብ በኾነው ቀጥተኛ መንገድ፥ አግባብ ባለውም፡ በተለመደው መንፈሳዊ ስሜትና ሥርዓተ ጸሎት፡ በጽሞና አከናውኖ መፈጸም ሲቻል፡ ዳሩ ግን፡ የመንግሥት በትረ ሥልጣን ለመያዝ፡ ማናቸውንም ነገር ከመሠዋት ወደኋላ ከማይሉት፡ ከቤተ ምልክናው ዓለማውያን ፈሊጠኞች ጋር በመመሣጠርና በመተባበር፡ መከረኛውን ዐፅም፡ ወደመስቀል አደባባይ ወስደው፥ ከዚያ፡ እንደወግ ዕቃ፡ በከተማዪቱ አደባባዮችና ጎዳናዎች በማዘዋወር ያካኼዱት፡ የተቀነባበረና የተቀናጀ ትእይንተ ሕዝብ፡ በእግዚአብሔር ፊት ቀርቶ፡ በምድራውያን የዓለም ተመልካቾች ዘንድ፡ የዘመኑን የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ከእንዴት ዓይነቱ ትዝብት ላይ እንደጣለ መገመቱ፡ ለማንኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አይከብደውም። እንደተውኔት በሚቆጠረው በዚህ ድርጊት[1] የተባበሩት ኹሉ፡ ምንነታቸው፡ በመላው ዓለም ታዛቢዎች ዘንድ በበለጠ ተጋልጧል።

## ይሉኝታና ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት ድርጊት።

አዎን! በዚህ ድርጊት፡ የዘመኑ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ማለትም፡ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው ብቻ ሳይኾኑ፡ ቤተ ሕዝቡ ጭምር፡ በእውነተኞች የዓለም ተመልካቾች ዘንድ፡ እጅግ በሚያሳፍር የትዝብት ሚዛን ላይ ወድቀውና ቀልለው መገኘታቸው፡ በጽኑ ሊያሳዝን ይገባል። ቅሌቱ፡ ነገሩ፡ በእግዚአብሔር ስም የምትታወቀውን፡ ኢትዮጵያንና የቃል ኪዳን እምባኳን፡ በዓለም ፊት ማስገመቱ ነው! ውድቀቱ ደግሞ፡ *"ወኢትግሥሡ መሢሓንየ"*፡ ማለትም፡ *"እኔ መርጬ በሾምኋቸው (በቀባኋቸው) ላይ እጃችሁን አታንሡ!"* የሚለውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ ያለይሉኝታና ያለፍርሃት መተላለፉ ነው።[፲፬]

ይህን አጭር አገላለጽ፡ እንዲህ በሚል፡ የቃላት ሓረግ ማብራራት ይቻላል፡- የቤተ ምልክናውን ሥልጣን ይዞ የነበረው ደርግ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ሕያው ሰውነት ላይ፡ ከዙፋን አውርዶ፥ አሥሮና አጉላልቶ፡ እስከመግደል በደረሰ ጭካኔ፡ ያን ያህል ግፍ ሲፈጽምባቸው፡ እኒህ፡ የቤተ ክህነቱ መሪዎች፡ ጳጳሳትና የቤተ ሕዝቡ ቀንደኞች፡ የቀድሞ ባለሥልጣኖች፡ አንዲት ቃል ሳይተነፍሱ፡ በተባባሪነትና በግብረ አበርነት፡ ዝም ብለው መመልከታቸው ይታወሳል። ዛሬ፡ ለየራሳቸው፡ የግል ዝና፥ ጥቅምና ዓላማ ማራመጃ፥ በሰውም ዘንድ፡ በከንቱ ውዳሴ ለመወደድና ለመከበር፥ ሥልጣኑን በያዘውም መንግሥት ላይ ያላቸውን የግል ተቃውሞ፡ በአጋጣሚው በመጠቀም፡ ስሜታቸውን ለመግለጽና ፍላጎታቸውን ለመፈጸም በሚሹበት ጊዜ ደግሞ፡ አፈር በኾነው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ምውት ዐፅም ላይ ያካኼዱትን ጉድ ድርጊታቸውን፡ ዓለሙ አይቶታል።

ይኸውም፡ ምንም የማያየውንና የማይናገረውን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ምውት ዐፅም፡ ጥሩ አጋጣሚ ምክንያታቸውና ተስማሚ መሣሪያቸው በማድረግ፡ ያን የመሰለ፡ የተቀነባበረ፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የተርእዮ ዝግጅት የተመላበትን ትእይንተ ሕዝብ ማካኼዳቸው ነው! ይህም፡ የሃይማኖት ውድቀትንና የምግባር ቅሌትን አረጋግጦ ያሳያል።

በዚህ ድርጊታቸው፡ "ይህ፡ ራሱን፡ 'ጥንታዊ ክርስቲያን' ብሎ የሚጠራ ሕዝብ፡ ሃይማኖታዊ ምግባሩን የሚፈጽመውና ሰብአዊ ስሜቱን በይፋ የሚያረካው፡ ወገኑን፡ በሕይወተ ሥጋ ሣለ፡ በህልውናው እንዲቀጥል በመርዳት ሳይኾን፡ ገድሎ በመቅበር ነው እንዴ!?" የሚለው፡ የሰውን የአውሬነት የተፈጥሮ ዝንባሌ የሚያንጸባርቀውና ሃይማኖት ሳይቀር ሊያሻሽለው ያልቻለው፡ ከፋው የሰብአዊ ባሕርይ ገጽታ፡ በተጨባጭ ማስረጃ ተጋልጧል! የኢትዮጵያውያንንም ሃይማኖት፡ አጠያያቂ አድርጎታል። የዘመኑን የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ማንነትና ምንነት ለማወቅና ለመመዘን፡ ራሱ፡ ይኸው አንድ ትውልድ፡ ለሕያዉና ለምውቱ "ቅቡዕ መሪው ሰውነት" በአንድ ጊዜ፡ ካሳየው፡ ይህን ከመሰለው፡ ተለዋዋጭ አቋሙና ከፈጸመው ግልብጥብጥ ድርጊቱ በላይ፡ ሌላ ማስረጃ ሊቀርብ ከቶ አይቻልም።

## ከክርስቶስ የሕይወት ቃል ይልቅ
## የዲያብሎስ የሞት ሕግ የሰፈነበት ሥርዓት።

በዘመኑ፡ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዘንድ፡ ሰፍኖ የሚካኼደው፡ ይህ፡ ሥር የሰደደ ልማድ፡ ከደርግ የጭካኔና የግፍ ድርጊት ባላነሰ መጠን፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ በዓለም ሕዝብ ዘንድ፡ በሚጎዳ መልክ፡ ያስገመተ በመኾኑ፡ አሳዛኝነቱ እሌ ሊባል ከቶ አይቻልም፤ ይኹን እንጂ፡ አሁንም፡ ይኸው ልማድ፡ እንደመልካም ባህል ተቆጥሮ፡ እየተዘወተረ በመቀጠል ላይ ያለ፡ የዕለት ተግባር እንጂ፡ እንደእንግዳ ነገር የሚታይ አይደለም! ይህም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እናንተ፡ በሕይወት ካሉት መካከል አንዱን የተራበውን ስላበላችሁልኝ፥ የተጠማውን ስላጠጣችሁልኝ፥ የታረዘውን ስላለበሳችሁልኝ፥ የታመመውን ስለረዳችሁልኝና የታሠረውን ስላጽናናችሁልኝ፥ የሚንከራተተውንም ስላሳረፋችሁልኝ፡ እኔ ደግሞ ያዘጋጀሁላችሁን የዘለዓለም ሕይወት ውረሱ!"* የሚለውን መለኮታዊ ቃሉንና *"ሙታንን ተዉዋቸው! ሙታናቸውን ይቅበሩ!"* ያለውን መመሪያውን በሚቃወም አቋም፡ ዲያብሎስ፡ "የለም፥ 'ብሞት ቀበራችሁኝ!' የሚል፡ ከእነዚያ ኹሉ የሚበልጥ ሌላ ቃል አለና፡ እርሱን ፈጽሙ!" ያለ ይመስል፡ ሕያዋንን፡ በቁማቸው ለመርዳት ሳይኾን፡ የሙታንን ሥጋ ለመቅበር ብቻ፡ "ዕድር" እየተባለ፡ በየሠፈሩ ተቋቁሞ በሚካኼደው ማኅበራዊ ዓላማ፡ በየቀኑ ሲፈጸም ይታያል።

ይህን አሳዛኝ ኹኔታ ለማረጋገጥ፡ እነዚያ፡ የዘለዓለማዊው ንጉሠ ነገሥት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖታውያን መመሪያዎች፡ የምእመናንና የካህናት፡ ሙሉ ተሳታፊነት ባለባቸው፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው አማካይነት፡ በምግባር ተተርጉመው፡ ለፍሬ እንዲበቁባቸው ተብሎ፥ ታስቦና ታቅዶ፡ በ፲፱፻፷፭ ዓ. ም. በመላዋ ኢትዮጵያ፡ በሕጋዊ አዋጅ ከተቋቋሙት "ሰበካ ጉባዔዎች" መካከል፡ ዛሬ፡ የትኞቹ ናቸው፡ የተቀደሰ ዓላማቸውን በተግባር ላይ አውለው ለፍሬ ያበቁ?

ይህም ማለት፡ በሥጋና በመንፈስ፥ በሃይማኖትና በምግባር፥ በትምህርትና በሙያ፡ የተራቡትን የሚያበሉ፥ የተጠሙትን የሚያጠጡ፥ የታረዙትን የሚያለብሱ፥ የታመሙትን የሚያክሙ፥ የታሠሩትን ነጻ የሚያወጡ፥ ቤት-አልባ የኾኑትንም፡ ለባለቤትነት የሚያበቁ ተግባሮችን እያካኼዱ ያሉት የትኞቹ ናቸው? ለመኾኑ፡ አሉ? ካሉስ፡ ስንት ናቸው? አንድ? ኹለት? ሦስት? ወይስ ምንም ፻፹፩ የለም? ወይስ፡ ይባስ ተብሎ፡ ቀደም ብለው የነበሩትም ተዘግተዋል?

ከኹሉ ይልቅ የሚያሳዝነው፡ ነገሩ፡ ሃይማኖትን የሚመለከት ስለኾነ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ *"ምእ እንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመንግሥቱ መለኮታዊ ምልክት፡ ከቤተ ምልክናው ብቻ ሳይኾን፡ ከቤተ ክህነቱም ተወግዶ፡ በሌሎች ምልክቶች መተካቱን እያወቀ፡ በሕያዉ ንጉሠ ነገሥት፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በአምላካዊ ማንተሙ ላይ ስለተፈጸመው የክህደት ዓመፅ፡ ምንም ዓይነት ደንታ የሌለው መኾኑን፡ በዚህ ድርጊቱ፡ በይፋ ማረጋገጡ ነው። ይህንኑም፡ ስለዚሁ ዓቢይ የሃይማኖት ጉዳይ ከመናገር ይልቅ፡ ለሟቹ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ዐፅም፡ ቅድሚያንና ብልጫን ሰጥቶ፡ ያን ያህል ከፍተኛ እንቅስቃሴንና ዝግጅትን በማድረጉ አሳይቷል። ከዚህ የተነሣ፡ ሕዝባዊዉም፥ ካህኑም፥ ምሉኩም፡ በኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ፥ አምልኮቱና ንስሐው ረገድ፡ በምን ዓይነት ዐዘቅት ውስጥ እንደወደቀ፥ የውርደት ደረጃውም፡ እምን ላይ እንደደረሰ፡ ለአስተዋይ ተመልካች የሚሰጠው ግንዛቤ፡ በቂ ይኾናል።

## የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ በመለኮታዊው ሥልጣን፡ ዳግመኛ ከመጠየቅ አያመልጡም።

በዚያ አጋጣሚና በየምክንያቱ፡ በየአደባባዩ፡ ቤተ ሕዝቡን እየወከሉ ሲናገሩ የሚደመጡት፡ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት፥ ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ሥላሴ፥ ራስ መንገሻ ሥዩም፥ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ፥ እነርሱንም የመሰሉት፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ አረጋውያን ሹማምንት፡ በየዘመናቱ ከደረሱት፡ የቅጣት፥ የስደትና የሞት መከራዎች እየታደጋቸው፡ በሕይወት ላቆያቸው ቸር ፈጣሪ፡ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚከፍሉት ውለታ፡ ዛሬ፡ እያካኼዱ የሚታየውን ድርጊት የሚመስል ይኾናል ብሎ ለመገመት፡ ለማንም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ አዳጋች ነው። ይኸውም፡ በዚህ፡ ዓቢይ ሃይማኖታዊ ጉዳይና የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ ይህ ትውልድ ሊያውቅ የሚገባውን፡ እውነተኛ የምስክርነት ቃላቸውን በመስጠት ፋንታ፡ እግዚአብሔር፡ በኢትዮጵያ፡ የሠራው ሥርዓተ መንግሥት ፈርሶ፡ ሰው ሠራሹና የባዕዳኑ እንዲተካ ለማድረግ፡ እነሆ፡ ዲያብሎስ፡ በአገልጋዮቹ አማካይነት በሚያካኼደው፡ የሞትና የሕይወት ከፍተኛ ዘመቻው ውስጥ ተካፋዮች እንደኾኑ የሚያስመስላቸውን፡ ይህን አሳሳችና አደናጋሪ አቋም ይዘው መገኘታቸው ነው። በዚህም፡ እነርሱና እነርሱን የመሰሉት አዛውንቶች ኹሉ፡ በዘለዓለማዊው ዳኛ ፊት፡ በነፍስ ወከፍ፥ በኅብረትም፡ በኃላፊነት ከመጠየቅ ሊድኑ እንደማይችሉ፡ የቅርቡ ጊዜ ትዝታ፡ በማያጠራጥር መልክ፡ ኹሉንም ያስታውሳል።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላካዊ መመሪያ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ዘንድ፡ እንዲህ፡ በየአግጣሚው፡ በገሃድ ተሸሮ፡ በእርሱ ፋንታ፡ የሓሳዊው የዲያብሎስ ትእዛዝ እንዲሠለጥን በመደረጉ፡ *"እናንት ግብዞች! ኢሳይያስ፡ ስለእናንተ፡ 'ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን፡ ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የኾነ ትምህርት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል!' ብሎ በእውነት ተናገረ!"* ያለው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ሕያው መልእክት፡ ዛሬም፡ ለዚህ ትውልድ፡ መለኮታዊ ተግሣፅ ኾኖ ቀርቦለታል።[፲፴]

## ኢትዮጵያ፡ ስለአልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ስትፋረድ!

የሥልጣን ይዞታቸውን ለማጽናት በሚጠበቡ ባለጊዜዎችና በትረ መንግሥት ለመያዝ በሚሩዋሩዋጡ የሥልጣን ጥመኞች፡ የፍልሚያ መሰናዶ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዐፅም ላይ የተካኼደው፡ የመጠቀሚያና የማስመሰል ሥርዓት፡ ቀደም ብሎ፡ በሰዎች እጅና ቁጥጥር ሥር ወድቀው ይንገላቱ በነበሩት፡ በልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንም ላይ፡ በዕረፍታቸው ጊዜ ብቻ ሳይኾን፡ ገና፡ በሕይወተ ሥጋ፡ በሕመም ተዳክመው እያሉ እንኳ፡ ያለርኅራኄ ሲፈጸምባቸው ታይቷል። ይኸውም፡ በሕመማቸው ምክንያት፡ "ወደቤተ ክርስቲያን ሊመጡ አይችሉም!" እየተባለ፡ ነገር ግን፡ በዚያ አሳዛኝ ኹኔታቸው፡ በየስብሰባው አዳራሽና በየቤተ ነግዱ (የHotel) ዝግጅት፡ በተሽከርካሪ ወንበር እየተገፉ፥ እዚያም፡ ከመቆየት የተነሣ፡ በድካም እየወደቁ፡ ለሥልጣን ጥመኞቹ ዓላማ ማራመጃ፡ በመሣሪያነት እንዲያገለግሉ መደረጉ ነበር።

በዕረፍታቸው ጊዜ የኾነውም፡ ይህንኑ የመሰለ ነበር። በዚያ በአሜሪካ አገርና ቀደም ብሎ፡ በእንግሊዝ አገር ሣሉ፡ በሕመማቸው ጊዜ፡ እንኳንስ ሊጠይቃቸው ይቅርና፡ ዘወር እንኳ ብሎ ሊያያቸው ያልፈለገው፥ ከእርሳቸውም ጋር ግንኙነት ያለው መስሎ ላለመታየት፡ ጥረት ሲያደርግ የኖረው ኹሉ፡ ጳጳሳት የተባሉት የቤተ ክህነት ሰዎች ሳይቀሩ፡ አልጋ ወራሹ "ዐረፉ" ተብሎ፡ አስከሬናቸው፡ በቤተ ክርስቲያን መቀመጡ ሲታወቅ፡ አሁንም፡ ለታይታና ለየራሱ ዓላማ ማራመጃ ሲል፡ ከየግዛቱ የተሰባሰበው ሰው ብዛት፡ ቤተሰቡን፡ የሚያጽናና ከመኾኑ ይልቅ፡ የሚያሳዝናቸውን አስተዛዛቢ ኹኔታን መፍጠሩ ይታወሳል።

## የአንድ መነኩስ/ጳጳስ፡ ሌላው አሳዛኝ ግብር።

ከእነዚህ ኹኔታዎች መካከል፡ ለምሳሌ ያህል፡ አንዱን እጠቅሰዋለሁ፤ ይህም፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ ቤተ ክህነቱንና መንፈሳዊዉን ጉዳይ በሚመለከት፡ የቤተ ምልክናው (የቤተ መንግሥቱ) ዋና ተጠሪ ኾነው ሲያገለግሉ የኖሩት፡ ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ የተባሉት መነኮሴ የፈጸሙት ይኾናል።

እኙህ መነኩስ: በደርግ አገዛዝ ታሥረው ከተፈቱ በኋላ: በዚያው የደርግ መንግሥት: በቤተ ክህነት ውስጥ: በተለያዩ የሥራ መደቦች÷ ኋላም: በጵጵስና ደረጃ ተሹመው ሲያገለግሉ ሣሉ: በመልእክተኛነት: ወደውጭ አገር መመላለስ እንደጀመሩ: ወደእንግሊዝ አገር መጥተው ኖሮ: ይህንኑ: በለንደን ከተማ ይኖሩ የነበሩት: ሕመምተኛው ልዑል አልጋ ወራሽና ባለቤታቸው ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ: ከነቤተሰባቸው ሰሙ:: መነኮሴው: የቤተ መንግሥቱ የቅርብ አገልጋይ በነበሩበት: በአጼ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ: ለእነርሱም የነበራቸውን ቅርበት በማስታወስ: "መቼም: እዚህ ድረስ ከመጡ: ምንም ቢኾን: እኛንም ሳይጠይቁን አይቀርም!" ብለው ተማምነው: በናፍቆትና በጉጉት ቢጠብቋቸው: መነኮሴው: በአካል መምጣታቸው ቀርቶ: ስልክም እንኳ የማይደውሉ ኾኑ! ዐረፉበት ቦታ ስልክ: ቢደውሉላቸውም: "ዛሬ: እኔንና እናንተን የሚያገናኘን ምንም ምክንያት የለም!" በሚል ቁርጥ ቃል: ነገሩን ዘጉት::

በዚህ ነገር: ቤተሰቡ እጅግ አዝነው: ያው: የቆዩበትን: የሕመም÷ የትካዜና የስደት ኑሮአቸውን ቀጥለው ሣለ: ለኹሉ: እንደየሥራው የሚከፍለው: እውነተኛው ዳኛ: እግዚአብሔር: ጊዜያዊ ፍርዱን በመስጠቱ: ደርግ: ከአገዛዙ ሥልጣን ወርዶ ሲባረር: እኙህም መነኩስ: ለጵጵስና ካበቃቸው ደርግ ጋር: ከሥልጣናቸው ተባርረው: ወደአሜሪካ ተሰደዱ:: አልጋ ወራሽ: ቀደም ብለው: ከነቤተሰባቸው: ወደዚያ አገር ተዛውረው: በአሜሪካ ይኖሩ ስለነበረ: በዚያን ጊዜም: "እስቲ: አሁን እንኳ ብቅ ብዬና ይቅርታ ጠይቄ ላጽናናቸው!" አላሉም:: ነገር ግን: ከአያሌ ወራት በኋላ: በኢትዮጵያ: የዘውድ መንግሥታዊ ሥልጣንን ለመያዝ እርስ በርሳቸው ከሚናቆሩት: የአጼ ኃይለ ሥላሴ ቤተሰባዊ አንጃዎች መካከል አንዱ: በመሣሪያነት ሊጠቀምባቸው: አስፈላጊውን አዘጋጅቶ: ወደአልጋ ወራሹ ዘንድ: በአማላጅነት እንዲኼዱላቸው በጠየቃቸው ጊዜ: ከምዕራቡ የአሜሪካ ጠረፍ: ከካሊፎርንያ ተነሥተው: ወደምሥራቃዊው ጠረፍ: ወደዋሽንግተን ዲ.ሲ. መጡ:: ይኹን እንጂ: አመጣጣቸው: ለበጎ ሳይኾን ለክፉ በመኾኑ: በመንገዳቸው ሳይቀናቸው ቀርቶ: ዓላማቸው ከመስነካከሉ በላይ: በዚያ ጉዳይ: ቤተሰቡ: እርሳቸውንም ኾነ ሌሎቹን መገናኘት የማይፈልግ መኾኑን አስታውቋቸው: አዝነው ተመለሱ::

ሕመምተኛው አልጋ ወራሽ: በሕይወተ ሥጋ ሣሉ: እንዲያዩዋቸው ጓጉተው ቢያስጠሩዋቸውም: እንኳንስ ኼደው ሊጠይቋቸው: በስልክ ለማነጋገር: ፈቃደኛ ሳይኾኑ የቀሩት: እኙሁ መነኩሴ: ተከታትሎ በደረሰው: በአልጋ ወራሽ ዕረፍት ምክንያት: በቤተ ክርስቲያን በተዘጋጀው ሥርዓት ላይ: ያው ላስለመዱት ታይታ: ያለይሉኝታና ያለፍርሐት ቢገኙም: የጠበቁትን የማዕርግ ቦታና የጸሎተ ፍትሐቱን መሪ ተካፋይነት እንዳይዙ ተከልክለው: በኃፍረት ተሰናብተዋል::

## የአጼነቱ መለኮታዊ ሥርዓት:
## በሰዎች ሕገወጥ አሠራር: ሊፋለስ አይችልም::

እዚህ ላይ: ልዑል መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴን በሚመለከት: ሊወሱ የሚገባቸው ቁም ነገሮች አሉ:: እነዚህም: የቀዱሱን ኪዳን ሃይማኖታዊ ሥርዓት መፋለስን የሚያመለክቱ: ሕገ ወጥ ድርጊቶች ናቸው::

ልዑል አልጋ ወራሽ: አባታቸው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: ገና በሥልጣን ላይ እያሉ: በድንገተኛ ሕመም: የአልጋ ቁራኛ መኾናቸው ሲረጋገጥ: ለአልጋ ወራሽነትም የማይበቁ መኾናቸው ታውቆ: በአሁኑ ጊዜ: በራስተፈሪያውያን የአምልኮ ልማድና ቁጥጥር ሥር በመታፈናቸው: የሃይማኖት፥ የአእምሮና የአካል ስንኩል ከመኾን የደረሱት ልጃቸው: ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ: የአልጋ ወራሽነቱን መብት: በአዋጅ እንደተረከቡ ይታወሳል:: ከዚህ ጋር: አንድ ኢትዮጵያዊ: ብቁ ነው ተብሎ: ቅብዓ መንግሥት ተቀብቶና ዘውድ ተቀዳጅቶ: በዙፋን ላይ ከተቀመጠ በኋላ: የአጼነቱን ስያሜ ለማግኘት: በቤተ ክርስቲያን የሚከናወን: ራሱን የቻለ ታላቅ ሥርዓት እንዳለ፥ በዚያም ሥርዓት ላይ: ከቤተ ሕዝቡ፥ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናው ወገኖች: የሚወከሉት ተጠሪዎችና አባሎች ተገኝተው: ሥርዓቱን ሊያስፈጽሙ እንደሚገባ በይፋ ይታወቃል:: ይህም: ቀደም ብሎ በሠፈረው በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ውስጥ ተብራርቷል::

ሥርዓቱ: በጥቂቱ የሚጠይቀው እነዚህን ግዴታዎች ሲኾን: ከላይ በተገለጸው ኹኔታ ላይ የሚገኙትን፥ ከዚያም አልፎ: በሕክምና ሊፈወስ ባልቻለ ጽኑ ሕመም የደከሙትን ሰው: "ግርማዊ ቀዳማዊ አጼ አምኃ ሥላሴ" ተብለዋል ብሎ ያወጀው ማነው? ቤተ ሰቦቻቸው? ወይስ: እንደአጼ ኃይለ ሥላሴ እያመለኳቸው ይጠብቋቸው የነበሩት: "ራስተፈሪያውያን ናቸው"? ወይስ ሌላ ማነው? በሕይወተ ሥጋ ሣሉም ኾነ: በዕረፍታቸው ጊዜ: ይህን የሥልጣንና የማዕርግ ስያሜ ተቀብለውና አጽድቀውላቸው የነበሩት: የቤተ ሕዝቡና የቤተ ምልክናው፥ በተለይም: የዚህ ጉዳይ ባለአደራ የኾነችው: የቤተ ክህነቱ ተጠሪዎች "ነን" የሚሉት: በውጭ አገር በስደት የሚኖሩት፥ በአገርም ውስጥ ተደላድለው የሚኖሩት: እጨጌውና ጳጳሳቶቻቸው ጭምር: ይህን ጉዳይና ድርጊት በሚመለከት: ዛሬና ወደፊት: ምን ይላሉ? ከእነርሱስ መካከል: በዚህ ነገር ተካፋዮች የኾኑ አሉን? ካሉ: ድርጊታቸውን: በይፋ ለምን አያስረዱም? አለዚያ: በሚጠየቁበት: መጠየቃቸው አይቀርም!

እንግዴህ: ለዚህ ጉዳይና ድርጊት ተጠያቂው ማነው? ቤተ ሕዝቡ ነበራ!? ነገር ግን: አልኾነም:: ይኹን እንጂ: በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ: እንደራሴያቸውን መርጠው ለሚሾሙትና ለሚያስቀምጡት: ለባለቤቱ ንጉሠ ነገሥትና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስና ለንግሥት እናቱ ድንግል ማርያም: ይህን ጉዳይና ድርጊት በሚመለከት: የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው አባል የኾነ ኢትዮጵያዊ: ሴትም ኾነች ወንድ: እያንዳንዱ: በግል፥ ኹሉም በጋራ: በጊዜው: በመንፈስና በእውነት: ከፊታቸው በግንባር እየቀረበ: ምላሹን ይሰጣል::

በተለይ: በዚህ ጉዳይ ላይ: የቤተ ክህነቱን ተጠሪዎች: እጨጌውንና ጳጳሳቱን በሚመለከት: የሚተላለፈው መልእክት: እንዲህ በሚለው: በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ይጠቃለላል:- *"እናንተ ግብዞች! የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ፥ የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡና 'በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በኾነስ: በነቢያት ደም ባልተባበርናቸውም ነበር' ስለምትሉ: ወዮላችሁ! እንግዲያስ: የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደኾናችሁ: በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ:: እናንተ ደግሞ: የአባቶቻችሁን መሥፈሪያ ሙሉ! እናንተ እባቦች! የእፉኝት ልጆች! ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?"*[፲፴]

## ኢትዮጵያ፡
## ሥርዓተ ሢመተ ጵጵስናን
## ስትፋረድ!

እንግዴህ፡ ዛሬ ባሉት ጳጳሳት ተግባር የማልደነቀውና ስለእነርሱም ኾነ፡ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ "እንዲህ ቢኾን፥ እንዲህ ቢደረግ ይሻላል!" የምለው፡ ያለምክንያት አይደለም፡፡ እነርሱ፡ ጳጳሳቱ፡ ሥጋ ለባሽ ሰዎች ስለኾኑ፡ ባለማወቅም፥ በማወቅም፡ ሊሳሳቱና ሊያጠፉ ይችላሉና፡ "የአገራችን፥ የሃይማኖታችንና የቤተ ክህነታችን ጉዳይ፡ ለእነርሱ ብቻ ሊተው አይገባም! አደገኛ ነው! ስለዚህ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ በኢትዮጵያዊነት የቃል ኪዳን ሃይማኖታውያንና መንፈሳውያን ይዞታዎቹ፥ ውርሶቹና ቅርሶቹ ጥበቃ በኩል፡ ታላቅ የኃላፊነት ድርሻ ስላለው፡ ግዳጁን ይፈጽም! እለዚያ፡ እያንዳንዱ የቤተ ሕዝቡ አባል፡ ሴትም ኾነች ወንድ፡ በሕሊናው፥ በአገሩና በእግዚአብሔር ፊት፡ በኃላፊነት መጠየቅ አይቀርምና፡ በዚያን ጊዜ፡ ስለሚሰጠው መልስ፡ እንዳይቸገርና እንዳይጸጸት ከአሁኑ ይጠንቀቅ!" እያልኩ አሳብ የማቀርበውና የማሳስበው እኮ! በማውቀው፥ ባየሁትና በደረሰብኝ እንጂ፡ እንዲያው ዝም ብዬ በመላምት፥ በዳበሳና በስሜት አይደለም፡፡

ጳጳሳቱ፡ ዋና ተሣታፊዎች ኾነው በተቀመጡበትና አጼው በሚመሩት፡ በዚያ፡ ቀደም ብሎ በተገለጸውና ስለቤተ ክህነት ጉዳይ፡ በተሰበሰበው ታላቅ ጉባኤ ላይ፡ እንደሥርዓቱ ከኾነ፡ እነርሱ እያሉ፡ እኔ መናገር አልነበረብኝም፡፡ በፍርሃቱና በሥጋቱም በኩል ከኼድን፡ ከእነርሱ ይልቅ ልፈራና ልሠጋ የሚገባኝ፡ እኔ ነበርኩ፤ ምክንያቱም፡ ሚስትና ልጆች ያሉኝ፡ ዓለማዊ፡ ማለትም፡ እንደነርሱ ገዳማዊ መነኵስ ሳልኾን፡ በኅብረተሰቡ መካከል የምኖር ባለትዳር ካህን ስለኾንኩ ነው፡፡

እነርሱ ግን፡ "ድንግላውያን መነኰሳትና ገዳማውያን ባሕታውያን" ስለኾኑ፡ ሌላውን ዓለማዊውንና ሥጋዊውን ነገር ኹሉ ንቀው ስለተዉት፥ ራሳቸውንም፡ በምንኵስና ሠይፍ ገድለው፡ ከምድራዊው ወደሰማያዊው ሕይወት ስለተሸጋገሩ፡ "እንግዴህ፡ በዚህ ዓለምና ለሕይወተ ሥጋቸው፡ ምንም የሚፈልጉት፥ ምንም የሚፈሩት ነገር የለምና፡ ስለእግዚአብሔር እውነት፥ ስለቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት፥ ስለቤተ ክህነት፡ ማለትም፡ ስለካህናትና ምዕመናን ደኅንነት፡ እስከሞት ድረስ ታማኞች ኾነው ያገለግላሉ" ተብሎ ነበር፡ በዚያ መንበር ላይ፡ ራሳቸው የተቀመጡት! እንዲቀመጡም የተደረገው! ነገር ግን እንደታሰበውና እንደሚገባው ኾነው እንዳልተገኙ፡ ይኸው፡ በዚያ ጉባኤ ላይ በኾነውና እስከዛሬ በይፋ በሚያካኺዱት ድርጊቶቻቸው ታየ! እየታየም ነው፡፡

### ጵጵስናን፡ ለመነኰሳት ብቻ ወስኖ የሰጠ ማነው?

ታዲያ፡ ለምንድር ነው፡ በዚህ፡ ግብፃውያን ባሸከሙን ከባድ ቀምበር፡ ራሳችንን ጠፍረን፡ ስንሠቃይ የምንኖረው? ይህ ሥርዓት፡ ከእኢሁ፡ ከባዕዳኑ ግብፃውያን ጨቋኞቻችን ያመጣነው ዕዳ እንጂ፡ ጥንቱንም ቢኾን፡ የእኛ፡ የኢትዮጵያውያን አይደለም፡፡ እነርሱም፡ እስከዛሬ ድረስ ሲያደርሱብን የኖሩት አንሶ፡ ይኸው ዛሬም፡ በደሉንና ግፉን፡ በኢየሩሳሌም ይዞታችን ላይ በገሃድ ሲፈጽሙብን እናያለን፡፡

በእኛ፡ በኢትዮጵያውያኑ ጥንታዊ ሥርዓት፡ የሊቀ ካህናትነቱ ሥልጣን የተመሠረተው፡ በኋላ በመጣው፡ በምንኵስና ላይ ሳይኾን፡ ቀደም ብሎ በነበረው፡ በድንግልና፥ በብሕትውናና በጋብቻ ላይ እንደኾነ፡ ሕያው የኾነው ዜና መዋዕላችን ያረጋግጥልናል፡፡ ይህም፡ በዘመነ ብሉይ፡ በእነመልከ ጼዴቅ፥ በእነዮቶር፥ በእነሙሴና ሚስቱ ሲጳራ፥ በእነ አሮንና በእነንግሥት ማከዳ፥ በዘመነ ሐዲስ ደግሞ፡ የአኵሱሙ ሊቀ ካህናት፥ ንቡረ እድና እጨጌ በነበረው፡ በእነእንበረም፥ ከእርሱ በፊትና ከእርሱ በኋላ በተሾሙትም፡ ሊቃነ ካህናት ሕይወት ይታወቃል፡፡

በዘመነ ክርስትና፡ የኋላ ኋላ፡ በ፩ኛው ምዕት ዓመት፡ ወደአገራችን የገባውና ከግብፃውያን ያገኘነው ምንኵስናም፡ እንደጌታ ቃል፡ በየግላቸው ለተመረጡትና ለተጠሩት የሚገባ፡ የቅድስናና የገድል ሕይወት ሲኾን፡ "ዕዳ፥ ቀምበር" ያልኩት፡ ምንኵስናውን ሳይኾን፡ በሰዎች ሥርዓት፡ በእርሱ ላይ ብቻ እንዲመሠረት የተደረገውን፡ የጵጵስናውን ሢመት ነው፡፡ ዓቢዩ ጥያቄ፡ "የጵጵስናው ሹመት፡ ለምን፡ ለመነኰሳት ብቻ ይኾናል?" በሚለው ነጥብ ላይ ይመሠረታል፡፡ ለዚህም፡ በዋቢነት የሚቀርቡት ማስረጃዎች፡ የራሱ የአምላካችን ቃላት ናቸው፡፡

እግዚአብሔር፡ ጥንት በፍጥረት መጀመሪያ፡ በአዳምና ሔዋን መሥርቶት ያገኘነውና እርሱም እንድንጠብቀው ያዘዘን፥ ኋላም፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ሰው ኾኖ፡ ያጸናው፡ የአንድ ወንድንና የአንዲት ሴትን ጋብቻን እንጂ፡ ምንኵስናን አይደለም፡፡ ይህንኑም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለጋብቻ አንድነትና ጽናት አብራርቶ ካስተማረ በኋላ፡ ፍቺ እንዳይኖር በማስጠንቀቅ፡ ለቶናገረው ቃል፡ ደቀ መዛሙርቱ ሳይቀሩ ተጨንቀው፡ *"የባልና ሚስት ሥርዓት እንዲህ ከኾነ፡ መጋባት አይጠቅምም!"* ሳሉት፡ መልሱን የደመደመው፡ *"ይህ ነገር፡ ለተሰጣቸው ነው እንጂ፡ ለኹሉ አይደለም፤ በእናታቸው ማሕፀን፡ ጃንደረቦች ኾነው የተወለዱ አሉ፤ ሰውም የሰለባቸው፡ ጃንደረቦች አሉ፤ ስለመንግሥተ ሰማያትም፡ ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ፤ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው!"* በማለት፡ በሚገባና በሚበቃ ገላልጾታል፡፡ እንግዴህ፡ "ከእርሱ፡ ከመለኮት ቃል፡ የበለጠ ቃል፥ ከእርሱ፡ ከመለኮት ሥርዓትም[198] የበለጠ፡ ሥርዓት አለ!" ሊል የሚችል ደፋር፡ ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡

ጵጵስናን፡ ለመነኰሳት ብቻ የወሰኑት ሰዎች፡ ምን ማለታቸው ነው? ምንስ ማድረጋቸው ነው? እግዚአብሔር የሠራውን፡ የጋብቻን ሥርዓት፡ ማቃለላቸው ነውን? ወይስ መናቃቸው ነውን? ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከብዙዎቹ ደቀ መዛሙርቱ መካከል፡ ለሐዋርያነት የመረጠው፡ ዮሐንስንና እርሱን የመሰሉትን ድንግላውያንን ብቻ አልነበረም፡፡ ታዲያ፡ ሚስት ካላቸው ባለትዳሮች መካከል፡ ቅዱስ ጴጥሮስን፡ ለሐዋርያነት ብቻ ሳይኾን፡ የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ ያህል ላስገኘለት፡ ለሊቀ ሐዋርያነት ጭምር፡ እንዴት፡ ወይም ለምን፡ መረጠው? ጵጵስና፡ ለድንግላውያን ወይም፡ ለመነኰሳት ብቻ ቢኾን ኖሮ፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ ይልቅ፡ በፍቅሩም ስለሚቀርበው፡ "ፍቁረ እግዚእ" የተባለውን፡ ዮሐንስን፡ ለምን አልመረጠውም? "ጵጵስና የሚገባው፡ ለመነኰሳት ብቻ ነው" የሚሉ ወገኖች ካሉ፡ እነዚህ ወገኖች፡ ጌታን፡ "የእኛ ሥርዓት ካንተ ይበልጣል" ማለታቸው ነውን?

*"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ"* ብሎ: ራሱን የሚጠራው፥ ራሱም: በድንግልና የኖረውና "እንደእኔ ብትኾኑ ይሻላችኋል" እስከማለት የደረሰው ጳውሎስ እንኳ: በመንፈስ ቅዱስ ተመልቶ: በጻፋቸው መልእክቶቹ: ስለዚህ ጉዳይ የሰጠውን መመሪያ እንስማ!

*"'እሙን ነገር: ዘይፈቅድ ይሠየም ጳጳሰ!' ሠናየ ግብረ ፈተወ:: ወባሕቱ ርቱዕ: ይሠየም ጳጳስ: ዘኢያደሉ ለገጽ፥ ዘአልቦ ምክንያት፥ ዘአሓተ ብእሲተ አውሰበ!" ማለትም: "'ማንም: ጵጵስናን ቢፈልግ: መልካምን ሥራ ይመኛል' የሚለው ቃል የታመነ ነው:: እንግዲህ: ጳጳስ: ሊኾን የሚገባው ሰው: የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሠራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ነገር ግን ገር የኾነ፥ የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድድ፥ በኹለንተናቸው ንጹሓን ኾነው የሚታዘዙ ልጆች ያሉት፥ ቤተሰቡን: በመልካም ሥርዓት የሚያስተዳድር ሊኾን ይገባዋል! ቤተሰቡን: በሥርዓት ማስተዳደር የማይችል ሰው: የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን: እንዴት ሊጠብቃት ይቻለዋል? በትዕቢት ተነፍቶ: በዲያብሎስ ወጥመድ እንዳይወድቅ: አዲስ ክርስቲያን አይኹን! ደግሞም: በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድ እንዳይወድቅ: በውጭ ባሉት ሰዎች ዘንድ: መልካም ምስክርነት ያለው ሊኾን ይገባል::"*[፻፴፭]

ታዲያ፥ እንዲህ ከኾነ: እኛ: ኢትዮጵያውያን: ከእግዚአብሔር ያገኘነውንና የራሳችን የኾነውን መለኮታዊ ሥርዓት: ባዕዳን አጥቂዎቻችን በኾኑት በግብፃውያን ሥርዓት ስንለውጠው: "እነርሱ: ከእነቅዱስ ጳውሎስ በላይ ያውቃሉ! እኛም እናውቃለን!" ማለታችን ነውን? ራሱ: ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ: በዓለሙ ኅብረተሰብ መካከል ተወልዶና አድጎ በየከተማው ሳይቀር: እየኖረ ማስተማሩ፥ ሐዋርያቱንም: ከገዳማውያንና ከባሕታውያን ሳይኾን: ከዚያው ኅብረተሰብ መካከል መምረጡ: ለምን ይመስለናል? ቅዱስ ጳውሎስስ: ግልጽ አድርጎ: *"ጳጳስ ኾኖ የሚሾመው ሰው: የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን: ሊጠብቃትና በሥርዓት ሊያስተዳድራት ይችል ዘንድ: የአንዲት ሚስት ባል የኾነ፥ በኹለንተናቸው ንጹሓን ኾነው የሚታዘዙ ልጆች ያሉት፥ ቤተሰቡን: በመልካም ሥርዓት የሚያስተዳድር ሊኾን ይገባዋል!"* ለምን አለ?

አንድ ጳጳስ: በዓለሙ ውስጥ የሚኖረውን እያንዳንዱን ግለሰብ፥ ከዚያም: ጋብቻን፥ የባልና ሚስት ኑሮን፥ ማለትም: የትዳርና የቤተሰብ ሕይወትን፥ በአጠቃላይም: ኅብረተሰብን በሚመለከት: ያለውን: ውሳጣዊና አፍአዊ ችግር: በቅርብ የሚያውቅና የሚረዳ፥ ከዚህም የተነሣ: ለችግሩ መፍትሔን ሊያገኝ የሚችል እንዲኾን በማሰብ መኾኑን: ማንም ተመልካች በቀላሉ ሊገነዘበው አያዳግትም::

ዳሩ ግን: እግዚአብሔር: እንዲህ አድርጎ የሠራውን ፍጹም ሥርዓት: ሰዎች: ለራሳቸውና በእነርሱም አማካይነት: ለዲያብሎስ በሚስማማ መንገድ በመለወጥ: ከላይ ስለተጠቀሱት: ስለግለሰብ፥ ስለትዳርና ስለዓለማውያን ኅብረተሰብ አኗኗርና ችግር: ምንም የማያውቁትን፥ ራሳቸውን: ከሰውና ከኅብረተሰብ ለይተው: የብሕትውናን ዝግ ሕይወት፥ በበረሃም የገዳማዊነትን መንፈሳዊ ኑሮ መርጠው የተቀመጡትን ሰዎች: ከበዓታቸው እያወጡ: እነርሱን ብቻ: ለጵጵስና ሹመት ማብቃት: "በእርግጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው" ብሎ ለመቀበል: ለሃይማኖታዊ ሰውነት: እጅግ ይከብደዋል::

እንግዴህ: ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተጠቅሰው: ከዚህ በላይ: በግልጽ በቀረቡት አምላካውያት ቃላት መሠረት: መጀመሪያ: በራሱ በእግዚአብሔር ተመሥርቶ፥ ኋላም: ራሱ: እግዚአብሔር ወልድ: በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ባጸናው፥ ተያይዞም: ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው እያለመለሙት በቀጠለው የኢትዮጵያውያን ሥርዓት: የጵጵስና ሹመት: ለመነኩሳት ብቻ ሳይኾን: ሥልጣነ ክህነት ላላቸውና ለመንበሩ ብቁ ኾነው ለሚገኙ: ሕጋውያን ጭምር: ለኹሉም ክፍት ኾኖ ሊፈቀድ ይገባል::

## ኢትዮጵያ:
## በጦር ኃይል ድርጅት የሚያምኑ ልጆቿን
## ስትፋረድ!

በምዕራቡ ፍልስፍናና ሥርዓት የተቋቋመው: የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ድርጅት: በዘመናዊው መልክ እየተሻሻለና እጅግ እየገዘፈ እንዲሄድ መደረጉ፥ እንዲሁም: በውጭው ብቻ ሳይኾን: በውስጥም: በየክፍሉና አንዱ በሌላው ላይ: እርስ በርስ: ምሥጢራዊ ጥበቃና ክትትል እንዲያካኺዱ የተዘረጉት የሰላ አውታሮች: አገልግሎታቸው: በየጊዜው እየተራቀቀና እየተስፋፋ እንዲቀጥል ያለገደብ መለቀቁ: እነዚህ ኹኔታዎች: ከቅዱሱ ኪዳን መሠረታውያን የእምነት ሥርዓቶች ጋር የሚቃረን: ከባድ ድርጊት እንደተፈጠረ በጉልህ ከሚያስረዱት ምልክቶች መካከል ጐልተው የሚታዩት ነበሩ::

## ለጸጥታና ለጦር ዝግጅት የፈሰሰው ገንዘብ
## ያስገኘው መራራ ፍሬ::

ይህ ተቃርኖ ሊፈጠርና ሊከሠት የቻለው: ቅዱሱ ኪዳን: የሕዝቡን: ኹለንተናዊ ደኅንነት፥ ጥበቃና መከላከል: በተሟላ ዋስትና የሚያረጋግጠው: ሌላ ረዳትን ሳይሻ: በራሱ ብቻ: ማለትም: ምንጊዜም: ለጠላት በማይበገረው፥ ድል አድራጊና ምሉእ በኵለሄ (በኹሉ የመላ) በኾነው: መለኮታዊ ጸጋውና መንፈሳዊ ኃይሉ በመኾኑ ነው:: የቅዱሱ ኪዳን የሃይማኖት ሥርዓቶች: በአንድ በኩል: የሰዎችን የሰላ ጥበብና የጦር ኃይል: የማያስፈልጉና የማይጠቅሙ፥ በአጠቃላይም እንዳልነበሩ የሚያደርግ: ረቂቅና ደምሳሽ የኾነ: የራሳቸው ጥበብና ኃይል አላቸው፤ በሌላው ወገን ደግሞ: ለእነዚያ: የሰዎች የሰላና የጦር ድርጅቶች: ተመድቦ የሚባክነውን: እጅግ በርካታና ከዓቅም በላይ የኾነ ከባድ የገንዘብ ወጪ: መቀነስ ብቻ ሳይኾን: የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወትና ሥጋዊ ኑሮ፥ ትምህርታዊ እውቀትና ማኅበራዊ ደኅንነት: ለማሻሻልና ለማሳደግ ሲባል: በቤተ ምልክናው በኩል: የሚወጠኑትን: የልማት ዕቅዶችና የምርት ተግባራት ማስፈጸሚያ እንዲውል የማድረግ ችሎታና ብቅዓት አላቸው:: የቅዱሱ ኪዳን የከበሩ ዓላማዎችና ተግባሮችም እነዚሁ ናቸው::

አጼ ኃይለ ሥላሴ ግን: ለመንግሥታቸው ደኅንነትና መረጋጋት፥ ለአገሪቱም: የውስጥና የውጭ ጠላት መከላከያ: በይበልጥ የተማመኑትና የተደገፉት: በስለላ ድርጅቶቻቸው አገልግሎትና በጦር ኃይሎቻቸው ትጥቅ ላይ ይመስል ነበር::

ለግል ሰውነታቸው መጠበቅና ለማይገሠሠው እጼነታቸው መከበር ሳይቀር፡ ዋናው መተማመኛ፡ "የእነዚህ አቋሞች መኖር ነው" ብለው ያምኑ ነበር። በእርሳቸው በኩል፡ በቅዱሱ ኪዳን መታመንና በእርሱ ላይ መደገፍ ከቀረ፡ ቆይቷል፤ ይህ ኹኔታም፡ በአያሌዎቹ የመንግሥታቸው መርሓ ግብሮችና የሥራ እንቅስቃሴዎች ውስጥ፡ በቀላሉ የሚታይ እውነታ ነበር።

እንግዴህ፡ ይህን የመሰለው ድርጊት፡ እያንዳንዱ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተፈጸመ፡ የክህደትና የርኵሰት ኃጢአት በመኾኑ፥ የኃጢአቱ ጽዋ ስለሞላና ያም፡ በንስሓ እንኳ እንዳይመለስ፡ የድርጊቱ ባለቤቶች ልቦና፡ በእምቢተኛነት ስለደነደነ፡ እውነተኛው ዳኛ እግዚአብሔር፡ የፍርዱን ቅጣት የሚፈጽምበት በትር አስፈለገው። ያም በትር፡ ሌላም አይደለ! ያው፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የራሳቸውን ሰብአዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያገለግላቸው ዘንድ፡ ራሳቸው፡ በምዕራባውያን ሥርዓት የወጠኑት፥ ያደራጁትና እያንከባከቡ ያኖሩት አቋም ኾኖ ተገኘ!

አዎን፥ ራሳቸው የፈጠሩዋቸው፡ እነዚያ የስለላ ድርጅቶቻቸውና እንዲሁም፡ የክብር ዘበኛ፥ የምድር ጦር፥ የአየር ኃይል፥ የባሕር ኃይል፥ የሕግ ዘበኛ (Police) እና የብሔራዊ ጦር የተባሉትን ዘርፎች የያዘው፡ የመከላከያ ኃይላቸው፡ ከባዕዳን ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመተባበር፡ ግዳጃቸውን በፍጹም አሟልተው አከናወኑ! ያም ግዳጅ፡ መሪያቸውና አዛዣቸው የኾኑትን፡ እርሳቸውን ራሳቸውን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን፡ ከነባለሥልጣኖቻቸውና ከመላዎቹ ሥራዎቻቸው ጋር ማስወገድና አገሪቱን ለውድመት፥ ሕዝቧንም ለእልቂት መዳረግ ነበር። ይህም፡ "ኢትዮጵያንና ሕዝቧን፥ ከነህብታቸውና ከነቅርሳቸው፡ ከጠላት ጠብቆና ተከላክሎ ሊያኖር ይችላል" ተብሎ የተቋቋመውና እምነት ተጥሎበት የኖረው፡ የራስ፥ የአገርና የወገን ድርጅት፡ "በሬ ከአራጁ ጋር ይውላል" እንደሚባለው፡ መልሶ፡ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ መጥፊያዋ ኾነ ማለት ነው።

## ኢትዮጵያ፡ የቲቶን ዩጎዝላቭያንና መሰሎቿን ስትፋረድ!

የቅዱሱ ኪዳን አገር የኾነችውን፡ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን፡ የወደፊት ዕድል ይወስኑ ዘንድ፡ የምሥጢር መረጃዎቿንና የቤት ውስጥ ጉዳዮቿን ጨምሮ ከማቅረብ ጋር፡ አስፈላጊው ሥልጣንና አደራ፡ በሙሉ ተሰጥቶ የነበረው፡ ከእግዚአብሔር-አልባ የጋርዮሽ አገሮች፡ በውልና በስምምነት ተመልምለው ለመጡ ባዕዳን ጠበብት ነበር። እነዚህም፡ መስኮብንና በተለይም፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ የቅርብ ምሥጢረኛ ወዳጅና በእግዚአብሔር-አልባ የጋርዮሹ (Communist ኮሚዩኒስት) ገዢ፡ በማርሻል ብሮዝ ቲቶ ትመራ የነበረችውን፡ ዩጎዝላቪያን የመሰሉት አገሮች ናቸው።

## የማይጣጣም፡
## የሃይማኖትና የምግባር
## እንቆቅልሽ፡፡

እኒያ፡ እግዚአብሔር-አልባ የጋርዮሽ ጠበብት፡ የቅዱሱን ኪዳን ሕዝብ ለመጣል፡ በአገሪቱ የህልውና ግንድ ላይ፡ የመገዝገዝ ተግባራቸውን፡ በሥውር ያካኺዱ የነበሩት፡ ቀድሞ፡ "ብሔራዊ የማቀጃ ምርፋቅ (Planning Board ፕላኒንግ ቦርድ)" ኋላ፡ በደርግ ጊዜ፡ "የዘመቻ መምሪያ" ይባል በነበረው መሥሪያ ቤት፡ ስምና ጥላ ሥር ነበር፡፡

ጠበብቱ፡ በእርግጥ፡ ዒላማቸው አድርገው፡ ዕቅዳቸውን ይነድፉና ይወስኑ የነበረው፡ የሕዝቡ ሕይወት፥ የአገሪቱም ህልውና፡ ጸንቶ የቆመበትን፡ የቅዱሱን ኪዳን መሠረትና አቋም፡ ከነአውታሮቹ፡ መነጋግለው ካፈራረሱ በኋላ፡ በዚያ ፍርስራሽ ላይ፡ የራሳቸው፡ የኾነውን፡ እግዚአብሔር-አልባ የጋርዮሽ ሥርዓት መሥርተው ለመገንባት በሚያስችላቸው ስልትና ግብ ላይ እንደነበረ መገመት፡ ለማንም አያዳግትም፡፡ ያም፡ ዓላማቸው ተሳክቶላቸው፡ እነሆ፡ ሀገረ እግዚአብሔር በተባለችው፡ በኢትዮጵያ ላይና ሕዝበ እግዚአብሔር በተባሉት ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ "እግዚአብሔር የለም" የሚል ሥርዓተ መንግሥት፡ በደርግ አማካይነት ተቋቁሞ፡ በግብር የተፈጸመውን፥ ከዚያን ጊዜ ጀምሮና ዛሬም እየተካኼደ ያለውን ድርጊት፡ ፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ በገሃድ እያየው ነው፡፡

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በቅዱሱ ኪዳን እምነት፡ *"ይብል ዓብድ በልቡ፡ 'አልቦ እግዚአብሔር!'"*፡ *"ሰነፍ በልቡ፡ 'እግዚአብሔር የለም!' ይላል"* የሚለውንና ዘወትር በሚደገመው፡ በዳዊት መዝሙር ጸሎት ላይ የሚገኘውን፡ ይህን ኃይለ ቃል እያወቁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያና የቃል ኪዳን ሕዝቧ፡ የወደፊት ህልውና፡ ምንና እንዴት ሊኾን እንደሚገባ፡ የዕድላቸውን አካኼድ እንዲቀይሱ፥ ፍጻሜውንም እንዲወስኑ፡ እንደነዚህ ያሉትን፡ "ሰነፎች" እንጂ፡ "ጠበብት" ሊባሉ የማይገባቸውንና በእግዚአብሔር ላይ በይፋ ያመፁትን ከሃዲዎች፡ በራሱ፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ ቀጥረውም ኾነ በእርዳታ ስም አምጥተው፡ ይህን የመሰለውን ኃላፊነትና አደራ መስጠታቸው፡ ዛሬም፥ ነገም፥ ወደፊትም፡ ለመቼውም ጊዜ፡ የማይጣጣም፡ የሃይማኖትና የምግባር [፻፴] እንቆቅልሽ ኾኖ ይኖራል፡፡

"እግዚአብሔር-አልባ የኾነው" ይህን የመሰለው ሴራና ወረራ፡ እንዲህ፡ በምሥራቅ በኩል፡ "ኅብረተሰባዊነት ወይም የጋርዮሽ ሥርዓት" (socialism/communism ሶሺያሊዝም/ኮሚዩኒዝም) በሚል የሽፋን መፈክር፡ "ሶቪዬት ዩኒየን" ይባል በነበረው፡ የመስኮብ ኅብረታዊ መንግሥት መሪነት ሲፈጸመብን፡ በምዕራብ በኩል ደግሞ፡ "ሕዝባዊ አገዛዝ" (democracy ዲሞክራሲ) በሚል ሌላኛ የሽፋን መፈክር፡ "ዩናይትድ ስቴትስ" በተባለው፡ በአሜሪካ ኅብረታዊ መንግሥትና በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን መሪነት፡ ሲካኼድብን የኖረው፡ "በገንዘብ አምልኮ ላይ የተመሠረተው" ሴራና ወረራ፡ እነሆ፡ አሁንም፡ እየተካኼደብን ይገኛል፡፡

እነዚህ፡ ኹለት፡ ተፃራሪ ወገኖች፡ በሥነ መንግሥትና በርእዮተ ዓለም እንደራሲዎቻቸው፥ በሃይማኖትና በወንጌል ስብከት ልኡካኖቻቸው፥ በዓለም አቀፍና በአህጉር አቀፍ አውታሮቻቸው፥ እንዲሁም፡ በግልና በማኅበር የንግድ ወኪሎቻቸው መሣሪያነት እየታገዙና እየተጠናከሩ፡ በምድር ላይ፡ የጋራ ደንቃራቸው ኾና፡ በማሰናከያነት የቆመችባቸውን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕያው መገለጫና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኖሪያ የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ የህልውናዋን ሕንፃ፡ ጉልላቱንና ጣሪያውን ብቻ ሳይኾን፡ ከዚያ ጀምረው እስከመሠረቱ ድረስ ጭምር፡ በሙሉ ለማፈራረስ፡ በተቀነባበረ ዕቅድና በተባበረ ስልት ተነሣሡብን!

እኛ ግን፡ ይህን ኹሉ፡ የዲያብሎስ የኾነውን እኩይ ግብር አልተረዳንም፤ አሁንም የተረዳን አይመስልም፤ ከተረዳነውም፡ ለየራሳችን፡ የግል ዓላማ ማስፈጸሚያ፡ ልንጠቀምበት የምንችል እየመሰለን፡ እንታለላለን፤ እንሞኛለን፤ የቀደሙትም፡ ተጠምደው፡ ለውድቀት የበቁት፡ በዚሁ የምትሓት አስተሳሰብ እንደነበረ አናስተውልም፡፡

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ተቃዋሚዎች ጋር ወግነው በይፋ የፈጸሙት፡ ይህ የሴራ ተባባሪነት፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ላደረሱት፡ የርኵሰትና የክሕደት በደል፡ ሌላው፡ ግልጽና ተጨባጭ የኾነው ማስረጃ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ፡ በገንዘብ አምልኮ ላይ ከተመሠረተው ሥርዓት በኋላ፡ እግዚአብሔር-አልባ የኾነው የጋርዮሹ ርእዮተ ዓለምና እርሱ የፈጠረው ሥርዓተ መንግሥት፡ (ሥርዓተ መንግሥት ሊባል ከተቻለ ማለት ነው)፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ ዐይሉና ሰፍኖ መተካቱ፥ በመጨረሻም፡ ሥልጣን መያዙ፡ በምንም ሊያስደንቅ ከቶ አይችልም፡፡ እርሱዉም ቢኾን፡ ሥልጣን የያዘው፡ ያው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን፡ ተደክሞ የተሠራውን ኹሉ፡ በሙሉ አፈራርሶ ለማውደም ብቻ ኾኖ ተገኘ!፡

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የራሳቸውን ሰብአዊ ምኞት፡ ለማከናወን "ያስችለኛል" ብለው በመተማመን፡ አዘጋጅተውት የነበረው፡ ያው አንድ ዓይነቱ፡ የራሳቸው የብልሃት መሣሪያ፡ እርሳቸውና እርሳቸው የቀረፁት ዓመፀኛ ትውልድ፡ ቅዱሱን ኪዳን በማርከስ ረገድ ላደረሱት ኃጢአት፡ በመለኮታዊው ዳኝነት ተበይኖ የመጣባቸውን የመርገም ቅጣት፡ እንደገና ለማስፈጸም አገለገለ! እዚህ ላይ ግን፡ ልዩነቱ፡ ያ፡ የብልሃት መሣሪያ፡ መልኩን በእግዚአብሔር-አልባው የጋርዮሹ የስንፍና ፍልስፍና ለውጦ መቅረቡ ብቻ ነው፡፡

## ኢትዮጵያ፡
## የአጼ ኃይለ ሥላሴን ሕገ መንግሥት
## ስትፋረድ!

የራሱን ማንነት እንዳያውቅ ተከልክሎ፥ ራሱን፡ ከእውነተኛ ማንነቱ እንዲለይ፥ ባዕድ የኾነ ማንነትንም በግድ እንዲቀበል የተደረገው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ፡ "ሥራ ለሠሪው! እሾህ ላጣሪው" ነውና፡ በራሳቸው፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ላይ በዓመፅ ተነሥቶ፡ መንግሥታቸውን ሲያነዋውጸው ከቆየ በኋላ፡ በመጨረሻ፡ በሚያሠቅቅ ኃይል ሲገለባብጠው፡ የተጻፈ ሕገ መንግሥታቸውንም ጨርሶ ሻረው! ሕገ መንግሥቱ የፈጠራቸውንም አቋሞች፡ ከእርሱ ጋር አብሮ፡ ኹሉንም አስወገዳቸው!

ይህን የመሰለውን ቅጣት ያስከተለው ምክንያት ምን እንደኾነ ለማሳወቅ አያስቸግርም፤ መልሱ ግልጽ ነው:: ይኸውም፡ በዚያ ጽሑፍ ሕገ መንግሥት ውስጥ ከሠፈሩት አንቀጾች መካከል፡ አንዳንዶቹ፡ ከቅዱሱ ኪዳን መሠረታውያን ሥርዓቶች ጋር በገሃድ የሚቃረኑ ኾነው መገኘታቸው ነበረ:: ስለዚህ፡ ያ ሕገ መንግሥት፡ ታውጆና ጸንቶ፡ በተግባር ላይ እንዲውል መደረጉ፡ የቅዱሱን ኪዳን ግዴታዎች እንደመተላለፍ የሚያስቆጥር በመኾኑ፡ በሕገ መንግሥቱ ላይ ደርሶ የታየው የመድደምሰስ ጽዋ፡ ራሱ፡ የፍጻሜውን አይቀሬነትና ተገቢነት፡ በማያሻማ ኹኔታ አረጋግጦታል::

## መለኮታዊዉን ሕገ መንግሥት፡ ሰብአዊው አይተካውም::

ለፍጻሜ በበቃው፡ በአምላካዊው የትንቢት ቃል መሠረት፡ በኢትዮጵያ፡ ዐይሉና ሰፍኖ መገኘት ያለበት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ የልብ ጽላት ላይ፡ በአዲሱ ኪዳን ጸንቶ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጣቶች የተጻፈው፡ የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት እንጂ፡ ሰብአዊ አእምሮ የፈለሰፈውና በፍጡር እጅ የተጻፈው አይደለም:: አዎን፥ መለኮታዊዉን፡ ሰብአዊው፡ ሊተካው ከቶ አይችልም፤ አይታሰብምም:: ይህች እውነት፡ የእግዚአብሔር ስለኾነች፡ ኹሉም አበክሮ ሊያውቃትና በሃይማኖት ሊቀበላት ይገባል!

የጥንቱንና የማዕከላዊዉን ዘመናት ትተን፡ ባለፉት፡ ጥቂት ዓሠርተ ዓመታት ውስጥ በተከሠቱት፡ አያሌ የቁም ነገር ምልክቶች አማካይነት፡ እኛ ኹላችን፡ የዓይን ምስክሮች በመኾን ባየነው ኹሉ፡ የዚችን የእግዚአብሔርን እውነት፡ እርግጠኛነትና ትክክለኛነት ተመልክተናል:: ይኸውም፡ እስከዛሬና ዛሬ፥ ከዛሬም በኋላ፡ በኢትዮጵያ ምድር ሰፍኖ የኖረውና እየኖረ ያለው፥ የሚኖረውም፥ ደግሞም፡ በምንም ሰብአዊ ጥበብ፥ ገንዘብና ኃይል ሊበከል ያልተቻለው፡ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት፡ በሰው እጅ ያልተጻፈው፡ ያ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ፡ መንፈሳዊ ልቦና ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኘው፡ መለኮታዊው መኾኑን ነው::

ይህንንም እውነታ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ኾነ፡ ከእርሳቸው ወዲህ የታወጁትን፡ የሰዎችን ሕግጋተ መንግሥት ባለመቀበል፥ የደም መፋሰስ ንቅናቄን ሊፈጥሩና ወይም ሥርዓተ አልበኝነት እንዲነግሥ ሊያደርጉ የሚችሉ ኹኔታዎች በሚታዩባቸው ጊዜያት እንኳ፡ የቃል ኪዳኒቱ አገር፡ ኹለንተናዊ አንድነቷን፥ ሉዓላዊነቷንና ጽናቷን እንደጠበቀች፥ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቧን አቅፋ እንደያዘችና ሰንደቅ ዓላማዋን እንግባ እንዳውለበለበች፡ እነሆ፡ አሁንም፡ በህልውናዋ እየቀጠለች የመኼዷ ምሥጢር ብቻ፡ በማያጠራጥር መልክ ሊያስረዳና በሚበቃ ሊረጋገጥ ችሏል::

እነዚያ ኹኔታዎችና ጊዜያት፡ ሰብአዊው የመንግሥት አስተዳደር፥ ዳኛና የሕግ ዘበኛ እንኳ የሌለበት የቀውስ ማዕበል ተነሥቶባቸውና እነዚህ ኹሉ አቋማት ተሽረው፡ እንደሌሉ ተቆጥሮባቸው፥ በዚህም ምክንያት፡ "የእርስ በርስ ጦርነት ይነሣል!" ተብሎ ተፈርቶባቸው የነበሩት ኹኔታዎችና ጊዜያት ናቸው::

ለዚህም፡ በቅርቡ፡ የደርግ ኃይል ወድቆና ተሽሮ፥ በቦታው የተተካው፡ ጊዜያዊው መሸጋገሪያ መንግሥት፡ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት፥ ገና የኤርትራና የትግራይ ሽምቅ ተዋጊዎች ጦር፡ ያለተቃውሞ ወደአዲስ አበባ መናገሻ ከተማ ውስጥ እየገባ ሲመሽግና አሰሳ ሲያደርግ ሣለ፡ አገሪቱ፡ በዚህ መልክ፡ ባለቤት አልባ የመሰለችበትን ባዶ ጊዜና ኹኔታ፡ እዚህ ላይ፡ ምሳሌ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል። በዚያን ጊዜ፡ ታላቅ የሕዝብ ሁከትና ሽብር እንዲፈጠር፥ ግርግርና እልቂትም እንዲካኼድ በማቀድ ይመስላል፡ በግዙፋን የነዳጅ ጋኖች መካከል ይገኝ የነበረውን፡ ዋና የጦር መሣሪያና የፈንጂ ማከማቻ ግምጃ ቤት በማቀጣጠል፡ ኸን ተብሎ፡ የጠላትነትና የሽር ተግባር መፈጸሙ ይታወሳል።

## "ድርጊት፡ በውጤቱ ይጸድቃል!" የሚለውን ፈሊጥ፡ ኢትዮጵያ አትቀበለውም።

ከላይ በተከታታይ በቀረቡት ሐተታዎች ውስጥ እንደሚታየው፡ የሥነ መንግሥት ፈሊጠኞችና ምሁራን የሚያምኑበት፡ "የትም ፍጪው፥ ዱቄቱን አምጪው!" የሚባለውን የሚመስል፡ "ድርጊት፡ በውጤቱ ይጸድቃል" ("the end justifies the means") የሚለው ሰይጣናዊ ፍልስፍና፤ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ሳይሠራ መቅረቱ ብቻ ሳይኾን፡ በቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ ኃይል፡ ትርጉሙና ተልእኮው፡ ወደተቃራኒው አግጣጫ ተቀይሮ፡ በእርሳቸው ላይ ሠርቶ መገኘቱን መመልከት ነው። በዚህ ረገድ፡ እርሳቸው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የፈጸሙት የርኵሰት በደል፡ ምንም እንኳ፡ የበረከተ ቢኾንም፡ ይህንኑ ኃጢአታቸውን፡ በንስሓ ሊያጠራላቸው፡ ፈቃድና ኃይል ያለው፡ የመለኮታዊው ቃል ኪዳን ጸጋ፡ እስከዕረፍተ ሥጋቸው የመጨረሻ አፍታ ድረስ፡ የይቅርታ እጁን፡ በእርግጥ ዘርግቶ እንደጠበቃቸው ይታመናል። እኛም፡ ነፍሳቸውን በሰላምና በፍቅር ተቀብሎ፡ በገነት ያሳርፋት ዘንድ፡ ወደመሓሪው አምላካችን እንጸልያለን። እያንዳንዳችንም፡ የየኃጢአታችንን ስርየት፡ ከፈጣሪያችን እናገኝ ዘንድ፡ ንስሓ እንድንገባ እንደገና አሳስባለሁ።

የቅዱሱን ኪዳን ግዴታዎች ልዕልና በትክክል አለመረዳትና እነርሱን ካለማክበር የተነሣ የሚደርሰውን አስፈሪ ቅጣት በእርግጥ አለመገንዘብ፡ የቱን ያህል አሳሳቢ እንደኾነ አውቃችሁ፡ ተገቢውን ለመፈጸም መዘጋጀት፡ ለእርስዎ (ለምስተር ናፍታሊ) እና ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ፡ አሁንም ከባድ ሊኾንባችሁ ይችላል። ዳሩ ግን፡ በሰዎች ዘንድ፡ በተለይም፡ የኪነ ጥበብ ሥልጣኔ እየተራቀቀ በኼደበት፡ በዚህ ዘመን፡ ይህን የመሰለው፡ የንቀትና የእምቢተኛነት ምላሽ፡ በሰፊው ተናኝቶና ገንኖ እንደሚታይ፡ *የእግዚአብሔር እውነት፡* ከዚህ በታች በተጠቀሰው፡ የትንቢት ቃሏ፡ አስቀድማ የተናገረችው ያስረዳል።

ቃሉም እንዲህ ይላል፡- *"ለሥጋዊው ሰው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር አያስደስተውም፤ ሞኝነት እየመሰለውም፡ አይቀበለውም። የሚመረመረውም፡ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደኾነ፡ ሊያውቅ አይችልም። መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው ግን፡ ኹሉን ይመረምራል፤ እርሱን ግን፡ የሚመረምረው ማንም የለም። የእግዚአብሔርን ሕሊና የሚያውቅ ማነው? አማካሪውስ ማነው? እኛ ግን፡ የክርስቶስ ሕሊና አለን!"* [፻፹፪]

## ለመጨረሻው ትዝብት መጋለጥ

ይህ ሰፊ ምዕራፍ: በአንድ እውን ኹኔታ ይጠቃለላል:: እርሱም: የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት: በኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ላይ: ያን የመሰለ: የማፈራረስ አሳዛኝ ድርጊትን በሚያካኺድበት ጊዜ: ራሱን: በዓለም ፊት: ለትዝብት እንዲያጋልጥ፥ የማይዋጥለትንም ፍሬ: ሳይወድ በግድ እንዲቀበል ያደረገ፥ ባልታሰበ መልክና ከአልታሰበ አግጣጫ የመጣበት ኹኔታ ነበር:: ያም ፍሬ: ቤተ ክህነት: በመለኮታዊው ሥልጣን: ከበቀለችበት መንግሥታዊ አካሏ: በሰብአዊው ምሣር ተቆርጣ: አማናዊ ማንነቷን እያጣች መኼዷን ስታረጋግጥ: በአንድ ወገን: የልማት ባላደራ (commission) የተባለ ምርፋቋን አቋቁማ: የራሷን የሰው ኃይልና የሀብት ይዞታዋን እያዳበረች: በአገልግሎት ላይ ማዋሏን፥ በሌላው ወገን ደግሞ: ራሷን ችላ ለመተዳደር ያበቃትን: የሰበካ ጉባዔዋን: በቤተ ሕዝቡ አማካይነት: በያለበት እየመሠረተች: የምታካኺደውን አስደናቂ የሥራ ክንውን ከተመለከቱት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መካከል: አንዱ የኾነው: የዓለም ቤተ ንዋይ (World Bank): በዓመፁ ዋዜማ ላይ: በአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ፊት የደነቀረበት: የሚያፋጥጥ የውሳኔ አሳብ ነው::

የዓለሙ ቤተ ንዋይ: ይህን የውሳኔ አሳብ የመሠረተው: ከኹለተኛ ደረጃ አንሥቶ እስከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ (University) ድረስ ላለው ለከፍተኛው የትምህርት ዘርፍ ማስፋፊያ የሚውል: በእልፍ አእላፋት የሚቆጠር: ከፍተኛ የገንዘብ ብድርን እንዲሰጥ: ከኢትዮጵያ መንግሥት: ቀደም ብሎና በሰፊው ተጥንቶ በቀረበለት ማመልከቻ ላይ ነበር:: የውሳኔው አሳብ: እንዲህ በሚል ቃል ይገለጻል:- "የኢትዮጵያ መንግሥት: ሕዝቡን በቀላሉ ለማስተማርና አገሪቱን በአፋጣኝ ለማልማት: መላ ኢትዮጵያን: ከመኻል ከተማ እስከዳር አገር፥ ኅብረተሰቡንም: ከታች እስከላይ በማካተት: በሰፊው የተዘረጋ: ሙሉ የድርጅት አውታር ያላትን፥ በልምድ የደለበውንና በሙያው የደረጀውንም: በርካታ የሰው ኃይሏንም: በልማት ምርፋቋ አማካይነት እያሠለጠነች: በፍቱን መሣሪያነት: ለፍሬያማ አገልግሎት በማቅረብ ላይ የምትገኘውን: የኢትዮጵያን ቤተ ክህነት: እስከዛሬ ሳይጠቀምባት መቅረቱ: እጅግ ያሳዝናል:: አሁንም: የጠየቃችሁትን ብድር የምንፈቅድላችሁ: ይህን: የተከማቸ ድርጅትና ኃይል የምትጠቀሙበት የኾነ እንደኾነ ብቻ ነው!"

እዚህ ላይ በተጨማሪ: ተያይዘው የሚወሱ ቁም ነገሮች አሉ፤ እነዚህም:- ፩ኛ: ይህን የውሳኔ አሳብ: ለኢትዮጵያ መንግሥት መሪና ባለሥልጣኖች በማስረዳት: አሳምኖ ለማስፈጸም: በዚያን ጊዜ: የዓለሙ ቤተ ንዋይ ገዢ የነበሩት: ራሳቸው ምስተር ማክናማራ: አዲስ አበባ ድረስ እንዲመጡ መገደዳቸው፥ ፪ኛ: የውሳኔውን አሳብ: የምሉካኑ (ministers) ምክር ቤት ተቀብሎ: አጼ ኃይለ ሥላሴ ካጸደቁት በኋላ: በውሳኔው መሠረት የሚፈጸም ለመኾኑ: እኔ: በቤተ ክህነት ስም ኾኜ: ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር: ጽሑፍ ኪዳኔን (firma) ያሠፈርሁበት የስምምነት ሰነድ: ለዓለሙ ቤተ ንዋይ እንዲደርስ ማስፈለጉ፥ ፫ኛ: ይህም የማይበቃ ኾኖ: እኔ ጭምር: ከኹለቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች: ማለትም: ከትምህርቱ ምሉክ: ከአቶ ሠይፉ ማኅተመ ሥላሴና ከመካነ አእምሮው ሙሴ: ከDr. አክሊሉ ሀብቴ ጋር: በአካል: ወደዋሽንግተን ተጉዤና እዋናው መሥሪያ ቤት ተገኝቼ: ጽሑፍ ኪዳኔን: በመጨረሻው ሰነድ ላይ: አብሬ እንዳሠፍር መደረጉ ናቸው::

# ምዕራፍ ፲

## ኹለተኛው የዓለም ጦርነት:
## የመጣበት መልእክት:
## በመለኮት ዳኝነት::

እንግዴህ አሁን በመጨረሻ: ለዚህ አከራካሪ ጥያቄዎ መንሥዔ ምክንያት ስለኾነው ዝክረ ነገር: ወደማትትበት መድረክ ደረስሁ! ይኸውም: "አጼ ኃይለ ሥላሴ: ቅዱሱን ኪዳን ትተው: ከእርሱ ይልቅ: የጀኔቫውን የመንግሥታት ማኅበር ቃል ኪዳን በበለጠ በመተማመናቸውና በእርሱ በመማፀናቸው: በቀደመው: በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸሙት: የክህደትና የርኵሰት በደል የተነሣ: በሙሶሎኒ: የፋሺስት ጣልያን ሠራዊት ድል መኾንን አስከተለባቸው" የሚለው ሃይማኖታዊ የመደምደሚያ አስተያየት ነው::

### ኢትዮጵያውያን:
### የቅዱሱ ኪዳን ግዳጃቸውን ሲዘነጉ::

በዚህ መጽሐፍ ገጾች ላይ: በያለበት ተደጋግሞ እንደተገለጸው: ኢትዮጵያን: በመላው የህልውናዋ ዕድሜ ውስጥ: በጊዜው ከሚኖረውና በንስሓ ከማይመለሰው: ከሃዲ፥ ዓመፀኛና አመንዝራ ትውልዷ ጋር: ኹለቱንም: ለሥቃይና ለውድቀት የሚዳርጋቸው: አንድ ምክንያት ቢኖር: ምንጊዜም: በቅዱሱ ኪዳን: ለአምላካቸው: ለእግዚአብሔር: የመሐላ ቃላቸውን ሰጥተው: የገቡትን ውለታቸውን ቸል ብለው: ተቃዋሚ ወደኾነው: ወደባዕዱ ሲያዘነብሉ ብቻ እንደኾነ: ዜና መዋዕላቸው ይመሰክራል::

ኢትዮጵያና እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን: እንደሌሎቹ የዓለም ሕዝቦች አይደሉም፤ በዚህ ረገድ: ከቀሩት ኹሉ ይለያሉ:: በቅዱሱ ኪዳን: ከእግዚአብሔር ጋር እጅግ የተሣሠሩ በመኾናቸው: ይህ አቋማቸው: ፍጹም ልዩ ሕዝብ አድርጓቸዋል:: የቅዱሱን ኪዳን: አንዲቷን ግዳጅ እንኳ ሳያከብሩ ቢቀሩ: ኃያልና ምሉእ በኵለሄ ከኾነው ያቺ ግዳጅ: ካላት መለኮታዊት ሥልጣን የተነሣ: ይህ የጥፋት ድርጊታቸው ከሚያስከትለው ተጠያቂነት: በምንም መንገድ ሊያመልጡ ከቶ አይችሉም:: ምክንያቱም: ቅዱሱ ኪዳን: የታተመው: ለመሥዋዕት በተለመደው: በእንስሳ ደም ሳይኾን: ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ፥ ለዘለዓለሙም: መለኮታዊ በኾነው: በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በመኾኑ ነው::

ኢትዮጵያውያን: ይህን ቅዱስ ኪዳን: በጠበቁትና ባከበሩት መጠን: በግል ኾነ በአገር ደረጃ: ሀብታቸው ሰፍቶና በበረከት ተመልቶ፥ በባዕዳን ዘንድ ተከብረው፥ ተወድደውና ሞገስን አግኝተው፥ እርስ በርሳቸውና ከሌሎችም ጋር: ስምም ኾነው: በሰላምና በፍቅር ይኖራሉ:: በዚህ አንጻር ደግሞ: እርሱን: ንቀውና ቸል ብለው: በተዉትና በተላለፉት ጊዜ: ራሳቸው ተዋርደውና ተጥለው: በጠላቶቻቸው እጅ: ሰለባ ኾነው ይወድቃሉ::

እርስዎ (ምስተር ናፍታሊ) እና "የተማሪ" የሚባለው: የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ: በእንቢተኛነት: "አንቀበልም" ብላችሁ የተቃወማችኋት እውነት: እንግዴህ: ይህች ናት!

ይኹን እንጂ: እናንተ ተቀበላችሁትም: አልተቀበላችሁትም፥ ወደዳችሁም: ጠላችሁም: የእግዚአብሔር እውነት: በልዕለ ተፈጥሮ ሰማያዊ ኃይሏ በምትፈጽመው ትንግርቷ አማካይነት: እስከዛሬ የገለጠችውና ዛሬም እየገለጠች ያለው፥ ወደፊትም መግለጧን የምትቀጥልበት እውነታ: ይህ ነው:: በጠቅላይ አዛዡ: በአጼ ኃይለ ሥላሴ አዝማችነት ይመራ የነበረው: የኢትዮጵያ አገሪኛ ተከላካይ ሠራዊት: በፋሺስቱ የጣልያን ወራሪ ጦር ኃይል: ማይጨው ላይ የመሸነፉ ዝክረ ነገር: ለዚህ እውነታ: ማረጋገጫው ምስክር ኾኖ ይኖራል:: ይህም: ከዚህ በታች በሠፈረው ሐተታ ተብራርቶ ቀርቧል::

እዚህ ላይ: መንፈሳዊ ዓይንዎን: በይበልጥ ከፈት አድርገው: ማይጨው ላይና እዚያ ከደረሰው: ከጦርነቱ ሽንፈት በኋላ የኾነውን: የአጼ ኃይለ ሥላሴን ማፈግፈግ፥ ወደአዲስ አበባ ያደረጉትንም: የሽሽት መልስ፥ ከዚያ: ለአቤቱታ ወደጀኔቫ የቀጠሉትን ጉዞና ለስደት ኑሮ: ወደእንግሊዝ ምድር ያመሩበትን አካሄድ፥ በመጨረሻም: በይሁዳው አንበሳ: በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊነት: ወደኢትዮጵያ ያከናወኑትን: የሚጠት ፍጻሜ: ይህን ኹሉ: በቅን አስተሳሰብና በትክክለኛ ትኵረት እየተመለከቱ: በዓይነ ሕሊና እንዲከተሉት: እንደገና እጠይቅዎታለሁ::

## ኢትዮጵያ:
## የማይጨውን ጦር ሜዳ
## ስትፋረድ!

"የጀኔቫው የመንግሥታት ማኀበር: ኢትዮጵያን በመደገፍ: ማለትም: ወደፊት እየገፋ የሚኼደውን: የጣልያንን ጦር እርምጃ የሚያቆም፥ ያም ባይቻል: የሚገታ: አንድ ዓይነት ብያኔን ሰጥቶ: ውሳኔውን ያስተላልፍልናል" የሚለው: የአጼ ኃይለ ሥላሴ: ምንጊዜም ያልተቋረጠው ጽኑ ተስፋቸው: በዚያ: በማይጨው የጦር ሜዳ ላይ እንኳ: ፈጽሞ አልተቀነሰም ነበር:: ያም የጦር ሜዳ: በአንድ ወገን: በግፍ የመጣበትን: ወራሪውን የጠላት ጦር ለማስተናገድ: በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው ረገድ: የኃይል ጸጋውን የተገፈፈው: ተከላካዩ የኢትዮጵያ ሠራዊት፥ በሌላው ወገን ደግሞ: ኢትዮጵያንና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቧን ደምስሶ ለማጥፋት: እጅግ በላቀ: በሥጋዊው የትጥቅ መሣሪያና ወታደራዊ ኃይል ብቻ ሳይኾን: ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ርእስ በተቀበለው: የአቡን ቡራኬ አማካይነት ባገኘው መንፈሳዊ ኃይል ጭምር ደርጅቶ: በሰብሪት የተነፋው: የጣልያን ሠራዊት: ለውጊያ ተፋጥጠውና ተሰልፈው የነበሩበት ነው::

## አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በጄኔቫው ቃል ኪዳን መታለላቸው።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለመቼውም ጊዜ ሳይደርስ፡ እንዲያው ተስፋ ብቻ ኾኖ ከቀረው፡ ከጄኔቫው ቃል ኪዳን፡ አንዳች "መልካም የኾነ ዜና ይመጣልኛል!" ለሚለው ምኞታቸው፡ ልባቸው፡ እስከመጨረሻው እንደተንጠለጠለ መቆየቱ ይታወቃል። ከዚያ ኹኔታቸው ጋር፡ በአሳብ እንዲወላውሉና ጠላትን፡ ባላቸው የጦር ኃይል ተዋግተው ለመቋቋም፡ የጀግንነት ውሳኔን ለመስጠት፡ ቆራጥ ወኔን እንዲያጡ ያደረጋቸው፡ ያ፡ አንዳች መንፈስ፡ በማይጨው ጦር ሜዳ ላይ ብቻ ሳይኾን፡ የፈተናው ማዕበል ከደረሰበት፡ ከመጀመሪያው ቀን አንሥቶ፡ እስከመጨረሻዋ ሰዓት ድረስ ሳይቀር፡ ያልተለያቸው፡ እንደነበረ፡ በአድራጎታቸው ኹሉ ታይቷል። ይኸውም፡ ምንም ሙያ ካልታየበት፡ ከጦርነቱ አውድማ ተመልሰው፡ በአዲስ አበባ፤ ከዚያም፡ ወደጄኔቫ ተጉዘው፡ በዚያ በቆዩበትና ተስፋ ቆርጠው፡ ለስደት ወደእንግሊዝ አገር፡ እስከገቡባት አፍታ ድረስ፡ በገሃድ ያሳዩት ኹኔታቸው ነው።

ያን የመሰለው ማመንታትና በታላቁ የአገር ጉዳይ ላይ፡ ተገቢውን ቆራጥ ውሳኔን፡ በጊዜው ለመስጠት አለመቻል፡ ከወራሪ ጠላቱ ጋር፡ እስከደሙ መፍሰስና እስከሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ተናንቆ፡ በመሥዋዕትነት ለማለፍና ለማረፍ፡ እንዲያ፡ በአገር ፍቅር እሳት እየተቃጠለ፡ በመንፈሳዊው ቅንዓት ይንበለበል የነበረው፡ ያ፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት የአርበኝነት ወኔ፡ በመሪው ዳተኛነት ብቻ፡ እንዲቀዘቅዝና በመጨረሻ እንዲጠፋ ስለተደረገ፡ ያ፡ ዝርክርክነት፡ ግፈኛው ሠራዊት፡ ድልን እንዲጐናጸፍ፡ የተመቻቸ ኹኔታን ሊፈጥርለት በቅቷል። ከዚህ የተነሣ፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት፡ ሐሞቱ ፈሰሶና መንፈሱ ወዳድቆ፥አውራ እንደሌለው የንብ መንጋ፡ በያለበት ተበታትኖና በውርደት፡ ጀርባውን ለጠላት ሰጥቶ፡ ወደኋላው እንዲመለስና እንዲሸሽ ተገደደ። ይህም፡ ኾን ተብሎ፡ በእውቀትና በፈሊጥ የተደረገ ከኾነ፡ ለዚህ ምሥጢራዊ ድርጊት፡ የተከፈለውን የዋጋ ዓይነት፡ እስካሁን ከተመለከትነው በላይ፡ የቀረውን ደግሞ፡ በማካተት፡ በሚቀጥሉት ገጾች እናያለን።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በአንድ ፊት፡ "በተግባር አውለዋለሁ" ብለው ያዘጋጁት፡ ያ ኹሉ የግምት ዕቅዳቸው፡ በዚህ መልክ ተሰነካክሎና ውጤት አልባ ኾኖ ሲቀር፡ በሌላው አንጻር ደግሞ፡ ከልባቸው ያመኑበትና፡ ግዴታዎቹን፡ በጋለ ስሜት እየተከታተሉ ሊፈጽሙ ይጓጉለት የነበረው፡ የጄኔቫው ቃል ኪዳን፡ እንደጠበቁት ሳይኾን፡ የጣሉበት ተስፋ ኹሉ፤ ከንቱ ኾኖ፡ በዓይናቸው ሥር ሲንኮታኮት ተመለከቱ። ይህም ፍጻሜ፡ ጭፍን በኾነ አስተሳሰብ፡ በመንግሥታቱ ማኅበር ቃል ኪዳን ላይ፡ አሳድረውት የነበረው፡ የፍጹም እምነታቸውና የሙሉ ትውክልታቸው መራራ ፍሬ ነበር። ይህንንም እውነታ፡ "ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ" በሚለው፡ የማስታወሻ መጽሐፋቸው ውስጥ፡ ራሳቸው አምነው አረጋግጠውታል።

## በቅዱሱ ኪዳን መታመን ሲቀር::

በቅዱሱ ኪዳን ፍጹም ዋስትና የተረጋገጠው: መለኮታዊው ጥበቃና ተከላካይነት: በማይጨው: የኢትዮጵያ ጦር ሠፈር ውስጥ: ጨርሶ ያልነበረ ለመኾኑ: የሚያጥለቀልቀውን ማስረጃ ሰምተናል:: ይኸውም: በጦርነቱ መስከና አካባቢ: ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ የታየው ኹኔታ: በባቢሎን ግንብ ጊዜ የነበረውን የመሰለ በመኾኑ ነው::

የቅዱሱ ኪዳን ጸጋና ኃይል: ኢትዮጵያውያንን ከተለያቸውና ሠፈራቸውን ጥሎ ከኼደ: ረዘም ያለ ጊዜ አልፎአል:: ይህም: አጼ ኃይለ ሥላሴ: እምነታቸውንና ተማኅጽኖአቸውን: በእግዚአብሔር ላይ ከመጣል ይልቅ: "ወደጀኔቫው ቃል ኪዳን መቀየር ይሻላል" ብለው: በሕሊናቸው መወሰናቸው: በቅዱሱ ኪዳን ባለቤት ዘንድ: ከታወቀባት ቅጽበት አንሥቶ ነበር! የዚያም ውሳኔያቸው ውጤት: "አክብሬ እጠብቀዋለሁ" ብለው: በሃይማኖታዊ የመሐላ ቃላቸው ያጸኑትን: መለኮታዊዉን ቃል ኪዳን መካድና ማርከስ ኾነባቸው!

ታዲያ፥ እዚህ ላይ: እርስዎ ምን ይላሉ? "እግዚአብሔር: በማይጨው ጦር ሜዳ : በኢትዮጵያውያን ሠፈር ውስጥ ነበረ" ይላሉን? ነበረ ሊባል ጨርሶ አይቃጣም:: የነበረ ከኾነማ: ደርሶ እንደታየው: ድል የመኾኑ ክፉ ዕድል: እንኳንስ ሊኾን ይቅርና: ሊታሰብ እንኳ: ከቶ አይደፈርም ነበር::

ዳግማዊ አጼ ምኒልክንና ንግሥት ዘውዲቱን የመሰሉትን: የቅርብ አባቶቻቸውንና እናቶቻቸውን ፈለግ ተከትለው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በቅዱሱ ኪዳን ላይ የነበራቸውን: ፍጹም እምነትና ሙሉ ትውክልት አጽንተው ቀጥለውበት ቢኾን ኖሮ እኮ፥ ወይም: ከእነዚያ ቀደም ብለው: በተከታታይነት: የአጼነቱን ሥልጣን ይዘው እንደነበሩት: ቀደምት አባቶቻቸው: እንደዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስና እንደአጼ ዮሐንስ ራብዓዊ: ራሳቸውን: ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ህልውና ሲሉ: በቤዛነት አሳልፈው ሰጥተው፥ ሕይወታቸውንም በክብር ሠውተው ቢኾን ኖሮ እኮ: የማይጨው የመጨረሻ ዕድል: ከመራራነት መዘከሩ: ፈጽሞ የተለየ በኾነ ነበር:: አዎን! አንጸባራቂ ዝናቸው: እንደቀትር ፀሐይ ሲያበራ ይኖር ዘንድ: ከጥቂት ዓሠርተ ዓመታት በፊት: በአድዋ፥ በመተማና በመቅደላ ላይ: በተከታታይ እንደተቀጣጠሉት: ሕያዋን የድል ችቦዎች ኹሉ: ያም የማይጨው ዕድል: እንዲያ: ውርደትና ኃፍረት መኾኑ ቀርቶ፥ የድል ጣፋጭ ጽዋ ኾኖ: ለኢትዮጵያና ለቅዱሱ ኪዳንዋ: ገናና ዝናን ባተረፈላት ነበር::

ለመኾኑ: የማይጨዉን ሽንፈት ያስከተለው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በቅዱሱ ኪዳን ላይ: የክህደትና የርኩሰት በደልን በመፈጸማቸው ምክንያት ብቻ ነበርን? ወይስ: ከዚያ በፊት: እርሳቸው እና/ወይም የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ የፈጸሙት: ይህን የመሰለውን ቅጣት: ሊጋብዝ የቻለ: ሌላ ኃጢአት ኖርዋል? ስለዚህ: ምሥጢር ስለኾነው ጉዳይ: የቅዱሱ ኪዳን አምላክና ታማኞቹ ልጆቹ: የሚያውቁትን ነገር: የእግዚአብሔር እውነት: በጊዜው ገልጣ እስክታስታውቅ ድረስ: በእኔ በኩል: ይህን አርእስተ ጉዳይ በሚመለከት: እዚህ ላይና በዚች ሰዓት: አንዳች: ዝርዝር የኾነ ነጥብን ከማቅረብ: ወይም ትችትን ከመሠንዘር መቆጠብን መርጫለሁ::

የማይጨዉን ሽንፈት በሚመለከት ግን፡ ያ፡ አሳዛኝ ፍጻሜ እንዲደርስ፡ እግዚአብሔር ለምን እንደፈቀደ፡ በእርግጥ፡ ይህን፡ ደህና አድርጌ አውቃለሁ። ይኸውም፡ በእርሱ ዘንድ፡ ያን አሳዛኝ ፍጻሜ ተገቢ የሚያደርግና በፊቱም፡ ጨርሶ በማያጠራጥር ኹኔታ፡ በቂ ኾኖ ሊገኝ የቻለ ምክንያት በመኖሩ መኾኑን የሚያረጋግጥ አጥጋቢ ማስረጃ ስላለ ነው። ይህም አጥጋቢ ማስረጃ፡ የቅዱሱ ኪዳን የውል ሥርዓቶችና ግዳጆች ካለመከበራቸው የተነሣ በደረሱት የበደል ውጤቶች ገዝፎ ይታያል።

አዎን! እግዚአብሔር፡ ፍጹሙ ፍትሕ ነው። የሚያደርገውም ኹሉ፡ ምንጊዜም ፍጹም ትክክል ነው። የፍትሕ ርትዕ ባለቤትነት፡ የእርሱ ብቻ ነው። ስለዚህ፡ የቅዱሱ ኪዳን አምላካችንን፡ በማይጨው ጦር ሜዳ ላይ ስለኾነው ነገርና ስለታየው ኹኔታ ኹሉ፡ "ለምን እንደዚያ ኾነ?" ብለን፡ በአሉታ መንፈስ ልንጠይቀው፥ ወይም የፍርድ ውሳኔን ልንሰጥ ከቶ አንደፍርም። በዚያ የኾነው ኹሉ የደረሰው፡ በመለኮታዊ ዳኝነቱ መሠረት፡ የተሰጠውን ፍርድ ለመፈጸም እንደነበረ እናምናለን እንጂ። በዚህ ረገድ፤ በቅዱሱ ኪዳን መሠረት፡ ለእርሱ ታማኞች ኾነን እንገኝ ዘንድ፡ የገባነውን ግዴታ፡ በሃይማኖት አቋማችን ጸንተን ካልፈጸምን በቀር፡ ወይም እስካልፈጸምን ድረስ፥ ወይም ደግሞ፡ ይህን ለማድረግ በማንችልበት ኹኔታ ላይ ተገኝተን፡ የበደል ኃጢአትን በፈጸምን ጊዜ፡ ይህንኑ ኃጢአታችንን፡ በንስሓ ካላስወገድነው በቀር፡ ቅንጣት ያህል እንኳ፡ ሕፀፅ (ጐድለት) ሊኖርበት የማይቻለው ዳኝነቱ፡ ከአምላካችን እንደማይቀርልን አምነን፡ የፍርዱን ፍጻሜ መጠበቅ ይኖርብናል።

## ኢትዮጵያ፡
## የጄኔቫውን የዓለም መንግሥታት ማኅበር
## ስትፋረድ!

የማይጨው ልምድ፡ ማለትም፡ በዚያ የደረሰውና የታየው አሳዛኝ ዕድል፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በቂ ትምህርት ኾኖ ሊያገለግላቸው፥ ወደትክክለኛውም ቅን አስተሳሰባቸው መልሶ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸሙት በደል፡ ተጸጽተውና ራሳቸውን በንስሓ አስተካክለው፡ የቃል ኪዳናቸውን ሃይማኖታዊ ግዳጅ ወደማክበሩ አግጣጫ እንዲመለሱ ሊያደርግ፡ ገና የቻለ አልነበረም። በአባል መንግሥታቱ ጽሑፍ ኪዳን (firma ፊርማ) በጸደቀውና በጄኔቫው ማኅበር ቃል ኪዳን ሕጋዊ ሰነድ ውስጥ በሠፈረው፡ በጋራ ፀጥታ ጥበቃ መሠረታዊ አሳብ ላይ ያላቸው ጽኑ እምነት፡ አሁንም በተመሥጦ እያሠቃያቸው ይገኛል። ከዚህ የተነሣም፡ ራሳቸው በአካል ተገኝተውና በግንባር ኾነው አቤቱታቸውን፡ በንግግር በማቅረብ፡ የማኅበሩን አባል መንግሥታት ለማሳመን፥ ጥያቄያቸውንም እንዲቀበሉ ለማድረግ እንደሚችሉ፡ አሁንም፡ በሙሉ ልብ ተማምነው፡ ወደጄኔቫ በመጓዝ፡ ይህን እምነታቸውን ለፍሬ ለማብቃት ጥረታቸውን ቀጠሉ!

## የክህደት ኮሶና ንግርት የመላበት: የጄኔቫው ዋንጫ::

ዳሩ ግን: ጄኔቫ ሲደርሱ: በዚያ የገጠማቸው ምን ኾኖ ተገኘ? ያ: ገጸ በረከት ኾኖ: ከመንግሥታቱ ማኅበር: "በወርቅ ጻሕል: በክብር ይቀርብልኛል" ብለው የተማመኑትና የጠበቁት: ጣፋጩ የቃል ኪዳን ቁም ነገር መኾኑ ቀርቶ: ያልጠረጠሩትና ያልጠበቁት፥ ቅስም የሚሰብርና ተስፋ የሚያስቆርጥ፥ የሚያሳዝንና የሚያስተዛዝብ: ፍጹም ሌላ ኾኖ ተገኘ! እርሱም: ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፎ እስከመስጠት የተደረሰበትንና መራራ የክህደት ኮሶን የተመላው: "የተሰባሪ ሸክላ ጽዋ": በንቀት ተወርውሮላቸው: እርሳቸውም: ተገድደው: በውርደት የተቀበሉት ስጦታ ነው! ይህን ሥርዓት ለመፈጸም ተጠርቶ የተሰበሰበው: የመንግሥታቱ ማኅበር ጠቅላላ ሸንጎ: የጉርፍ ውኃ እንደሚፈስስበት ዓለት ቁጭ ብሎ: አቤቱታቸውን: ፈጽሞ በማይሰማ ጆሮው በሚያዳምጥበት ጊዜ: ዐምቆ ይዞት የነበረው: የማስመሰል ሰላማዊ ፀጥታ: አልፎ አልፎ: በጠላትነት የተቃውሞ ጩኸት ይደናቀፍ ነበር::

የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ የኾነው: እግዚአብሔር: እርሱ መርጦ በሾመውና በተቀባው አገልጋዩ: በአጼ ኃይለ ሥላሴ አማካይነት: የመለኮታዊ እውነቱን ትንቢታዊ መልእክት: ለመንግሥታቱ ማኅበር አባሎች፥ ሕዝቦችና መሪዎቻቸው ብቻ ሳይኾን: ለመላው ፍጥረተ ዓለሙ ጭምር ለማሰማት: ያ: በጄኔቫ የተከናወነው ሥርዓት: መድረክ ኾኖ አገልግሎታል:: ትንቢታዊ መልእክቱም: የእግዚአብሔር መንግሥት በኾኗችው ኢትዮጵያ ላይ: አህጉር አቀፍ የኾነው: የጄኔቩ ማኅበር አባሎች የኾኑትና ያልኾኑት መንግሥታት: ሴራ በማድረግ፥ ለኢትዮጵያም: በቃል ኪዳን የገቡትንና በጽሑፍ ኪዳን ያጸኑትን ውል: በክህደትና በተንኰል በማፍረስ: ለፈጸሟቸው ወንጀሎች: የተዘጋጀላቸውን የደለበ የቅጣት ዋጋ: የሚቀበሉበት: የዋይታ ጊዜ: በአሠቃቂ ገጽታው: እየተቃረበ መኾኑን: ለመላው የዓለሙ ኅብረተሰብ ለማስጠንቀቅ: የተላለፈ መለኮታዊ አዋጅ ነበር::

እዚህ ላይ ግን: "ከእግዚአብሔር መንግሥት በቀር: በምድር ላይ: ማናቸውም መንግሥት: አንዱ ከሌላው አይበልጥም" የሚለውን ኃይለ ቃል: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በዚያ: በጄኔቫው ሥርዓትና መድረክ ላይ ባሰሙባት ሰዓት: የኢትዮጵያን ማንነት፥ የራሳቸውንም ምንነት: የዘነጉ ይመስላል፤ ወይም: በዚህ ረገድ: የእግዚአብሔር እውነት የፈጸመችውን ዘለዓለማዊ ሥራዋን: አዎን! በዚያ ሕያው ንግግራቸው ላይ: በማያሻማና በበረታ ቃል መግለጹን ትተው በዝምታ ያለፉት: "ኾን ብለው ሊኾን ይችላል" ብሎ መገመቱም ያስኬዳል::

እንዲያማ ካልኾነ: አያይዘውና አበክረው ሊሰጡት ይገባ የነበረው መግለጫ: የሚከተሉትን፥ የማይለያዩ ቁም ነገሮች: አዋህዶ መቅረብ ነበረበት፤ ከእነዚህም: አንደኛው: "የእግዚአብሔር መንግሥት" የምትባለው አገር: በዚሁ የአቤቱታ ንግግራቸው ውስጥ የጠቀሷት፥ በዚያን ጊዜ: እዚያው ጄኔቫ: እርሳቸው የወከሏትና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ መኖርያ የኾነችው: ይህችው ኢትዮጵያ መኾኗን ነው::

ኹለተኛው ደግሞ፡ እርሳቸው ራሳቸው፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" ተብለው፡ በተቀቡበት ሰውነታቸው፡ ለዚችው መለኮታዊት መንግሥት፡ ንጉሠ ነገሥት የኾነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የንግሥተ ነገሥታቱ፡ የድንግል ማርያም ተጠሪና ዋና አገልጋይ መኾናቸውን የሚያረጋግጡት እውነታዎች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ፡ እንዲህ፡ ከፍጥረት ጀምራ፡ በምድር ላይ ተገልጣና ሰፍና የምትኖር፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኾና የመኖር ጸጋዋን፡ እንደእስከዛሬው ኹሉ፡ ለወደፊቱና ለዘለዓለም እንደያዘች፡ በህልውናዋ ትቀጥላለች፡፡

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የኢትዮጵያን ጉዳይ፡ ለጀኔቫው ጉባዔ ባቀረቡበት ጊዜ፡ ቀድሞውኑ፡ ራሳቸው፡ አገራቸውን፡ የማኅበሩ አባሎች ከኾኑት፡ የሰዎች መንግሥታት መካከል፡ አንዷቱ፡ መሰል ሰብአዊ መንግሥት እንደኾነች አድርገው፡ ስላስተዋወቋት፡ የመንግሥታቱ ማኅበር ኾነ፡ ወይም ግብረ አበሮቹ፡ በኢትዮጵያ ላይ በክህደት ያካኺዱት ከነበረው፡ የሴራና የተንኮል ተግባር የተነሣ፡ ይጠብቃቸው የነበረው፡ የፍዳ ዓይነትና መጠን፡ እጅግ የከፋና የጠነከረ ሊኾን ስለመቻሉ፡ በትክክል አለመገንዘባቸው፡ በምንም አያስደንቅም፡፡

ይህ ኹሉ ኹኔታ፡ በጀኔቫ እየደረሰባቸው እንኳ፡ አሁንም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለመንግሥታቱ ማኅበር ቃል ኪዳን ያላቸው የተሣሠረ ፍቅር፡ ቀጠለ እንጂ፡ ከቶ አልተለወጠም፤ ለምን በዚያ የእምነት አቋማቸው፡ ያን ያህል እንደጸኑም ለመረዳት፡ ዛሬም ቢኾን ያዳግታል፡፡ እንዲያውም፡ ለዚያ የሰዎች ቃል ኪዳን ለመገዛት፡ የነበራቸው ታማኝነት፡ እጅግ የላቀ ከመኾኑ የተነሣ፡ በጀኔቫ ከተማ ለመቀመጥ ይችሉ ዘንድ፡ ከስዊትዘርላንድ መንግሥት፡ የመኖርያ ፈቃድ ለማግኘት፡ ማናቸውንም ጥረት አድርገው ነበር፤ ዓላማቸውም፡ ለመንግሥታቱ ማኅበር መሥሪያ ቤት ቅርብ መኾናቸው፡ የኢትዮጵያን ጉዳይ፡ ዕለት በዕለት ለመከታተል እንደሚያመቻቸው ስላመኑ ነበር፡፡ ዳሩ ግን፡ አሁንም እንደገና፡ ኹሉንም ያስገረመና ያልተጠበቀ እንግዳ ነገር ደረሰ! ይኸውም፡ በጽሑፍና በይፋ ያቀረቡት ማመልከቻ፡ ተቀባይነትን አጥቶ፡ የስዊስ መንግሥት፡ የጠየቁትን የመኖርያ ፈቃድ ከለከላቸው፡፡

ስለዚህ፡ ድካማቸው ኹሉ ፍሬ አልባ ኾኖ÷ የደረሰባቸውንም ኹሉ አምነው ለመቀበል፡ አዳጋች ኾኖባቸው÷ በጽኑ የልብ መሰበር፡ የጀኔቫን ከተማ ለቅቀው መውጣት ግድ ኾነባቸው! ይህም፡ የማይጨውን ልምድ የመሰለ፡ ሌላው ትምህርት÷ አዎን! ሌላው የመለኮታዊው ማስጠንቀቂያ ምልክት ነበር፡፡

## የስደቱ ጽዋ፡ ያስገኘው የንስሐ በረከት፡፡

በመጨረሻ፡ በእንግሊዝ አገር፡ የስደት ኑሮን እንዲመሠርቱ ተገደዱ፡፡ ይኹን እንጂ፡ እዚያም ኾነው፡ ለጀኔቫው የመንግሥታቱ ማኅበር ቃል ኪዳን የተመሠጡበት የከረረ ፍቅር፡ ፈጽሞ ሊረግብ አልቻለም፡፡ አሁንም፡ እዚያው ጀኔቫ ድረስ ኼደውና በጉባዔው አዳራሽ፡ በአካል ተገኝተው፡ እንደገና የአቤቱታቸውን ንግግር፡ ለማኅበሩ ጠቅላላ ሸንጎ፡ በቃል ለማሰማት፡ ጥያቄ አቀረቡ፡፡

የዚህን ጥያቄያቸውን ምላሽ፡ ከጄኔቫ በጉጉት መንፈስ በሚጠባበቁበት ወቅት፡ በጽኑ ታምመው፡ አልጋ ያዙ፤ ሕመማቸውም እየበረታ ሄዶ፡ ከአሥጊነት ደረጃ ደረሰ፡፡ ያን የጓጉለትንም ንግግር፡ በሸንጎው ላይ፡ በግንባር ተገኝተው ለማሰማት ሳይችሉ ቀሩ! ይህም፡ ሌላ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ኾኖ የቀረበ፡ መለኮታዊ መልእክትን ይመስላል፡፡ ያን በመሰለ የሕመም ይዞታ ላይ እያሉ እንኳ፥ የሐኪሞቻቸውን ምክር ሳይቀር በመጋፋት፡ "እምቢ" ብለው፡ እየታገሉ፡ በለንደንና በጄኔቫ ከተሞች መካከል ለመመላለስ መሞከራቸው አልቀረም፤ አዎን! በደከመና በከሣ ሰውነታቸው፡ ጥብቅ የኾነ የሕክምና ቁጥጥር እየተደረገላቸው፡ በመንግሥታቱ ማኅበር ስብሰባዎች ላይ ተገኙ፡፡

ጉዳዩ፡ ተስፋ አስቆራጭ በኾነ፡ ይህን በመሰለ ደረጃ ላይ መድረሱ እየታወቀም፡ ለመንግሥታቱ ማኅበር ቃል ኪዳን ያላቸውን ታማኝነት፡ ብቅዓት የሌለው የሚያስመስል ወይም የሚቀንስ መስሎ የሚያሳይ፡ አንዳች ጉድለት ወይም እንከን፡ ከእርሳቸው በኩል እንዳይገኝ፡ ያላደረጉት ሙከራ አልነበረም፡፡ ይኹን እንጂ፡ ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ፡ በበለጠ ጥረት ባደረጉ መጠን፡ የዚያ ጥረታቸው ውጤት ደግሞ፡ የባሰ ፍሬቢስና ከንቱ እየኾነ መጣ!

ያ ኹሉ መሥዋዕትነት ከተከፈለ በኋላ፡ በጎርፍ ከሚናወጽ ተራራ ላይ እየተፈነቀለ እንደሚወርድ የድንጋይ ናዳ፡ ከጄኔቫው የመንግሥታት ማኅበር ቃል ኪዳን፡ በተከታታይ እየተወረወረ ያቆሰላቸውና የተከመረባቸው አሳዛኝ የሸንገላና የክህደት ጦር፡ ሊቋቋሙት የማይቻላቸውና ከዓቅማቸው በላይ የኾነ የኀዘን ጭነት ስለኾነባቸው፡ እነሆ፡ በአታካቹ የአቀበት ጉዟቸው ፍጻሜ ላይ፡ ወደቅዱሱ ኪዳን አምላካቸው ተመልሰው፡ በፊቱ እንዲንበረከኩ ተገደዱ!

ያች የልቦና ጸጸት፡ ወደተረጋጋው ደህና አእምሮአቸው የተመለሱባት ቅጽበት ኾነች! በዚያች አፍታ፡ በቅዱሱ ኪዳን መንፈስ ተመልተው፡ በትክክል ማሰብ ጀመሩ! ጠፍቶ ወደአባቱ እንደተመለሰው ባካና ልጅ፡ በጥልቅ ሃይማኖታዊ ሕሊና፡ ንስሓ ገብተው፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ስለፈጸሙት በደል፡ የፈጣሪያቸውን ይቅርታ ጠየቁ!

እግዚአብሔርም፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደእርሱ፡ በተመለሱባት፡ በዚያች ቅጽበት፡ ቅዱሱን ኪዳኑን አሰበ! መርጦ ወደሾመውና ወደቀባው አገልጋዩም፡ የምሕረት ዓይኖቹን፡ በርኅራኄ መለሰ! አዎን፥ ልክ፡ ጠንቃቃ ወላጅ አባት፡ ለሚጨነቅለት ልጁ ደኅንነት ሲል፡ ይህንኑ የሚወድደውን ልጁን እንደሚገሥፅና እንደሚቀጣ ኹሉ፡ የኢትዮጵያ አምላክም ያደረገው፡ እንዲሁ ነበር፡፡ በቅዱስ ኪዳኑ፡ በደነገገው ሥርዓቱ፡ የቃል ኪዳን ልጁንና ተጠሪ አገልጋዩን፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን፡ ስለኃጢአታቸው፡ ገሠፀ፥ ቀጣ! እርሳቸው፡ በእውነት ወደእርሱ ተመልሰው፡ ሲጠሩት ደግሞ፡ እርሱም፡ ፈጥኖ፡ "ወይ!" ብሎ፡ ተመልሶ ተቀበላቸው!

በዚህ መልክ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ በእውነተኛ ንስሓ ወደፈጣሪያቸው መመለስ፡ ይህም ማለት፡ የአስተሳሰባቸው አቋም፡ ፍጹም መለወጥ፡ የኢትዮጵያን ጉዳይ፡ የሚይዙበትና የሚከታተሉበት ኹኔታ እንዴት ሊኾን እንደሚገባ፡ እያመለከተ የሚመራቸውን፡ የሕሊናቸውን ኹለንተና፡ ከመሠረቱ ቀየረው!

እንግዴህ ወዲህ: በእርሳቸው በኩል: "በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከተፈጸመው ክህደትና ርኵሰት" የተነሣ: "በካቶሊካዊው በሙሶሎኒ የፋሺስት ጣልያን ጦር ሠራዊት መሸነፍን" በእርሳቸው ላይ ያስከተለው: "የጄኔቫው የመንግሥታት ማኅበር ቃል ኪዳን": በእርሳቸው ዘንድ "መታመኑና መማጸኛ መኾኑ": አበቃ፥ አከተመ!

ንስሓቸው ያደረገው: ይህን ብቻ አልነበረም፤ በይበልጥ: በቅዱሱ ኪዳን ላይ ሊኖራቸው የሚገባውን: "ፍጹም እምነታቸውንና ሙሉ ትውክልታቸውን": ወደነበረበት የቀደመ መሠረታዊ ሥፍራው ሊመልስላቸው መቻሉ የተረጋገጠበትንም ተአምር አሳይቷል! ይህም ተአምር: የአጼ ምኒልክ: ያልተናወጸ የሃይማኖት ጽናት: አድዋ ላይ ያሳየውን ትንግርት በመሰለ ኹኔታ: "ኃያሉን የጣልያን ሠፋሪ ጦር: ከኢትዮጵያ ምድር: አባርሮና ጠራርጎ በማስወጣት: የተከሠተው አስገራሚ ድል ነው።

ልቦናቸው: በእርግጥ: ፍጹም ተለውጦ: ወደነበረበት መመለሱ: ጥርት ብሎ በግልጽ የታየውና ተጨባጭ ኾኖ በግዝፈት የተዳሰሰው: በኹለት ምግባሮቻቸው ነበር። እነዚህም: በመጀመሪያ: በግላቸው: ቁርጥ የኾነውን: ሃይማኖታዊ ውሳኔ በማድረግ: ራሳቸውን በጸሎትና በንስሓ ሱባዔ መወሰናቸው ሲኾን፥ ኹለተኛው ደግሞ: ከዚህ በማከታተል: በእንግሊዝ አገር: ባት በተባለው ሥፍራ: ፌርፊልድ ተብሎ የሚጠራውን መኖርያቸውን: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና የማያቋርጥ ትጋሃ ጸሎት ይካኼድበት ዘንድ: ለቤተ መቅደስነት መመደባቸው ናቸው።

ከላይ: በተለይ: በኹለተኛው ደረጃ የተጠቀሰውን: ሃይማኖታዊ ምግባር: እውን ለማድረግ: በዚያን ጊዜ: በኢየሩሳሌም: የኢትዮጵያ ገዳማት ይኖሩ ለነበሩት: ለእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (ኋላ እጨጌ ባስልዮስ ለተባሉት): ቀሳውስትንና አስፈላጊ የኾኑትን ንዋያት ቅድሳት ኹሉ: አሟልተው: በተቻለ ፍጥነት ይልኩላቸው ዘንድ: አንዱን የቅርብ ባለሟላቸውን: የሰላምታና የአደራ ደብዳቤ አስይዘው: ሳይዘገዩ ላኩባቸው።

ዛሬ: በሕይወት ያሉት ቤተሰቦቻቸውም: በአሁኑ ጊዜ በሚገኙበት: የስደት ኑሮአቸው ውስጥ: ይህን የመሰለውን: ፈተና መቋቋም፥ መከራውንም: ድል መንሣት የሚቻለው: በዚያ: አባታቸው: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በንስሓ ተመልሰው በተጠቀሙበት: በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው መንገድ ብቻ መኾኑን ተረድተው: ጊዜያቸውንና ኃይላቸውን፥ ገንዘባቸውንም: በማይረባውና ከንቱ በኾነው: በሰብአዊው የሥነ መንግሥት ሥልጣን ሽሚያ ላይ በመራኮት ከማሳለፍና ከማባከን ይልቅ: ያን: የእርሳቸውን ምግባር: በአርአያነት በመከተል: የሚበጃቸውን ያደርጉ ዘንድ ትሑት ምክሬን አበረክታለሁ።

## የንስሓው ፍሬ:
## በከሃዲዎቹ ላይ ያወረደው በቀል።

እነዚህ የቅዱሱ ኪዳን ቀዳሚ ግዳጆች እንደተሟሉ: ወዲያው: የአጼ ኃይለ ሥላሴ የቃል ኪዳን አምላክ: መለኮታዊ ምሕረቱን: ወደተነሳሒው "ሥዩም" አገልጋዩ መለሰ!

መለኮታዊ መዓቱን ግን፡ በምድር ላይ፡ መንግሥቱ የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ በክህደትና በተንኰል ተነሣሥተው፡ ፈጽመው ሊያጠፏት ወደተዘጋጁት፥ ከዚሁ በደላቸውም፡ ባለመጸጸታቸው ምክንያት፡ አምልጠው ሊድኑ የማይቻላቸውን፡ የበቀል ቅጣቱን ሊጥልባቸው ወደተገቡት፡ ወደእነዚያ ግፈኞችና ግብረ አበሮቻቸው፡ በስፋት ለቅቆ አመጣባቸው!

የበቀል መቅጫ ኾኖ የመጣው፡ ያም መለኮታዊ መዓት፡ ኹለተኛው የዓለም ጦርነት ነው:: ጦርነቱ አልቀረም፥ ፈነዳ! የጀርመኑ ሂትለር፥ የጣልያኑ ሙሶሎኒና የጃፓኑ ጦረኞች፡ በቃል ኪዳን፡ ግንባር ፈጥረው፡ በኅብረት ተነሡ! የተነሡትም፡ ራሳቸው፡ እነዚሁ አምባገነኖች፡ እንዳሰቡትና እንዳቀዱት፥ እንደመሰላቸውም፡ የየግላቸውን፡ ወይም የጋራ የኾነ ዓላማቸውን ለማስፋፋትና ከግብ ለማድረስ አልነበረም! የእግዚአብሔር መቅጫ በትር ኾነው በማገልገል፡ መለኮታዊ ፍርዱን ለመፈጸም ብቻ፥ አዎን፥ ይህን ጽኑ የተልእኮ ግዳጅ ለማከናወን ብቻ እንጂ!

የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላኳና እውነተኛው የዓለም ዳኛ የኾነው እግዚአብሔር፡ የጀኔቫው የመንግሥታት ማኅበር፥ ከአውሮጳ አባል አገሮቹና ከእነዚያ፡ እስስትና ጅብደኞች ጌቶቹ መንግሥታት ጋር፥ በተለይም፡ ለኢትዮጵያ የገቡትን፡ የቃል ኪዳን ግዳጃቸውን፡ በክህደት አፍርሰው፡ በማናለብኝነት ትምክህት፡ ለጠላቷ በገሃድ አሳልፈው የሰጧትን፡ ፈረንሳይንና እንግሊዝን፥ እንዲሁም፡ ፋሺስት ጣልያን፡ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ፡ ያላወቀች መስላ ለመታየት በመሞከር፡ "እኔ፡ ከደሙ ንጹሕ ነኝ" ብላ፡ ከበደሉ ልትነጻ የማትችለው፡ የአሜሪካ ዩናይትድ ስቴትስ እንኳ ሳትቀር፡ ኹሉም፡ ለፈጸሙት ታላቅ ወንጀል፡ ተመጣጣኝ የኾነውን ከፍተኛ ዋጋ እንዲከፍሉ አደረገ!

አዎን! በየማዕዘናቱ ከተከፈቱት፡ የጠላቶቻቸው ጦር ሠፈሮች፡ ያለማባራት፡ ከሰማይ የሚዘንበው የእሳት በረዶ፥ ያለፋታ፡ ከባሕር የሚወነጨፈው የእሳት ነበልባልና ያለዕረፍት፡ ከየብስ የሚጎርፈው የእሳት ማዕበል፡ ወሰን በሌለው ጭካኔ፥ ያለርኅራኄና ያለማቋረጥ፡ በሩቅና በባሕር ማዶ የሚገኙትን ግዛቶቻቸውን ጨምሮ፡ በእነዚህ አገሮችና ሕዝቦቻቸው ላይ፡ ለአምስት ዓመታት፡ እየወረደ መታቸው! እየተወረወረ አነደዳቸው! እያጥለቀለቀ ደመሰሳቸው!

ይህን በመሰለ ኹኔታ፡ ለአምስት ዓመታት የተቀበሉት ጽኑ ሥቃይ፡ የፋሺስት ጣልያን ጦር፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ኢትዮጵያ ላይ፡ ወረራን እንዲያካኺድ፥ በምድሩዋም ሠፍሮ እንዲቆይ በማድረግ፡ በደባ ተማምለው ለፈጸሙት፡ የአምስት ዓመታት ግፍ፡ መለኮታዊቷ እውነት፡ በማያዳላው ዳኝነቷ፡ የሰጠችው ማካካሻ ፍርድ፡ እንዴት ሚዛናዊ እንደኾነ፡ በማስተዋልና በአንክሮ መመልከት ነው! አዎን! እነዚያ ወንጀለኞች፡ በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸሙት በደል፡ ተገቢውንና ትክክለኛውን ዋጋ ከፈሉ ማለት ነው::

ወደድንም፥ ጠላንም፡ ፍትሕ ርትዕ የተመላባት፡ የእግዚአብሔር ዳኝነት፡ እንግዴህ፡ ይህች ናት! እርግጥ፡ በዓይን አትታይም፤ በእጅም አትዳሰስም፤ ነገር ግን፡ ይህን የመሰለውን ተአምርና ኃይል፡ ይኸው፡ እንዲህ ስትሠራ ትገኛለች:: በሥነ ፍጥረት ዝምታና በሰዎች አንደበት፡ ያለመታከት ትናገራለች፤ በእየአንዳንዱ ሕሊናም ውስጥ፡ "እነሆኝ አለሁ!" ትላለች፤ ነገር ግን፡ "እውን ናት" ብሎ፡ አምኖ የሚቀበላት የለም::

የፍጡራን አእምሮ፡ ሊያስባቸው እንኳ የማይቻለውን፡ ድንቃድንቅ ነገሮችን፡ ዘወትር ታደርጋለች። ተከታዮቿ፡ የእርሷ ስጦታ ወደኾነው ቃል ኪዳን፡ በንስሓ ተመልሰው፡ ረድዔቷን በጠየቁ ጊዜ፡ አሳፍራ አትመልሳቸውም፤ "ደካሞች ናቸው! ረዳትም የላቸውም!" ብለው፡ በገንዘባቸው፥ በጥበባቸው እና/ወይም በኃይላቸው ታብየውና ተመክተው፡ ሊያጠቋቸው የሚነሡባቸውን፡ ወይም የሚመጡባቸውን ልበ ደንዳኖች ዕብሪተኞች፡ ተገቢ የኾነውን፡ የፍርድ ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ከማድረግ፡ ወደኋላ ያለችበት፡ አንዳችም ጊዜ ከቶ የለም።

**መለኮታዊው ፍትሕ፥ ጥበብና ኃይል፡**
**ከሰብአዊው ይልቅ እጅግ ይበልጣል፤ ይረቅቃልም።**

ምንጊዜም፡ የእግዚአብሔር ጥበብና ኃይል፡ የሰዎች ከኾኑት ይልቃል፤ ይቀድማል፤ ይበረታልም። በዚህ መሠረት፡ መለኮታዊው የቀጠሮ ቀን ሲደርስ፡ እኒያ ከሃዲዎች መንግሥታት፡ ቀደም አድርገው፡ አሽቀንጥረው የጣሏቸውን፡ እነዚያን፡ የቃል ኪዳን ተግባሮቻቸውንና በውል፡ የገቡባቸውን ግዴታዎቻቸውን አክብረው እንዲፈጽሙ፡ የኢትዮጵያ አምላክ፡ ልጓሙን፡ ሳይወድዱ በግድ፡ በአፋቸው አግብቶ፡ አስገደዳቸው! አዎን! እኒሁ ግፈኞች፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በእነርሱ እጅ፡ ተገድደው እንዲጠጡት አድርገውት የነበረውን፥ እርሳቸው ግን የንስሓ ሽሬትን ያገኙበትን፡ ያን መራራ የኮሶ ጽዋ፡ ዛሬ፡ ለእነርሱ፡ የዓመፃቸው ዋጋ ኾኖ፡ እንዲጋቱት፡ በዚያው በተለጐመ አፋቸው ውስጥ፡ አሠሩ ሳይቀር አለቅልቆ፡ አንጠፈጠፈባቸው!

ከዚህ የተነሣ፡ እኒያ መንግሥታት፡ በተለይም፡ ታላቋ ብሪታንያ የምትባለው እንግሊዝና ግብረ አበሩዋ ፈረንሳይ፡ ከቃል ኪዳን ጦር ጓደኞቻቸው ጋር፡ በራሳቸው ቀስቃሽነትና ጉትጎችነት ተነሣሥተው፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን ለማግኘት፡ በታላቅ ጉጉት፡ አስቸኳይ አሰሳና ፍለጋ ማካኼድ ጀመሩ፤ እርሳቸውንም፡ በሱባዔ በዓታቸው ተወስነው አገኟቸው! እዚያም፡ በድብቅ ቀርበውና ተገናኝተው፡ ለእነርሱ፡ የቀድሞ ወዳጃቸውና የዛሬ ጠላታቸው የኾነውን፡ የፋሺስት ጣልያንን ጦር ኃይል፡ ከኢትዮጵያ ምድር፡ አባርረው ለማስወጣት ባዘጋጁት የጦርነት ዘመቻ ውስጥ፡ የኢትዮጵያውያን ድጋፍ እጅግ ስላስፈለጋቸው፡ በዚያ እንዲተባበሩዋቸው፡ እየተማጸኑ ለመኗቸው።

በዚህ ረገድ፡ የእግዚአብሔር ዳኝነት ያደረገችውንና ያስደረገችውን ኃይል ለማሳየት፡ ለዚህ፡ ለእነርሱ ድርጊት፡ ተስማሚነትና ተገቢነት ያላቸውን የአበው ምሳሌዎች፡ እዚህ ላይ መጠቃቀሱ ይቻል ነበር፤ ነገር ግን፡ ራሱ ድርጊቱ፡ በራሱ፡ በቂ ማስረጃ በመኾኑ፡ ምሳሌ ስለማያስፈልገው፡ "ምሳሌ ዘየሐፅፁን" (የማይመጥነውን ምሳሌ) ትቼዋለሁ።

ይህች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገር፡ ኢትዮጵያ፡ በልጆቿ ኃጢአት ምክንያት፡ በጠላት እጅ ከወደቀችበት፡ የመርገም ይዞታና ሠፈራ፡ በዚህ መልክ፡ ፍጹም ጠርታ፡ የነጻነት ህልውናዋን መቀጠል ከምትችልበት ዕለት ልትበቃ፡ እነሆ ተቃረበች።

ይህም ብቅዓቷ የተከናወነው፡ በገንዘብ፥ በመሣሪያና በሰው ኃይል ረገድ፡ ያለው ፍላጎቷ፡ በእርሷ በኩል፡ ምንም ያህል ችግርና ተፅዕኖ ሳያስከትልባት፡ በቀድሞዎቹ የክህደት ሸንጋዮቿና በዛሬዎቹ የቃል ኪዳን ጦር ጓደኞቿ ከፋይነት፥ አቅራቢነትና አዘጋጅነት ተሸፍኖ በተሟላበት ኹኔታ ነበር።

ባጭሩ፡ እነዚህ ኹሉ ግዴታዎች፡ በሚገባ ተሟልተው፡ ከመጨረሻው ግብ ተደረሰ! አዎን፥ ኢትዮጵያ፡ በጠላት ይዞታ ምክንያት፡ ለአምስት ዓመታት፡ ተሸፍና የቆየችበትን ጥቁር ሸማ ወዲያ ጥላ፡ ተጐናጽፋው የኖረው፡ ጥንታዊው የዘውድ ልብሷ፡ በነጻነት ብርሃን፡ እንደገና አሸብርቆ ታየ! ከቶ፡ ይህ፡ እንዴት ሊኾን ቻለ? ቅዱሱ ኪዳን፡ በሚያስተማምን ዋስትናው፡ ያረጋገጠው ስለኾነ ነዋ!

የእግዚአብሔር እውነት ላከናወነችው፡ ለዚህ ትንግርታዊ ድርጊት፡ ራሱ፡ የኹለተኛው የዓለም ጦርነት፡ የአጨራረሱ ኹኔታ፡ ምስክር ኾኖ ይናገራል። ይኸውም፡ ለዓለሙ ጦርነት፡ ቀንደኞች ኾነው የተነሡት፡ የሦስቱም አገሮች፡ ማለትም፡ የጀርመን፥ የጣልያንና የጃፓን መሪዎች፡ ተልእኳቸውን ፈጽመው፡ ኹሉም፡ በአንድ ጊዜ፥ በአንድነት መጥፋታቸው ነው።

የእነርሱም ተልእኮ፡ አንድ ብቻ ነበር! እርሱም፡ በመለኮታዊው ዳኝነት የተሰጠውን መለኮታዊውን ፍርድ፡ ቅጣቱን ሊቀበሉ በሚገባቸው፡ በወንጀሉ አድራጊዎች ላይ መፈጸምና ከዚያ፡ በቅዱሱ ኪዳን ንስሓ፡ በተገኘው የእውነት ፍሬ፡ የኢትዮጵያን፡ ኹለንተናዊ ሉዓላዊነት፡ ወደነበረበት መመለስ ነበር። አዎን፥ ማንም ፍጡር፡ መልአካዊ ኾነ፡ ሰብአዊ፥ ወይም፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር" የኾነው፡ አጼውና "የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ" የኾኑት ኢትዮጵያውያን ጭምር፡ ማንም ቢኾን፡ ከእግዚአብሔር ዳኝነት፡ ማምለጥ የሚችል የለም።

## መለኮታዊቷ የድል አክሊል!

የእግዚአብሔር ድል፡ እንዲህ ኾና ከተገኘች በኋላ፡ በመላው የስደት ኑሮአቸው ጊዜ ኹሉ፡ በቅዱሱ ኪዳን ጸጋና ኃይል ተጠብቀውና ተበረታትተው የቆዩት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በመለኮታዊው ኵነኔ ሥር በወደቁት አገሮችና መንግሥታት መሥዋዕትነት፡ የድል አክሊላቸውን ተቀዳጅተው፡ መናገሻ ከተማቸው፡ አዲስ አበባ ተመልሰው ገቡ!

ኹለተኛው የዓለም ጦርነት፡ በአንድ ወገን፡ በሥጋ ለባሾችና በሙታን ሰዎች ተዘጋጅቶ፡ እኒያ፡ የኢትዮጵያ ከሃድያን የወዳጅ ጠላቶች፡ በእርግማን ተገድደው እንዲጋቱት የተደረገው ቃል ኪዳን፡ መራራ የኮሶ ጽዋ ሲኾን፥ በሌላ ወገኑ ደግሞ፡ በንስሓ ለተመለሱት፡ ለቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ሕዝብና ለአጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በበረከት ቀርቦላቸው የጠጡት፡ የሕያው እግዚአብሔር ቅዱስ ኪዳን፡ ጣፋጭ የማር ጽዋ መኾኑ ተረጋግጦበታል።

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በእነዚህ ኹሉ፡ የፈተናና የመከራ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፈውና ወደአገራቸው ተመልሰው፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ በመለኮታዊው የዘውድ ዙፋን ላይ ከተቀመጡ በኋላ፡ ራሳቸው፡ "አዲስ ዘመን" ብለው በሠየሙትና ለብቁ አመራር፡ ተሰናድቶ በጠበቃቸው፡ በዚያ የብርሃን ጊዜ፡ በተግባራቸው፡ እንዴት ኾነው ተገኙ?

በቅዱሱ ኪዳን የንስሐ ውኃ እንደብርጭቆ ጠርቶና በእሳት ማንጠሪያው፡ እንደወርቅ ተፈትኖ በወጣው፡ በዚያ፡ በታደሰው መንፈሳቸው፡ መለኮታዊት መንግሥቱን፡ ኢትዮጵያን፡ ከአዲሱ ትውልዱ ጋር፡ ይመሩለት ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳኑ፡ አደራ የሰጣቸውን፡ እርሳቸውም በመሐላ የተቀበሉትን፡ ያን ኃላፊነታቸውን፡ በቀጠለው ቀሪ ዘመናቸው፡ በእንዴት ያለ ይዞታና መልክ ተወጡት?

ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፡ የእግዚአብሔር እውነት የተናገረችውን ቃልና የሰጠችውን ምስክርነት፡ እስካሁን በተጓዝንባቸው ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው ታትተው ስለተመለከትናቸው፡ ኹሉንም በሚበቃ የተረዳን ይመስለኛል።

በመጨረሻ፡ ባለፈውና በቅርቡ ጊዜያት የኾነውን፥ በእየራሳችንም ላይ የደረሰውን፡ ይህን ኹሉ ያየን፡ እኛ፡ የዛሬዎቹ ደግሞ፡ "ምን እንሆን ይኾን? ምንስ እናደርግ ይኾን?" ተብሎ የሚቀርብ ጥያቄ ካለ፡ (እዚህ ላይ፡ ራሴን የጨመርሁት፡ መቼም፡ በሕይወት ቆሜ ከተገኘሁ ብዬ ነው) ለዚህ ጥያቄ፡ "ዕድሜውን የሰጠው፡ ያ፡ ባለዕድል፡ በራሱም ኾነ በሌሎች፡ የሚኾነውንና የሚደረገውን፡ ኹሉንም ያያል!" በሚል መልስ አሳጥረዋለሁ።

በበኩሌ ግን፡ "እግዚአብሔር፡ እንግዲህ ወዲህ፡ ይህን የመሰለውን ጽዋ፡ በኢትዮጵያም ኾነ በመላው ዓለም አያድርስ!!!" በሚል ልባዊ ምኞትና ጸሎት፡ አጠቃልዬ፡ ነገሬን እዘጋለሁ።

## መፈጽም፤
## ለዚህ መጽሐፋዊው መልስ።

የዚህን፡ የኹለተኛውን ክፍል ጽሑፌን ከመዝጋቴ በፊት፡ እርስዎ (ምስተር ናፍታሊ) እና እርስዎን የመሰሉት ባልደረቦችዎ፡ በእውነተኛ ንስሐ፡ ወደእውነተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር ትመለሱ ዘንድ፡ እንዲሁም፡ በእኔ አማካይነት፡ በደረሰዎ፡ በፊተኛውም ኾነ፡ በዚህኛው፡ በኹለቱም ጽሑፍ መልእክታት ውስጥ ተገልጻ የቀረበችውን የእግዚአብሔር እውነት ትቀበሉ ዘንድ በመለመን፡ ምክሬንና ማሳሰቢያዬን፡ እነሆ፡ እንደገና ልኬልዎታለሁ።

በእርስዎ በኩል አስፈላጊ መስሎ ከታየዎት፡ እንደገና በግል ተገናኝተን፡ በዚሁ ጉዳይ ላይ በበለጠ እንድንነጋገር፡ ኢጋብዝዎ ዘንድ፡ ፈቃደኛነትዎንና አሳብዎን ቢገልጹልኝ ደስ ይለኛል፡ ይህን ብናደርግ፡ ስለዚሁ እርእስተ ነገር፡ የተሟላ እውቀትን ለማግኘት ይረዳዎታል ብዬ አምናለሁ።

በዚህ ባቀረብኩልዎ አሳብ የሚስማሙ ቢኾን፡ በምድር ላይ ሐሤት አድርገን፡ ወደእንድነታችን ዕቅፍ የምንቀበላችሁ፡ እናታችን ኢትዮጵያና እኛ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቿ ብቻ ሳንኾን፡ *"ንስሐ በሚገባ፡ በአንድ ኃጢአተኛ፡ በሰማያት፥ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት፡ ታላቅ ደስታ ይኾናል"* ሲል፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የምሳሌዎቹ መዝገቢያ እያደረገና *"የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና፡ ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ!"* እያለ በሰጠው[፻፴፰] ትምህርት እንደተናገረው፡ በሰማያትም ጭምር ነው እንጂ።

ዳሩ ግን፡ ይኾናል ተብሎ በማይታሰብ ውሳኔዎ፡ ይህን አርእስተ ጉዳይ በሚመለከት፡ ስለፈጸሙት ኃጢአት፡ ንስሓ ከመግባት፡ ምናልባት፡ ራስዎን ቢከለክሉ፥ ደግሞም፡ "የእግዚአብሔር እውነት፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት የምትሰጠው ምስክርነት" በሚል ርእስ፡ ከዚህ ቀደም ብሎ፡ በዕትም መልክ በደረሰዎትና አሁን፡ በበለጠ ተብራርቶ በተዘጋጀው፡ በዚህ በአሁኑ የመልስ ደብዳቤ፡ በኹለቱም ጽሑፎች ውስጥ የቀረበውን መልእክት ተቀብለው ለመፈጸም፡ ፈቃደኛ ባይኾኑ፡ ከእኔ በቀደሙት፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴና በእጨጌ ባስልዮስ አማካይነት፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም በተቀበልኩት፡ በተዋህዶ ሃይማኖቴ፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሥልጣን፡ ከዚህ የሚከተለውን የውግዘት ቃል ማስተላለፌን በይፋ አስታውቃለሁ፡፡

*በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፡ አሐዱ አምላክ! ወበስማ ለእምነ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ወላዲተ አምላክ፡ ዝ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው፡፡*

*በቅዱሱ ኪዳን፡ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት፡ የትስብእት አምላክነትና እንዲሁም፡ በራእየ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ ፭፥ ቁጥር ፭ ላይ፡ ተጽፎ የሚነበበው፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጡ የባሕርይ ገንዘቦቹ ናቸው፡፡ ይህም፡ "የእግዚአብሔር እውነት፡ ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት የምትሰጠው ምስክርነት" በሚለው፡ በዚህ መጽሐፍ፡ የመጀመሪያ ክፍል፡ በቀረበው መልእክት ውስጥ ተብራርቶ ተገልጿል፡፡*

*አሁን፡ ስማቸውና አድራሻቸው፡ በዚህ መጽሐፍ፡ በኹለተኛው ክፍል፡ መግቢያ ገጾች ላይ ሠፍሮ በሚገኘው፡ በራሳቸው ደብዳቤ የተጻፈው ግለሰብ፡ በዚሁ ደብዳቤያቸው ውስጥ ተከሥቶ እንደሚታየው፡ ከላይ የተጠቀሰውን፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፡ ትክክለኛ ትርጉሙን በምፀት ለውጠው፡ ለሟቹ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ በመስጠታቸው፥ የምሥጢረ ሃይማኖቱንም ነገር፡ በዚሁ መልክ አቀናብረው፡ አምላክነትን ለእርሳቸው በማጕናጸፋቸው፡ በእግዚአብሔር ላይ፡ ታላቁን፡ የስድብ ኃጢአት ፈጽመዋል፡፡*

*በዚህ ረገድ፡ ማለትም፡ ሟቹ ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ እንደአምላክ ተቆጥረው እንዲመለኩ ለማድረግ፡ በገሃድ በሚካኼደው፡ ይህን በመሰለው፡ የድፍረት ሙከራና የኑፋቄ ተልእኮ፥ እንዲሁም፡ በእግዚአብሔር ላይ፡ የስድብ ቃልን እንደመናገር በሚያስቆጥረውና ከላይ የተጠቀሰው፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፡ ለእርሳቸው እንደተነገረ አስመስሎ፡ ለእርሳቸው ለመስጠት በሚደረገው ሓሳዊ ጥረት፡ ከእኒሁ፡ ማንነታቸው ቀደም ብሎ ከተወሳው ግለሰብ ጋር፥ ወይም፡ ከማናቸውም ሌላ ግለሰብ ጋር፥ ወይም የግለሰቦች ማኅበር ጋር፡ በምንም ዓይነት ወይም በምንም መልክ፡ ኅብረትና ተሳትፎ ያለው፡ ማነኛውም ኢትዮጵያዊ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ የተቀደሰውን ሃይማኖቱን እንደካደና ተመሳሳዩን ታላቅ ኃጢአት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡*

*ስለዚህ፡ ይህን ኃጢአት የፈጸመው ኢትዮጵያዊ፡ ከዚህ ኃጢአቱ፡ በሥርዓቱና በአግባቡ ንስሓ ካልገባ በቀር፡ ወይም እስካልገባ ድረስ፡ ከቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቱ ተውግዞ የተለየ መኾኑን፡ በመንፈሳዊ ሥልጣኔ አስታውቃለሁ፡፡"*

ኢትዮጵያ፡

በዚህ መልእክት ውስጥ የሠፈረውን ጉዳይ፡ ሊያውቁ ለሚገባቸው ኹሉ፡ ቅጂው እንዲደርሳቸው የሚደረግ መኾኑን እገልጻለሁ።

ይህን፡ የመለኮታዊት መልእክት ጽሑፍ፡ እዚህ ላይ፡ ከዚህ በሚከተለው ቃል፡ አጠቃልላለሁ። ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉት ብቻ ሳይኾን፡ ለሌሎችም ጭምር፡ ጠቃሚ ትምህርትን ሊያበረክት የሚችለውን፡ ይህን ማብራሪያ ለማዘጋጀት፡ መንሥዔ ምክንያት ይኾነኝ ዘንድ፡ የቃል ኪዳን አምላኬ፡ ከዚህ በፊት፡ በእኔ አማካይነት፡ እንዲደርስዎ ሳደረገው መልእክቱ፡ የነቀፌታ ምላሽን፡ ያውም በብዕር ኪዳንዎ አጽድቀው፡ በጽሑፍ እንዲሰጡኝ፡ የገፋፋዎን መንፈስ፡ ወደእርስዎ ስለሰደደ፥ ለእኔ ደግሞ፡ የዘውድ መንግሥቱ በኾነችው ኢትዮጵያ፡ ተጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ስለተገለጸችው፡ መለኮታዊት እውነቱ፡ የምሰጠውን የምስክርነት ቃል፡ እንደገና፡ እንዲህ፡ በበለጠ ድፍረት ለማቅረብ የቻልሁበትን፡ የሚያበረታታ መንፈሱን በጸጋው ስላደለኝ፡ ለእርሱ፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋናዬን፡ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙም አቀርብለታለሁ።

የመለኮታዊው ንጉሥ፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የንግሥት እናቱ፡ የድንግል ማርያም በረከት፡ በኹላችንም ላይ ያድርብን ዘንድ፡ እጸልያለሁ።

\+ + +